# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 024 መስከረም 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

















# «ሀገራዊ ምክክሩ እዚህም እዚያም የሚታየውን ረብሻ ሊያስቀር የሚችል ነው»

-ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር



ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክሩ እዚህም እዚያም የሚታየውን ረብሻ በማስቀረት ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑን የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር እና የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ተናገሩ፡፡

ፕሮፌሰር በየነ በተለይ ለኢፕድ እንዳስታወቁት፤ በአሁኑ ወቅት እንደመልካም አጋጣሚ የተገኘው ሀገራዊ ምክክር ሊያመልጠን አይገባም፡፡

ፕሮፌሰር በየነ እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ምክክሩ መካሄድ አለበት። አሁን እየተካሔደ ያለው ጅማሮም ጥሩ የሚባል ነው። ይህ መልካም የሆነው አጋጣሚ እንዲያመልጠን ማድረግ የለብንም፡፡

በአሁኑ ወቅት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ እያካሔደ ያለው ሒደት አበረታች ነው ያሉት ፕሮፌሰር በየነ፤ ሌሎቹም ልብ እንዲገዙ የሚረዳም ጭምር ነው፤ ፀጥታ አደፍራሾቹ ሕዝቡ ከእነርሱ ጋር እንዳልሆነም የሚረዱበት እንደሚሆን ተስፋ አለኝ፤ በዚህ አጋጣሚም በጥባጮች ሊጋለጡ ይችላሉ ብለዋል።

ከዚህ በኋላ በዱር በገደሉ መረበሽ ሊቀር እንደሚችል የጠቀሱት ፕሮፌሰሩ፣ ይህ ምክክር

«ሀገራዊ ምክክሩ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ከኦሮሚያ ክልል የመኸር እርሻ 265 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

ገጽ 4

## በዋግ ኽምራ በተከሰተው ድርቅ ከ123ሺህ በላይ ዜጎች የዕለት ምግብ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል

**- መንግሥት በሁለት ዙሮች ከአራት ሚሊዮን ለሚበልጡ ዜጎች ድጋፍ አድርጓል**

**-የረጂ ድርጅቶች ድጋፍ ማቆም ጉዳቱን አባብሶታል**

ገጽ 4

# ለሆራ ሀርሰዴ ኢሬቻ በዓል አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- መስከረም 27 በቢሾፍቱ ከተማ ለሚከበረው የሆራ ሀርሰዴ የኢሬቻ በዓል አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራ መጠናቀቁን የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

የቢሾፍቱ ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ ገዛኸኝ ደጀኔ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መስከረም 27 ቀን 2016 ዓ.ም በቢሾፍቱ ከተማ ለሚከበረው ሆራ ሀርሰዴ የኢሬቻ በዓል ኅብረተሰቡን ያሳተፈ አጠቃላይ ዝግጅት ተደርጓል።

በከተማዋ የሚገኙ ሆቴሎችና መኝታ ቤቶች እንዲሁም የተለያዩ መስተንግዶ የሚያቀርቡ የንግድ ተቋማት በዕለቱ የሚታደሙ እንግዶችን በተሻለ መልኩ ማስተናገድ የሚችልበት መንገድ ላይ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

በአገልግሎት ሰጪ ሆቴሎች ላይ ችግር እንዳያጋጥም ከባለሀብቶች ጋር የተለያዩ ውይይቶች መደረጋቸውን አንስተው፤ በበዓሉ ታዳሚዎች ላይ የዋጋ ጭማሪዎች እንዳያጋጥሙ ሆቴሎችን የሚቆጣጠር ግብረኃይል በማቋቋም ከፍተኛ ክትትል ይደረጋል ብለዋል፡፡



ከፀጥታ ጋር በተያያዘ በቢሾፍቱ ከተማ በዓሉ ሰላማዊ በሆነ መልኩ እንዲከበር የክልሉና የፌዴራል ሰላም አስከባሪዎች፣ የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪዎችን ጨምሮ ወጣቶችና ፎሌዎች ተቀናጅተው የበዓሉን ሠላምና ደህንነት ለማስጠበቅ እየሠሩ መሆኑን

ለሆራ ሀርሰዴ ኢሬቻ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ወይዘሮ እናትዓለም መለሰ

## መዲናዋ ከዛሬ ጀምሮ ሦስት ታላላቅ መድረኮች ታስተናግዳለች

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከዛሬ ጀምሮ የተለያዩ ታላላቅ ዓለምአቀፍ፣ አህጉር አቀፍና ሀገር አቀፍ መድረኮችን የምታስተናግድ መሆኗን ከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ የኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ እናትዓለም መለሰ እንደገለጹት፤ ከተማዋ የፊታችን ቅዳሜ ከሚከበረው የኢሬቻ በዓል ጎን ለጎን ሦስት ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለምአቀፋዊ ኩነቶችን ታስተናግዳለች። መድረኮቹ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሲሆኑ ከመስከረም 24 እስከ ጥቅምት አንድ 2016 ዓ.ም ድረስ ይከናወናሉ።

የመጀመሪያው መስከረም 24 እና 25 የአፍሪካ ከንቲባዎች የሊደርሺፕ ኢኒሼቲቭ የተሰኘው እና የአፍሪካ ከንቲባዎች የርስ በርስ መማማሪያ መድረክ ይካሄዳል ያሉት ኃላፊዋ፤ በዚህም ከአፍሪካ ሀገሮች የሚመጡ የከተሞች ከንቲባዎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ከተሞች የሚመጡ ከንቲባዎች እና ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች ይሳተፋሉ ብለዋል።

ሁለተኛው መድረክ መስከረም 28 እና 29 የሚካሄደው የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም የልህቀት ማዕከልን ለማቋቋም የተዘጋጀ ዓለም አቀፍ ምክክር እንደሆነ ገልጸው፤ ከተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚመጡ የዘረፉ ምሁራን፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ኃላፊዎች፣ የፋውንዴሽኖች ኃላፊዎች እና ከተማዋ አመራሮች የሚሳተፉበት መሆኑን ገልጸዋል።


በምክክሩም የልቀት ማዕከሉን ስትራቴጂካዊ ዕቅድ እና ትልሞች እንዲሁም የንድፈ ሃሳብ ጥናቶች ቀርበው ውይይት ይደረግባቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ ከመስከረም 28 እስከ ጥቅምት 1 ቀን 2016ዓ.ም የሚካሄዱት የሀገር አቀፍ መሪዎች የልምድ ልውውጥ መድረኮች ናቸው። ሁሉም መድረኮች «ሕፃናት የነገ ተስፋ ለአዲስ አበባ» በማለት በተነደፈው ፕሮግራም ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው። በቆይታቸውም የአዲስ አበባ ከተማ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ሁኔታ ገለጻ፣ የመስክ ጉብኝት እና ውይይቶች የሚካሄዱ ሲሆን በተጨማሪም የከተማዋ ፓርኮች እና የልማት ሥራዎች ይጎበኛሉ።

መድረኮቹ ከተማዋ ሕፃናትን ለማሳደግ ምቹ የሆነች ምርጥ የአፍሪካ ከተማ የመሆን ራዕይዋን ታድሳለች፣ በለውጡ ማግስት ማሳካት የተቻሉ የሰው ተኮር የልማት ፕሮግራሞች ውጤታማነት እውቅና እንዲያገኙ ይረዳል ብለዋል።

# በመዲናዋ በሚገኙ ወረዳዎች የኢሬቻ በዓል በድምቀት ይከበራል

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በሚገኙ ወረዳዎች ባህላዊ እሴቱን በሚያጸባርቅ መልኩ የኢሬቻ በዓል በድምቀት እንደሚከበር የአራዳ፣ የለሚ ኩራና የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች ገለጹ።

የአራዳ ክፍለ ከተማ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ደሳለኝ ደበሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዓሉ የፍቅር፣ የመቻቻልና የምስጋና በመሆኑ የመዲናዋን ገጽታ በሚያደምቅ ሁኔታ በክፍለ ከተማው በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች ይከበራል።

እንደ አቶ ደሳለኝ ገለጻ፤ ኢሬቻ በዓል አካባበር ላይ ወጣቶችና የወረዳው ነዋሪዎች የሚሳተፉበት የፓናል ውይይት፣ የባህል ሲፖዚዬምና የተለያዩ መሰናዶዎች የሚቀርቡባቸውት ዝግጅቶች ይካሄዳሉ።

ክፍለ ከተማው ሆራ ፊንፊኔን ለማክበር ወደ መዲናዋ ለሚመጡ እንግዶች የምግብና የመኝታ አገልግሎት ችግር እንዳያጋጥም ሰፊ ዝግጅት ማድረጉን አቶ ደሳለኝ አስገንዝበዋል።

የኢሬቻ በዓል ከተያዘው ሳምንት ጀምሮ በወረዳዎች ደረጃ እየተከበረ መሆኑን የገለጹት አቶ ደሳለኝ፤ በዓሉ በክፍለ ከተማው ደረጃ መስከረም 24 ቀን ከሰዓት በኋላ ከአንድ ሺህ በላይ ኗሪዎች በተገኙበት በድምቀት ይከበራል ብለዋል።

የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፉፋ ሶርሳ በበኩላቸው፤ ክፍለ ከተማው ለመዲናዋ መግቢያ በር በመሆኑ የበዓሉ አከባበር በሦስት ክላስተር እንዲደራጅ ተደርጓል።

በዓሉ በጎሮ ክላስተር፣ በአያት (ደራርቱ አደባባይ) እና በጣፎ ክላስተር የሚከበር መሆኑን የጠቆሙት አቶ ፉፋ፤ በዓሉን በደማቅ ሁኔታ ለማክበር የሚመጡ እንግዶች የሚያስተናገዱባቸውን መዝናኛዎችን የሚያዘጋጁ ኮሚቴዎች መዋቀራቸውን አስታውቀዋል።

በሚሊዮን የሚቆጠር የበዓሉ ታዳሚ ወደ መዲናዋ እንደሚገባ ይጠበቃል ያሉት አቶ ፉፋ፤ እንግዶችን በሠላማዊ ሁኔታ በማስተናገድ የኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ እንደሚገባ አመልክተዋል።

ለበዓሉ ታዳሚዎች የመኝታ አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎች እንግዶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማስተናገድ የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ኢሬቻንና መሰል የአደባባይ በዓላትን የጋራ ማድረግና ለሁሉም ማኅበረሰብ በማሳየት ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ እንደሚገባም ተናግረዋል።

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ቢሊሱማ አለማየሁ፤ በክፍለ ከተማ በሚገኙ ወረዳዎች በዓሉን በማስመልከት የፓናል ውይይት የሚካሄድ መሆኑን ገልጸዋል።

በክፍለ ከተማው በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች የበዓሉን ባህላዊ እሴቱን በሚያንጸባርቁ የተለያዩ የመዝናኛ ዝግጅቶች ይከበራል ብለዋል።

ክፍለ ከተማው ሆራ ፊንፊኔን ለማክበር ወደ መዲናዋ መግቢያና ወደ ቢሾፍቱ ሆራ አርሰዴን ለማክበር ለሚሄዱ ታዳሚዎች መውጫ በር ነው ያሉት አቶ ቢሊሱማ፤ የኢሬቻን ትውፊት የሚያሳዩ የእንግዶች አቀባበልና ባህላዊ የምግብ ዝግጅት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

ኢሬቻ የሠላም የአንድነትና የወንድማማችነት ዓርማ በመሆኑ ኢትዮጵያዊነትን በሚያጎላ መልኩ ሊከበር እንደሚገባ አቶ ቢሊሱማ ገልጸዋል።

# የአምስት ዓመቱ የዲጂታል ስትራቴጂ የታቀደለትን ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት እየተተገበረ ያለው የአምስት አመቱ የዲጂታል ስትራቴጂ በታቀደለት መሠረት ውጤት እያስመዘገበ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ባልቻ ሮባ አስታወቁ።

ዳይሬክተሩ ለ2023 «የአይ ቲ ዩ» ክልላዊ ልማት ፎረም የማስጀመሪያ መርሐ ግብር ላይ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ የተጀመረው የአምስት አመቱ የዲጂታል ስትራቴጂ ትግበራ ግማሽ ጉዞውን አጠናቋል። እስካሁንም በኢንተርኔት ተደራሽነት፤ በብሮድባንድ መሠረተ ልማትና የመንግሥት አገልግሎቶችን በዲጂታል መንገድ በማቅረብ ረገድ ከፍተኛ ለውጥ ማስመዝገብ ተችሏል።

ትግበራው ሲጀመር የነበረውን ከ18 ሚሊዮን ያልበለጠ የሞባይል ስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ በአሁኑ ወቅት 36 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል ያሉት ኢንጂነር ባልቻ፣ በርካታ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችም እየተከናወኑ መሆኑንና የወቅቱ ቴክኖሎጂ የደረሰበት የ5ጂ አገልግሎት በሀገሪቱ እየተተገበረ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

ኢንጂነር ባልቻ እንዳሉት፤ የቴሌኮም አገልግሎት ለግል ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆን በማስቻል ተጨማሪ አገልግሎቶች ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል። ዜጎች በተለያየ መስክ የሚያገኟቸውን አገልግሎቶች በዲጂታል አሠራር ለማድረግ የዲጂታል መታወቂያ ወሳኝ በመሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ አንድ መታወቂያ እንዲኖረው የተጀመረው ሥራም አበረታች ለውጥ እያስመዘገበ ይገኛል። እንደአጠቃላይም በቀጣይ ሁለት አመታት ተኩል የነበሩ ክፍተቶችን በማረም እቅዱን ለማሳካት የሚሠራ ይሆናል።

በተጨማሪም በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ስጋትነቱ እየጨመረ የመጣውን የሳይበር ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል አቅም እየተገነባ መሆኑንም ጠቁመው፤ በቀጣይ ሁለት አመታት ተኩል የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመሻገር የሚያስችል አቅም በመገንባት እቅዱን ለማሳካት የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

የዲጂታል ስትራቴጂ ውጤታማነት የኢትዮጵያን የውስጥ እድገት ከማቀላጠፍ ባለፈ ሀገሪቷ በዓለምአቀፍ ደረጃ ለሚኖራት ግንኙነቶችም ትልቅ ፋይዳ አለው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የሚሠሩት ሥራዎች በተባበሩት መንግሥታት የተቀመጠውን የዘላቂ ልማት እቅድ ከግምት በማስገባት መሆኑን ጠቁመዋል።


ኢንጅነር ባልቻ ሮባ፤

እ.አ.አ በ2015 የተቀመጠው የዘላቂ ልማት ግብ «ሁሉን አቀፍና አካታች እድገትና ብልጽግናን በማረጋገጥ ድህነትንና ረሃብን ማጥፋት» የሚል ዓላማ ያለው ሲሆን በስሩም 17 ግቦችና 160 ዓላማዎች አሉት። በዋናነትም ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሥራ ዕድል ፈጠራን በማበረታታት ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለግብርናና ለሌሎችም ዘርፎች ልማትን በማምጣት ብልጽግናን ማረጋገጥ ነው።

ነገር ግን የኮሮና ወረርሽኝን፣ ግጭቶችንና የተፈጥሮ አደጋዎችን ጨምሮ እቅዱን የሚያሰናክሉ በርካታ ተግዳሮቶችን አስተናግዷል። የእቅዱ የግማሽ ወቅት ጉዞ ግምገማ በተካሄደበት ወቅትም ያልተሳኩና ወደኋላ የቀሩ ግቦች እንዳሉ ለመለየት የተቻለ ሲሆን በቀጣይ ሰባት አመታት እቅዱን ለማሳካት ፈጣን ሥራዎች መሥራት ከሁሉም የሚጠበቅ መሆኑ ተመላክቷል።

የዘላቂ ልማት ግቦች እቅድ ከሰባት አመታት በኋላ የሚጠናቀቅ በመሆኑ ኢትዮጵያ በእነዚህ ጊዜያት በዓለምአቀፍ ደረጃ የተቀመጡትን ግቦች እንደ ሀገር ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የምትንቀሳቀስ መሆኑንም ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

# በመዲናዋ ለኑሮ የማይመቹ ቆሻሻ ስፍራዎች ለምተው ለነዋሪዎች ማራኪ እንዲሆኑ ተደርገዋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ለኑሮ የማይመቹ ቆሻሻ ስፍራዎች ለምተው ለነዋሪዎች ማራኪና ሳቢ እንዲሆኑ ተደርገዋል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ።

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ግማሽ ቢሊዮን ብር ወጪ ከ54 ሄክታር በላይ በሆነ መሬት ላይ የለሙ የመንገድ አካፋይና የሞዴል መንደሮች አረንጓዴ ስፍራዎች ተጠናቀው ሙሉ በሙሉ ለአገልግሎት ክፍት ተደርገዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤና ሌሎች የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች የአረንጓዴ ስፍራዎቹን ፕሮጀክቶቹን ትናንት ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።

በወቅቱ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፤ ለኑሮ የማይመቹና ለጤና አስቸጋሪ የሆኑ ስፍራዎች ለምተው በአረንጓዴ ተክሎች በመሸፈናቸው ለአረጋውያን ማረፊያና ለሕፃናት መጫወቻ ስፍራዎች ሆነዋል።

አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብና ሳቢ የማድረጉ ተግባር በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት በአንድነት ፓርክ፣ በወዳጅነት አደባባይና በእንጦጦ ፓርክ ቀደም ብሎ ተጀምሯል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ የከተማ አስተዳደሩም ይህንኑ አርዓያነት በመከተል ነዋሪውንና ባለሀብቱን በማስተባበር የአረንጓዴ ልማት ሥራውን በስፋት እያከናወነ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ የአረንጓዴና የውበትን ደረጃ ለማሟላት በቀጣዮቹ ሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የከተማዋን የአረንጓዴ ሽፋን ከነበረበት 15 በመቶ ወደ 30 በመቶ ከፍ ለማድረግ ማኅበረሰቡን በማስተባበር እየተሠራ መሆኑን አስታውሰዋል።

የአረንጓዴ ልማት ዕቅዱን ለማሳካትም ሁሉም የከተማዋ ነዋሪዎች ድጋፋቸውን ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ ከንቲባዋ ተናግረዋል።

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ግማሽ ቢሊዮን ብር ወጪ ከ54 ሄክታር በላይ በሆነ መሬት ላይ የለሙ የመንገድ አካፋይና የሞዴል መንደሮች አረንጓዴ ስፍራዎች ለከተማዋ ተጨማሪ ውበት የሰጡ መሆናቸውን አመልክተዋል።

ከንቲባዋ፤ ለሥራው መሳካት ድጋፍ ላደረጉ የክፍለ ከተማው አመራሮችና ባለሀብቶች ምስጋና አቅርበዋል።

የአረንጓዴ የልማት ሥራው ግማሽ ቢሊዮን ብር ወጪ የተደረገበት ሲሆን ወጪውም ከመንግሥትና በክፍለ ከተማው የሚገኙ ባለሀብቶችን በማስተባበር መሸፈን ተችሏል ብለዋል።

«50 ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለ50 ሰው ጌጡ ነው» ያሉት ከንቲባዋ፤ ባለሀብቱ በእንደዚህ ዓይነት የልማት ሥራዎች ላይ እያደረገ ያለው ተሳትፎ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል።

በልማት ሥራው 15 ባለሀብቶች ተሳትፎ አድርገውበታል፤ በሥራው ሂደት ከ12 ሺ ለሚበልጡ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን አስታውሰዋል።

በቋሚነትም የአትክልት ለእንክብካቤና ተያያዥ የሥራ መስኮች ከአምስት ሺህ በላይ ወጣቶች በማኅበር ተደራጅተው ወደ ሥራው እንደሚገቡ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ከንቲባ አዳነች በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኘውን የለሚ ፓርክም ጎብኝተዋል። በመርሐ ግብሩ ላይ ከንቲባ አዳነች አቤቤና የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አመራር አባላት ተሳትፈዋል።

# ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚያገለግል ጨው በበቂ መጠን አለመቅረብ ምርትና ምርታማነት ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው

## -ኢንዱስትሪዎች በዓመት ከሚፈልጉት ጨው ውስጥ እየቀረበ ያለው ከ50 በመቶ በታች ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚጠቀሙት የጨው ምርት በበቂ መጠን አለመቅረብ በፋብሪካዎች ምርትና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ። ጨውን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በዓመት ከሚፈልጉት የጨው መጠን ውስጥ በአሁኑ ጊዜ እየቀረበ ያለው ከ50 በመቶ በታች መሆኑ ተገልጿል።



አቶ ሀሰን መሐመድ

በኢንዱስትሪዎች ጨው ፍላጎትና አቅርቦት ላይ ያተኮረ የባለድርሻ አካላት የውይይት መድረክ የከፈቱት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሀሰን መሐመድ እንዳሉት፤ ጨውን በግብዓትነት ከሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች መካከል ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ የቆዳና ቆዳ ውጤት አምራቾች፣ ኬሚካል አምራች ኢንዱስትሪዎችና መጠጥ ኢንዱስትሪዎች ይገኙበታል። ለእነዚህ ኢንዱስትሪዎች በቂ ጨው ምርት ማቅረብ ባለመቻሉ የኢንቨስትመንት መስፋፋት፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የውጭ ምንዛሪ ከማግኘትና ገቢ ምርትን መተካት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል።

በሁሉም ዘርፍ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ያላቸው ዓመታዊ የጨው ፍላጎት 26 ሚሊዮን 353 ሺህ 846 ኩንታል ሲሆን ከዚህ ውስጥ እየቀረበ ያለው ግን ከ50 በመቶ በታች ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ኢትዮጵያ ሰፊ የጨው ሀብት ቢኖራትም ያለውን ሀብት በሚገባው ልክ ጥቅም ላይ ማዋል አልተቻለም ብለዋል።

እነዚህንና ተዛማጅ ችግሮችን ለመቅረፍና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ መጀመሩን አስታውሰው፤ እስካሁን ድረስ ሥራ አቁመው የነበሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ መመለስን ጨምሮ ትልልቅ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

በጨው አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለው ትስስር አለመጠናከር፣ የጨው አቅራቢዎች ተደራሽነት ውስን መሆን፣ በተቋማት መካከል ያለው ግንኙት በሚፈለገው መጠን አለመጠናከር ከሚስተዋሉ ችግሮች መካከል እንደሚገኙበት ጠቅሰው፤ በተጨማሪም በግብይት ሰንሰለቱ ላይ የደላሎች መብዛት፣ የሚወጡ አሠራሮችና መመሪያዎች በአግባቡ አለመተግበርና ከጎረቤት ሀገራት ጨው በሕገወጥ መልኩ እንዲገባ በር መክፈቱ ዘርፉ ላይ ያሉ አንኳር ችግሮች መሆናቸውን ዘርዝረዋል።

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍም የተቋማትን ቅንጅታዊ አሠራር ማጠናከር፣ ሀገራዊ የጨው ፍላጎትን በየጊዜው ማጥናት፣ በጨው አምራች አካባቢዎችና ተጠቃሚዎች ያለውን የአሠራር ችግር መፍታት እንደሚጠበቅ ጠቅሰው፤ በተጨማሪም የጨው አቅርቦት ወጥና ዘላቂ እንዲሆን ማድረግ፣ የጨው ምርት ወደ ውጭ የሚቀርብበትን አማራጭ ማየትና መሰል እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል ነው ያሉት።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያለውን የጨው ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውልና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲቻል በቁርጠኝነት እንደሚሠራ ጠቁመው፤ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ አሳስበዋል።

ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ የቆዳና ቆዳ ውጤት አምራቾች፣ ኬሚካል አምራች ኢንዱስትሪዎችና መጠጥ ኢንዱስትሪዎች ጨውን በግብዓትነት ከሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች መካከል መሆናቸው ተመላክቷል።

# «አባገዳዎች የኢሬቻ በዓል ታዳሚዎችን ለተያዘው የሠላም አጀንዳ ስኬት ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል»

- አቶ አለማየሁ ኃይሌ
በኦሮሞ ባህል ማዕከል የባህልና ታሪክ ዘርፍ ዳይሬክተር

**አስቴር ኤልያስ**



አዲስ አበባ፡- አባገዳዎች እንደ ሀገር ለተያዘውና ታላቅ ለሆነው የሠላም አጀንዳ ስኬት የኢሬቻ በዓል ታዳሚያንን ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ በኦሮሞ ባህልና ቱሪዝም የኦሮሞ ባህል ማዕከል የባህልና ታሪክ ዘርፍ ዳይሬክተር አቶ አለማየሁ ኃይሌ አስታወቁ።

የኦሮሞ ባህልና ታሪክ ተመራማሪው አቶ አለማየሁ ኃይሌ ለኢፕድ እንዳስታወቁት፤ ኢሬቻ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ካሉ በርካታ ተቋማት ውስጥ አንኳር እና ትልቁ ነው። ኢሬቻ የጋራ የምስጋና ቀን ሲሆን፣ ኦሮሞ በጋራ ወደአደባባይ ወጥቶ አምላኩን የሚያመሰግንበት በዓል ነው። በዚህ ታላቅ በዓል ላይ ዘንድሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተያዘው ታላቅ የሠላም አጀንዳ እንዲሳካ አባገዳዎች የበዓሉን ታዳሚዎች ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

አቶ አለማየሁ እንደተናገሩት፤ በኢሬቻ በዓል ላይ አባ ገዳዎች የሚያደርጉት ንግግር እና ምረቃት አለ። አንድ የፖለቲካ አመራር ከሚናገረው በላይ የኦሮሞ ሕዝብ በአባ ገዳ የሚነገረውን ንግግርም ሆነ ምርቃት በማጤን ያዳምጣል። ይህ የማዳመጥ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የተነገረውንም ነገር በአግባቡ ከመፈጸም ጋር የሚያያዝ ነው። ታዳሚው ከሠላም ጋር ተያይዞ በባህላዊ መሪው የሚነገረውን ነጥብ አስተውሎ የሚተገብር ስለመሆኑ ጥርጥር የለውምና አባገዳዎች ለሠላሙ ስኬት የበኩላቸውን እንደሚያደርጉ ይጠበቃል።

ከዚህ አኳያ የፖለቲካ መሪዎች የተያዘው ታላቅ የሠላም መርሐግብር ስኬታማ ይሆን ዘንድ ተሰሚነት ያላቸውን አካላት ቢጠቀሙ መልካም ነው ያሉት አቶ አለማየሁ፣ ሠላም ለማምጣት በተለይም አባገዳዎች፣ የጎሳ መሪዎችና ሌሎችንም በመጠቀም በሕዝቡ ውስጥ ትልቁን ሥራ መሥራት አለባቸው ብለዋል።

እንደ አቶ አለማየሁ ገለጻ፤ እንደ ኢሬቻ ዓይነቱን መልካም እሴት በመጠቀም የተጎዳው እንዲካስ፣ የበደለውም እንዲክስ ማድረግ፣ የተከፋውንም ማስታረቅ ይቻላል። አንዱ ለሌላው የሚያስብ፣ የሚጠነቀቅ፣ የሚሳሳ እንዲሆን በማድረግ የተሳሳተውን ነገር መመለስም ይቻላል። ይህ የኢሬቻ ዓይነቱ ታላቅ እሴት በሌሎቹም አካባቢዎች ያለ እሴት እንደመሆኑ እንደዚህ ዓይነቶችን በማቀፍ የተያዘውን ትልቅ እቅድ ስኬታማ ማድረግ አለባቸው። ከሠላም ላለመጉደልም በፈጣሪ ፊት ለሠላም ራስን ዝግጁ ማድረግ ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው።

ይህ የሠላም አጀንዳ ስኬታማ ይሆን ዘንድም መልካም ነገር አድራጊ የሆኑት ሁሉ እውነት ብቻ ይዘውና እሱን ብቻ መሠረት አድርገው እንዲሠሩ ለአባገዳዎችም ሆነ ለሌሎች ግንዛቤ መስጠት መልካም ነው። ሕዝቡ ግን አባገዳዎች የሚሉትን ሰምቶ ከተስማማ በኋላ በጎን ሌላ ነገር የሚሠራ ከሆነ ደግሞ ከክህደት የሚቆጠር ነው ብለዋል።

የኦሮሞ ባህልና ታሪክ ተመራማሪው እንደተናገሩት፤ ፊትን ወደተዘረጋው ሠላም በማዞር መገፋፋትን መግታት ያስፈልጋል። እርስበእርስ መገዳደሉ ቀርቶ ልጆች በሠላም ወደትምህርት ቤት ሄደው ሊመለሱ ይገባል።

ሠላም መፍጠር ማለት የአንድ ወገን ዕጣ ፈንታ ብቻ አይደለም ያሉት አቶ አለማየሁ፤ ሠላም መፍጠር በበዳይም በተበዳይ መካከል የሚደረግ ቃል ኪዳን እንደመሆኑ የሁለቱን ማለት የበዳይንም የተበዳይንም ስምምነት ግድ የሚል ነው ሲሉ አስረድተዋል። ብሔራዊ እርቅንም ብሔራዊ ሠላምንም ማካሄድ የሚቻለው በዚህ ዓይነት መንገድ እንደሆነ ገልጸዋል።

የኢሬቻ ቀን ደግሞ አጋጣሚ ሆኖ የእርቅ፣ ምልጃ እና የሠላም ቀን ነው ያሉት የኦሮሞ ባህልና ታሪክ ተመራማሪው፣ እርቅ መውረድ ያለበት ከፈጣሪ ጋር ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ እርስ በእርስ መተራረም እና ወደሠላም ስምምነት መምጣት ነው ሲሉ ተናግረዋል። ኢሬቻ ይህን ማድረግ እንደሚገባ የሚያስቀምጥ እንደሆነም አስገንዝበዋል።

ዜና

# ከኦሮሚያ ክልል የመኸር እርሻ 265 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

ሄለን ወንድምነው



አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ከ2015/16 የመኸር እርሻ ሥራ 265 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ ስምንት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለምቷል።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ በሪሶ ፈይሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015/16 የመኸር እርሻ ሥራ ስምንት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር በማልማት 265 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት እየተሠራ ነው።

በመኸር እርሻው እየለሙ ከሚገኙት ሰብሎች መካከል ስንዴ፣ ጤፍ፣ ሩዝና የተለያዩ ሰብሎች እንደሚገኙበት አቶ በሪሶ አስታውቀዋል።

የዝናብ ስርጭቱ ከቦታ ቦታ የተለያየ በመሆኑ ቀድሞ የክረምት ዝናብ በገባባቸው አካባቢዎች ላይ በዘር የመሸፈን ሥራው ተጠናቋል ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ በሌላ በኩል በቅርቡ ዝናብ መጣል በጀመረባቸው የባሌ አካባቢዎች በዘር የመሸፈን ሥራ መጀመሩን አመላክተዋል።

በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ቀደም ብለው የተዘሩት ሰብሎች እየደረሱ በመሆኑ ከሚቀጥለው ወር ጀምሮ ምርት ለመሰብሰብ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

በ2015/16 የመኸር እርሻ ሥራ ላይ የተዘሩ ሰብሎች ለመሰብሰብ እስከሚደርሱ የመንከባከብ፣ ከአረም፣ ከበሽታና በጸረ-ተባይ ኬሚካል በሽታዎችን የመከላከል ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

እንደ አቶ በሪሶ ገለጻ፤ በምሥራቅ ሐረርጌ ተከስቶ የነበረውን የአንበጣ መንጋ ለመከላከል የኬሚካል ርጭት ተደርጓል። በተከናወነው ሥራም የአንበጣ መንጋው የከፋ ጉዳት ሳያደርስ መቆጣጠር ተችሏል።

በተመሳሳይ በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች፣ በምሥራቅ ሸዋና አርሲ አካባቢ የተከሰተው የግሪሳ ወፍ በሰብል ላይ መጠነኛ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን፤ ጉዳቱን ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር የኬሚካል ርጭት እየተከናወነ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

በቀጣይም በየቀበሌው የሚገኙ የልማት ጣቢያ ሠራተኞችና የግብርና ባለሙያዎች በሰብል ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎችን፣ የአንበጣ መንጋ፣ የግሪሳ ወፍና የተለያዩ ችግሮችን ለመከላከል ከአርሶ አደሩ ጋር በቅርበት እንደሚሠሩ አመላክተዋል።

የተያዘውን የመኸር እርሻ ዕቅድ በማሳካት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የኑሮ ውድነቱን ማረጋጋት፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት፣ እንዲሁም የግብርና ምርት የወጪ ንግድን ለማሳደግና የገበያ ትስስር ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

የግብርና ሥራን ለማዘመን እየተሠራ ነው ያሉት አቶ በሪሶ፤ አርሶ አደሩ ከእርሻ ሥራ እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ሜካናይዜሽን እንዲጠቀም የማድረግና አርሶ አደሩን ወደ ኢንቨስትመንት የማሸጋገር ሥራ እየተከናወነ ነው ብለዋል።

# በዋግ ኽምራ በተከሰተው ድርቅ ከ123ሺህ በላይ ዜጎች የዕለት ምግብ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል

## - መንግሥት በሁለት ዙሮች ከአራት ሚሊዮን ለሚበልጡ ዜጎች ድጋፍ አድርጓል

## -የረጂ ድርጅቶች ድጋፍ ማቆም ጉዳቱን አባብሶታል

አዲሱ ገረመው



አዲስ አበባ፡- በዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን በተከሰተው ድርቅ ከ123ሺህ በላይ ዜጎች የዕለት ምግብ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው የዞኑ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ። የረጂ ድርጅቶች ድጋፍ ማቆም ጉዳቱን እንዳባባሰው ተገልጿል።

የዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ምህረት መላኩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ የ2015 ዓ.ም የክረምት ዝናብ ስርጭት በመዛባቱ ምክንያት ድርቅ ተከስቷል። በሁሉም የብሔረሰቡ አስተዳደር ወረዳዎች የክረምቱ ዝናብ ዘግይቶ መጀመሩንና ፈጥኖ መውጣቱን አስታውቀዋል። በዚህም በአራት ወረዳዎችና 40 ቀበሌዎች ድርቁ የከፋ ጉዳት ማድረሱን ነው የገለጹት። ከ123ሺህ በላይ ዜጎች የዕለት ምግብ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸውም ጠቁመዋል።

በሰሃላ ሰየምት ወረዳ ባሉት 13 ቀበሌዎች በዘር ተሸፍኖ ከነበረው ከስምንት ሺህ 13 ሄክታር በላይ መሬት በድርቁ ምክንያት ከስሞ መቅረቱን ጠቅሰዋል። በአካባቢው አንድ ሺህ 236 የሚሆኑ የተለያዩ እንስሳት በምግብ እጦት ምክንያት መሞታቸውንም ተናግረዋል። አርሶ አደሮች እንስሳትን ይዘው መኖ ወደሚገኝበት አጎራባች ወረዳዎች እየተሰደዱ እንደሆነም ጠቁመዋል። በዝቋላና አበርገሌ አጎራባች ቀበሌዎች ላይም ተመሳሳይ ችግሮች እንዳሉ ገልጸዋል።

በዞኑ በድርቁ አስከፊ ጉዳት የደረሰው በሦስት ወረዳዎችና 26 ቀበሌዎች ቢሆንም፤ ዝናብ በመዝነብም ሆነ ባለመዝነብ በምርትና ምርታማነት ተጽዕኖ ችግሩ የተፈጠረባቸው አራት ወረዳዎችና 40 ቀበሌዎች ልዩ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ብለዋል። በእነዚህ አካባቢ ያሉ 123ሺህ 84 ዜጎችም የዕለት ምግብ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ገልጸዋል።

አካባቢው ዝናብ አጠርና የድርቅ ተጋላጭ መሆኑን የገለጹት አቶ ምህረት፤ ቀደም ብሎ እንደ ሀገር የአጋር አካላት ድጋፍ መቋረጡ ድርቁን እንዳባባሰውም ተናግረዋል። አካባቢው ከሁለት ዓመታት በላይ ጦርነት ውስጥ የነበረና ማገገም በጀመረበት ማግስት ድርቁ መከሰቱ የማኅበረሰቡን ችግር የከፋ ማድረጉንም አስታውቀዋል።

ክልሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ጨርሶ ወደ ተግባር ለመግባት ጥረት ላይ እንዳለ በመግለጽ የተጋለጭ ቁጥሩ እንዳይጨምር ዓለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶችን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት እንዲሰጡም ጠይቀዋል። የክልሉ መንግሥትና አንዳንድ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በተለያዩ ድጋፎች ለመሳተፍ ቢያስቡም መዘግየቶች እንዳሉ ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አታለለ አቡሀይ በበኩላቸው፤ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ድርቅና ጎርፍ መከሰቱን ገልጸው፤ በተለይ በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች ተብለው ከተለዩት ውስጥ የዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን አንዱ መሆኑንና መንግሥት በሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች ጊዜያዊ ምግብ እጥረት አጋጥሟቸው የከፋ ችግር ውስጥ ላሉ ዜጎች ከራሱ መጠባበቂያ የምግብ ክምችት መጋዘኖች ወጪ አድርጎ በሁለት ዙሮች ለአራት ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ ማድረጉን ተናግረዋል።

ከ54 ሺህ በላይ ኩንታል አልሚ ምግብ፣ ከአንድ ሚሊዮን ሊትር በላይ ዘይትና ከ600 መቶ አስር ሺህ በላይ ኩንታል ሰብዓዊ እርዳታን የጫኑ ከ150 በላይ ተሽከርካሪዎች በመላው ሀገሪቱ እርዳታ ወደሚያስፈልጋቸው ዜጎች መንቀሳቀሳቸውን ገልጸዋል። ድጋፉ በዚህ አካባቢ ያሉትንና የቅድሚያ ቅድሚያ የሚያስፈልጋቸው ዜጎችንም እንደሚያካትት ነው የገለጹት።

እንደ አቶ አታለለ ገለጻ፤ የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅትና አጋር አካላት በኢትዮጵያ ለተወሰኑ ወራት ምግብ ነክና ሌሎችንም ሰብዓዊ ድጋፎች ማቋረጣቸውን ተከትሎ መንግሥት ሰሞኑን የሁለተኛ ዙር ድጋፍ አድርጓል። እርዳታው በየ45 ቀኑ የሚደረግ ሲሆን፤ አሁንም የከፋ ችግር ውስጥ ላሉና ቅድሚያ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች የሚደረገው አፋጣኝ ድጋፍ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ድጋፍ ካቋረጡት አንዳንድ አጋር አካላት ድጋፉን ለመጀመር ፍላጎታቸውን ቢገልጹም እስካሁን ወደ ተግባር አልገቡም ያሉት አቶ አታለለ ፤ ከተቋቋሙበት ሰብዓዊ ድጋፍ የማድረግ ዓላማ አንጻር መንግሥትን አግዘው ችግር ያጋጠማቸውን ዜጎች ሊረዱ ይገባል። በሌሎች ሀገራት ላይ የሚያደርጉትን ድጋፍ ሰብዓዊነት ተሰምቷቸው በኢትዮጵያም ወደ ቀደመ ሥራቸው ተመልሰው ድጋፉን እንዲቀጥሉ መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት ንግግሮችን እያደረገ ነው። ተቋማቱ ያቋረጡትን ድጋፍ እንዲቀጥሉ አሁንም የዲፕሎማሲ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

# «ሀገራዊ ምክክሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መካሄድ ይኖርበታል ሲሉ አስረድተዋል።

ፕሮፌሰር በየነ እንደተናገሩት፤ ምክክር መካሄዱ የሚያሳጣው አንዳች ነገር የለም፤ ይልቁኑንም የሚጨምረው መልካም ነገር በርካታ ነው። ሚዛን የሚደፋው የሕዝብ ቁጥርም በዚህ ምክክር ላይ አሉታዊ የሆነ አቋም አይኖረውም። ስለሆነም ፀጥታውን የሚያደፈርሱ አካላት ምክክሩ እንዳይካሄድ ቢፍጨረጨሩም እንደስጋት ተወስዶ የቀረበውን መልካም አጋጣሚ ማስመለጥ አይገባም።

ፕሮፌሰር በየነ፣ አንዳንድ ጽንፈኞች በተለይ ለኢትዮጵያ የማይመጥን ገጽታ እያላበሱ ስሟን ለማጠልሸት እንደሚሯሯጡም ጠቁመው፤ ይሁንና ኢትዮጵያ እነሱ ከሚሏት በተቃራኒ ያለች ሀገር ናትና ለዚህ አትበገርም ብለዋል።

ፕሮፌሰሩ እንዳሉት፤ የዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ኢትዮጵያ በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እያካሔደች ያለውን ሒደትን የሚያዩት ከራሳቸው ጥቅም አኳያ ነው። አንድ ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር ከኢትዮጵያ ጋር መወዳጀት የማይፈልግ የውጭ ሀገር መንግሥት አለመኖሩን ነው። ኢትዮጵያ ዝነኛም ታሪካዊም ሀገር ናት። ስለዚህ ከዚህች ሀገር ጋር መወዳጀት የማይፈልግ ሀገር የለም። ይልቁኑ ከኢትዮጵያ ጋር ለመወዳጀት የሚደረግ ሽሚያ ይበዛ ይሆናል እንጂ ሆነ ብሎ ኢትዮጵያን ለማፍረስና ለመበታተን የሚያስብ መንግሥት ይኖራል ተብሎ አይታሰብም።

ኢትዮጵያ ብትፈርስ የሚጠቀም አይኖርም። የኢትዮጵያ መፍረስ በብዙ የሚያጎድል እንደሆነ መንግሥታት አሳምረው ያውቁታል ያሉት ፕሮፌሰር በየነ፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ፣ በጠቅላላ በአፍሪካ እና በዓለምአቀፉ ዘንድ ተፈላጊ ሀገር ናት ብለዋል። ለዚህ የሚሆን ማሳያ የቅርቡን ብቻ ማስታወስ በቂ ነው ሲሉ ጠቅሰው፤ በአህጉራችንም ሆነ በሌላ አህጉር በኢኮኖሚያቸው የሚበልጡና ሊመረጡ የሚችሉ ብዙዎች እያሉ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል እንድትሆን መመረጧ ተፈላጊነቷን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

# ስሆራ ሀርሰዴ ኢሬቻ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አስታውቀዋል።

በዓሉ ሠላማዊ በሆነ መንገድ እንዲከበር በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ከከተማው ነዋሪዎች ጋር ሰፊ ውይይቶች መደረጋቸውን ጠቁመው፤ በካሜራና በተለያዩ ቴክኖሎጂ በመታገዝ በዓሉ በሚከበርበት ስፍራ፣ በዋና ዋና መንገዶችና በመሀል ከተማው ላይ አስፈላጊው ቁጥጥር እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

በዓሉ የሚከበርበትን ቦታ ከአባ ገዳዎች፣ ፎሌዎችና አደ ሲንቄዎች ጋር በመሆን የማጽዳትና የማዘጋጀት ሥራዎች ሲከናወኑ መቆየታቸውን የገለጹት ምክትል ከንቲባው፤ ኅብረተሰቡ በትብብር ለበዓሉ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

የከተማው መስተዳድር ከሆቴል አገልግሎት በተጨማሪ ነዋሪዎችን በማቀናጀት በተለያዩ ቦታዎች ላይ አገልግሎት መስጫ ስፍራዎችን ማዘጋጀቱን አስታውቀው፤ በርካታ ሕዝብ ማስተናገድ የሚችሉ 11 ምግብና መጠጥ የሚቀርብባቸው ማዕከላት መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል።

በቢሾፍቱ ሆራ ሀርሰዴ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ታዳሚዎች ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል ያሉት አቶ ገዛኸኝ፤ ከሆቴሎችና ከመኝታ ቤቶች በተጨማሪ በድንኳኖች፣ በተለያዩ አዳራሾችና በመኖሪያ ቤቶች ጭምር አስፈላጊውን ግብዓት በማቅረብ እንግዶችን ለመቀበል የሚያስችል ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል።

የኢሬቻ በዓል በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ የገዳ ሥርዓት ማሳያ መሆኑን ጠቁመው፤ የሕዝቦችን አንድነትና ትስስር ለዓለም ለማሳየት የሚረዳ በዓል በመሆኑ ባህሉንና እሴቱን በጠበቀ መልኩ ሊከበር ይገባል ብለዋል።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል መስከረም 26 ቀን በሆራ ፊንፊኔ እንዲሁም መስከረም 27 ቀን 2016 ዓ.ም በቢሾፍቱ ሆራ ሀርሰዴ በርካታ የበዓሉ ታዳሚዎች በተገኙበት የሚከበር መሆኑን የኦሮሞ አባገዳዎች ኅብረት ማስታወቁ የሚታወስ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሀገራዊ አቅሞቻችንን በሚገባ ማወቅ ለኢትዮጵያ ብልጽግና መሠረት ነው!

የአንድ ሀገርና ሕዝብ የወደፊት ዕጣ ፈንታ በዋናነት የሚወሰነው ያ ሕዝብ /ሀገር ስላለው ሀብትና አቅም ተገቢው እውቀት ሲኖረውና እና ይህንን ዕውቀት ወደሚጨበጥ ተስፋ መለወጥ የሚያስችል መነቃቃት መፍጠር ሲችል እንደሆነ ይታመናል። አሁን ላይ ስለማደጋቸው ብዙ የሚነገርላቸው ሀገራትና ሕዝቦችም እውነታ ከዚህ የተለየ እንዳልሆነ የታሪክ መዛግብት ያመላክታሉ።

እነዚህ ሀገራት ዛሬ ላይ የደረሱበት የዕድገት ደረጃ ለመድረስ እንደ ሀገር ያላቸው ተፈጥሯዊ ፣ ማህበራዊና ሰብዓዊ ሀብቶቻቸውን አግባብ ባለው መንገድ ትኩረት ሰጥተው ለማየት ረጅም ርቀት ተጉዘዋል። በዚህ ሂደት ያገኟቸውን አቅሞች በማጎልበት የሀገርና የሕዝብ ተጨባጭ ተስፋ የሚሆንበትን መልካም አጋጣሚ ፈጥረዋል። ዜጎችም ያላቸውን አውቀው ባላቸው መጠን እንዲያስቡ ማድረግ የሚያስችል ሥርዓትም መፍጠር ችለዋል፡፡

አንዳንድ ሀገራት ከራሳቸውም ባለፈ ባህር ማዶ ተሻግረው የሌሎችን አቅም በማጥናት ተጠቃሚ ለመሆን የሄዱበት ሆነ እየሄዱበት ያለው መንገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸውን ተጠቃሚነት እያጎለበተላቸው ለዜጎቻቸው ከትናንት የተሻለች ዛሬን ፈጥረዋል። ነገዎቻቸውን ከዛሬ በተሻለ ተስፋ የሚጠብቁበትን ማንነትም ገንብተዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ሀገር የህልም ችግር ያለብን ሕዝቦች አይደለንም። ትናንት የትልቅ ታሪክ ባለቤት ከመሆናችን የተነሳ ከፍያሉ ህልሞችን ለማለም ብዙ ተግዳሮቶች የሚፈታተኑን አይደለንም። ከዘመን ዘመን ከትውልድ ትውልድ የሚሻገሩ ታላላቅ ሕልሞች ባለቤቶች ነንና። እያንዳንዱ ትውልድ ከትናንት ታሪኩ እየተነሳ የበለጸገች ታላቅ ሀገር የመፍጠር ራዕይ ሰንቆ የህይወት ጉዞውን ለመጓዝ ሞክሯል።

ይህም ሆኖ ግን “በየዘመኑ ትልቅ እንደሆንን ትልቅ እንሆናለን” ከሚለው ትውልዳዊ መፈክር ባለፈ እንደሀገር ወደ አሰብነው ለመድረስ ሳንችል ዘመናት ተቆጥረዋል። ካሰብነውና ካለምነው ይልቅ ያላሰብነውና ለማሰብ የሚከብደን እጣ ፈንታችን ሆኖ ብዙ ዋጋ ከፍለናል። በዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ባልተገቡ ስያሜዎች ለመጠራት ተገደናል።

ለዚህ ደግሞ በዋነኛነት እንደ ችግር የሚጠቀሰው ከራሳችን ተርፎ ለብዙዎች የሚተርፍ ተፈጥሯዊ ፣ ማኅበራዊና ሰብአዊ ሀብት ባለቤት የመሆናችንን እውነታ በአግባቡ አለማወቃችን፤ ለዚህ የሚሆን የትውልዶች መነቃቃት የሚፈጥር የአስተሳሰብ መሰረት መገንባት አለመቻላችን እንደሆነ ይታመናል። በተለይም እንደ ሀገር ይህን አእምሮ አለመፍጠራችን ከትናንት የተሻለች ሀገር እንዳንፈጥር ተግዳሮት ሆኖብናል።

ይህ ችግር ከሁሉም በላይ የተሻለች ሀገር ለመፍጠር የሚያስፈልገንን ሀገራዊ ሰላም ተጨባጭ ለማድረግ ትልቁ ፈተና ከሆነ ሰነባብቷል፤ ከዚህም ባለፈ ዜጎች ነገዎቻቸውን ባሰቡ ቁጥር ተስፋቸውን ባህር ማዶ እንዲያደርጉ ፣ በዚህም ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ እያደረጋቸው ይገኛል።

በዚህ መልኩ ወደ ፊት ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጁ ዜጎችም ቁጥር እንዲህ በቀላሉ የሚሰላ ነው ተብሎም የሚገመት አይሆንም። በቀደሙት ዘመናት እንደ ሀገር ያለንን አቅም አለመረዳታችንም ሆነ ለዚህ የሚሆን ሀገራዊ መነቃቃት አለመፍጠራችን፤ የቱንም ያህል ዋጋ ያስከፈለን ቢሆንም አሁን ላይ በችግሩ ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር ከቻልን እንደ ሀገር የሚኖሩን ነገዎች ብሩህ ስለመሆናቸው ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደሉም። የማወቃችንን ያህል መለወጣችንም የማይቀር ነው።

ከዚህ አንጻር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ይህንን እውነታ ታሳቢ አድርገው በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ሰሞኑን ያደረጓቸው ጉብኝቶች እና በጉብኝቶቹ የፈጠሩት አቅምን የማወቅ መልካም አጋጣሚ እንደሀገር ለጀመርነው የብልጽግና ጉዞ ስኬታማነት ትልቅ ጉልበት እንደሚሆን ይታመናል።

በተለይም የክልል መንግሥታት የክልሎቻቸውን አቅም በአግባቡ ማወቅ የሚያስችል ወጥነት ያለው የአሰራር ሥርዓት በመፍጠር የዜጎቻችንን ነገዎች ብሩህ ለማድረግ የተጀመረው ሀገራዊ ንቅናቄ ትርጉም ያለው ውጤት እንዲያስመዘግብ ከቢሮ ያለፈ ስምሪቶች እንደሚያስፈልግም ያሳየ ነው።

በክልሎች የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ቢሆኑ በሀገር ዕድገት ውስጥ ተጨባጭ ሚና እንዲኖራቸው፤ በየአካባቢው የሚገኙ ሀገራዊ አቅሞችን በመለየት ለዜጎች የተሻለች ሀገር ለመፍጠር ትልቅ ኃላፊነት እንዳለው ተቋም ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

ባለሀብቶቻችንም ቢሆኑ እነዚህን አቅሞች በማወቅ በራሳቸውም ሆነ ከሌሎች ሀገራት ባለሀብቶች ጋር በመተባበር ለማልማት ግንባር ቀደም መሆን ይጠበቅባቸዋል ፤ በዚህም ለራሳቸው ፣ ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው፤ ከዛም ባለፈ ለሀገርና ለመጪዎቹ ትውልዶች የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር በሚደረገው ሁለንተናዊ ርብርብ የዜግነት ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ</u>
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

<u>ዋና አዘጋጅ</u>
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

<u>አድራሻ</u>
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>
ስልክ - 011-1-26-43-39

<u>ማከፋፈያ</u> ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከውጪ ኢንቨስትመንትና ኢንቨስተሮች ጋር ሊታሰቡ የሚገባቸው ጉዳዮች


ጋሹ ሀብቴ (ዶ/ር)
Ghabte12@aol.com


የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ወደ ሀገር ውስጥ በመሳብ ሂደት እንደ ሀገር ሊገኙ የሚችሉ መልካም እድሎች የመኖራቸውን ያህል፤ በዛው ልክ ሊታሰቡ የሚገባቸው ሥጋቶች መኖራቸው መዘንጋት የለውም። ምክንያቱም የውጪ ኢንቨስተሮች በአንድ ሀገር ሲሰማሩ ከጋራ ተጠቃሚነት የኢኮኖሚ ጉዳያቸው ባሻገር፤ የራሳቸውን ትርፍ ማግኘትና ሀብታቸውን ማሳደግ፣ ጥሬ እቃን በርካሽ ማግኘት፣ ርካሽ ጉልበትን ለመጠቀም፣ ብዙ ሕዝብ ባለበት ሀገርና አካባቢ ሰፊ ገበያን ፍለጋና ዋጋ የሚያወጡ መረጃዎችን በስለላ መልክ ለማሰባሰብም ዓላማ አድርገው ነው።

ከነዚህ በተጨማሪ ደግሞ የውጪ ባለሀብትም ሆኑ መንግሥታት በሀገራቸው ለማስቀመጥ ኪራይ የሚከፍሉበትን የተትረፈረፈ ገንዘብ ወይም ሀብት ከኪራይ ክፍያ ነጻ በሆነና በተከታታይ ጥቅም በሚሰጥ መልኩ ለማዋል ሲሉ በሌሎች ሀገራት ለረጅም ጊዜ ጥቅም ሊያገኙ በሚችሉበት መልኩ ኢንቨስት ያደርጋሉ። ይህ ገንዘብ የማሸሹ ፍላጎት የሚመነጨው በበለጸጉ ሀገሮች ሀብታሞች ገንዘባቸውን ለማስቀመጥ ኪራይ ስለሚከፍሉ የሚያገኙት ወለድ ከዜሮ በታች(negative interest rate) በመሆኑ ነው።

ከዚህም ሌላ በዓለም ዙሪያ ባለው የዋጋ ግሽበት (ኢንፍሌሽን) ምክንያት የገንዘባቸው የመግዛት አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንደሚሄድ ስለሚያውቁ በኢንቨስትመንት ስም ገንዘባቸውን ወደ ውጪ በማሸሽ ኢንቨስት ያደርጋሉ። ከነዚህም በተጨማሪ ከሚደረገው ኢንቬትመንት ጋር በተያያዘ የውጪ ኢንቨስተሮች ለዜጎቻቸው ለሚፈጥሩት የሥራ እድልም ከፍተኛ ቦታ ይሰጡታል።

እነዚህንና ሌሎች አላማዎችንና ፍላጎቶችን መሰረት ባደረገ መልኩ የውጪ ሀገር ኢንቨስተሮች በሌላ ሀገር ገንዘባቸውን ኢንቨስት ያደርጋሉ። እናም የውጪ ኢንቨስተሮች ሌላውን የመርዳት ፍላጎታቸው ለሽፋን ካልሆነ በስተቀር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። ስለሆነም የውጪ ኢንቨስትመንት ጥቂት ጥቅሞች ሊኖሩት ቢችሉም፤ በአብዛኛው በርካታ ጉዳቶች እንዳለው በሰፊው ይታመናል።

ለምሳሌ፣ በ1883 ስምንት ሀገሮች ባደረጉት የአፍሪካን እንከፋፈል ስሌትና ስምምነት በአፍሪካ አህጉር ሰፊ ሰብዓዊ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ የተፈጥሮ ሀብት ምዝበራም ፈጽመዋል፡፡ እነዚህ የዛን ጊዜው ቅኝ ገዢ ሀገራት ታዲያ ዛሬም በአብዛኛው በባለሀብቶቻቸው አማካይነት ወደ አፍሪካ ሀገሮች ገንዘባቸውን የሚልኩ ሆነዋል።ይህንን አይነት ድርጊት በጥቅሉ በርካታ ቁጥራቸው የማይናቅ ባለሙያዎችና አዋቂዎች በጥንቃቄ ያልተወሰነ ከሆነ፤ ቀደም ሲል በጦርነት የነበረውን የቅኝ አገዛዝና ሀብት የመዝረፍ ድርጊት የሚተካ ዘመናዊ የሆነ የኢኮኖሚ ቅኝ አገዛዝ (Economic Colonialism) ነው ይሉታል።

እናም ይህንን ብሂል በሚያንጸባርቅ ወይም በሚመስል አግባብ ድርጊቶች በትርፍ መልክ አንዳንዴ ማቆሚያ በሌለው ወይም የረጅም ጊዜ ውስብስብ ውለታን መሰረት በማድረግ ሀገሮች የሚወጣው የውጪ ምንዛሬና የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች እጅግ በጣም የከፉ ናቸው። ለምሳሌ ያህል፣ በዚህ አይነቱ ውል ውስጥ ሀገራችን በ1897 ዓ.ም በመግባት ከአዲስ አበባ ጂቡቲ በተዘረጋው የባቡር ሃዲድ በጦርነት ሊያገኙት ያልቻሉትን የሀገራችንን ሃብት በእንቨስትመንት ስም የፈረንሳይ መንግሥት ሚሲዮናዊያን ከሆኑ ከእነዚያ ሁለት ፈረንሳዊያን ጋር በተደረገ ውል ለመቶ ዓመታት ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ ሀገራችን እንድትከፍል አድርገዋታል።

በመሆኑም ከሀገር በቀል ኢንቨስተሮች ጋር ሲነጻጸር የውጪ ኢንቨስተሮች የተገኘውን ትርፍ መልሰው እዚሁ ሀገር ውስጥ እናጥፋ ወይም ኢንቨስት እናድርግ ስለማይሉ፤ የተገኘውን የምርት ውጤትና ጥቅም (Newly Created Wealth) በተለያየ መልኩ ማለትም በትርፍ፣በዲቪዴንድ፣በሮያሊቲ፣ በደመወዝና በሌላ መልኩ በውጪ ምንዛሬ ከሀገር እንዲወጣ ያደርጋሉ። ዋናው አላማቸው ትርፍ ማግኘት ስልሆነም ትርፋቸውን እንደ የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች መልሰው በሀገር ውስጥ ተከታታይና ተደጋጋፊ በሆኑ ሥራዎች ላይ አያውሉም። ስለሆነም የተመረተው ወይም በሀገር ውስጥ ጉልበትና ጥሬ እቃ የተፈጠረው ሀብት ተከታታይ እድገት (Extended Reproduction) ማስገኘት አይችልም ማለት ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ እጅግ በጣም አስፈላጊ ሳይሆን የሚመጣ የውጪ ኢንቨስትመንት ሀገር ቤት ያሉትን ተመሳሳይና እያደጉ ያሉ ኢንዱስትሪዎችን ወይም ተመሳሳይ ሥራ የሚሰሩትን ሌሎች ድርጅቶችን በተለያየ መልኩ የሚሰጡትን አገልግሎቶች በመሻማት የማቀጨጭ ወይም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ደግሞ ከነአካቴው የመተካትና ከገበያ የማውጣት ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ። እንደዚሁ ደግሞ ነባር፣ ተመሳሳይና ተቀራራቢ ድርጅቶች ላይ በሚፈጥሩት ጫና ሀገር በቀልና ባህላዊ ምርቶችን ቀስ በቀስ ከገበያ ሊያወጣቸው ይችላሉ።

የውጪ ኢንቨስተሮች ዋነኛ አላማቸው ትርፍ በመሆኑ የዜጎችን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ሥራ ሊሠቸሩ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል፣ ለዜጎች የጡረታ ጥቅም አለማስከበር እንደ ትልቅ ጉዳት ሊቆጠር ይገባዋል። በዜጎች ላይ ብቻ ሳይሆን ትርፍን ከማሳደግ ዋነኛ አላማቸው የተነሳ በአካባቢ የአየር ሁኔታና የተፈጥሮ ሀብት ላይ ጥፋትና ብክለት ሊፈጥሩ ይችላሉ።

በተለይ የኢንዱስትሪ ምርት አምራች የሆኑ የውጪ ኢንቨስተሮች ምርት በሚመረትበት ጊዜ የሚወጣው ፍሳሽም ሆነ ጭስ ወይም ሌላ ነገር በአየር ጠባይና የአካባቢ ብክለት በቀላሉ የሚያስከትሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ አስፈላጊ ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ በአካባቢ ነዋሪዎች፣ እንስሳትና የተፈጥሮ ሀብት ላይ ከፍተኛ ችግር ማስከተል እንደሚችሉ በማወቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

ሌላው እጅግ የከፋ የሚሆነው፣ የውጪ ኢንቨስተሮች ችግር የውጪ ምንዛሪ ላይ ጫና ሊፈጥሩና እጅግ አስፈላጊ ለሆኑ ግብአቶች መግዣ የሚውል የውጪ ምንዛሪ ሚዛን ሊያዛቡ መቻላቸው ነው። ለኢትዮጵያ የውጪ ምንዛሪ ማለት ጠንካራና ዘመናዊ የሀገር መከላከያ ማለት ነው። አስፈላጊና በቂ መድኃኒቶች፣ ነዳጅ፣ ማዳበሪያ፣ የሕክምና መሳሪያዎችና ለትምህርት ዘርፍ የሚውሉ በርካታ ግብአቶች ማለት ነው። በርካታ ማሽነሪዎችንና የእርሻ መሳሪያዎች ማቅረብ ማለት ነው፡፡ ተሽከርካሪዎችንና የመለዋወጫ እቃዎቻቸውን ማቅረብ ማለት ነው፡፡ አልባሳትንና የሕንጻ ግብአቶችን፣ የኤሌክትሮኒክስና የቤት ውስጥ ፍጆታ እቃዎችንና ሌሎች በርካታ በውጪ ገንዘብ የሚገዙ እቃዎችን ለሕዝብ ማቅረብ መቻል ማለት ነው።

ከእነዚህ በተጨማሪ ሀገራችን የውጪ ምንዛሪ ለበርካታ ጉዳዮች አንገብጋቢ በሆነ ደረጃ ትፈልጋለች። ስለሆነም ከውጪ ኢንቨስተሮች ጋር የሚደረገው ስምምነት በክፍያ በኩል አስገዳጅ፣ የጊዜ ገደብና ቅጣት ያለው ከሆነ ሊሰጠው ከሚገባ ቅድሚያ የተነሳ በሀገራችን የውጪ ምንዛሪ ፍላጎት ላይ ከፍተኛ ጫናን ይፈጥራል። ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች አስፈላጊ ግዢዎች ላይ ከፍተኛ ጫናን ይፈጥራል። ስለሆነም ትርፋቸውን በውጪ ምንዛሪ የሚወስዱ ነገር ግን ወደ ውጪ የሚሸጥ ምርት የማያመርቱ የውጪ ድርጅቶችን ወደሀገር በመጋበዝ ጉዳይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የውጪ ኢንቨስተሮች ሲመጡ ሌሎች የራሳቸው ዜጎች

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ከውጪ ኢንቨስትመንትና...

እዚህ የሚሠራውን ሥራ የሚሠሩት ወይም የሚያስተባብሩት በውጪ በሀገራቸው ሆነው ነው። በውጪ ምንዛሪ የሚከፈሉትም እዚህ ከሚሰራው ሥራ ትርፍ ነው። ኢንቨስት አድራጊው ድርጅት ወደ ውጪ የሚሸጥ ምርት የማያመርት ከሆነ ይህንንም ክፍያ ከፋዮች የእኛው የቡና ገበሬዎችና ሌሎች ወደ ውጪ የሚሸጡ ምርት አምራቾች ናቸው ማለት ነው። ስለሆነም የነዚህንም አይነት ኢንቨስተሮች የውጪ ገበያ ፈልገው ምርታቸውን በመሸጥ የውጪ ምንዛሬ የሚያስገኙ ስለመሆናቸው ከስምምነቱ በፊት እርግጠኛ መሆን ይገባናል።

በነዚህ አይነት ሊታዩ በሚችሉ ውሳኔዎች በሀገራችን በርካታ ፋብሪካዎች ለውጭ ሀገር ኢንቨስተሮች ተሸጠዋል። ይሄ ለአጭር ጊዜ ጥቅም ሲባል፣ የመሐከለኛና የረጅም ጊዜ እዳና ግዳጅ ሳይታሰብ ወይም በደላላዎች ጫና ሊሆን ቢችልም፤ በዚህ ግን ሀገራችን በርካታ ግዴታዎች ውስጥ የገባች መሆኑ ይታወቃል።

ለምሳሌ ያህል፣ ለውጪ ኢንቨስተሮች በርካታ የቢራ ፋብሪካዎች ተሸጠዋል። ከተሸጡት የቢራ ፋብሪካዎች መሃከል የበደሌ ቢራ ፋብሪካ ከ12 ዓመታት ገደማ በፊት የተሸጠው በ310 ሚሊዮን ዶላር ነው። ለምን ለውጪ ኢንቨስተር መሸጥ አስፈለገ? ከሽያጩ በኋላ ለገዥው ድርጅት በሀገር ውስጥ ለሚሸጠው ምርት በተከታታይ በውጪ ምንዛሪ የሚከፈል ክፍያ ስላለ በሽያጩ ገንዘብ ሌላ ምን የውጪ ምንዛሬ የሚያስገኝ ኢንቨስትመንት ተደረገበት? ባለፉት 12 ዓመታት በውጪ ምንዛሪ ለገዢው የተከፈለው ገንዘብ ከተገዛበት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል ነው ? ወደ ውጭ ሀገር የሚሸጥ ምርት ያመርታሉ ወይ? ከሌሎች ከፍ ባለ ጠርሙስ የሚሸጡት ቢራ በሌሎች አምራቾች ላይ ምን ተጽእኖ ይፈጥራል? የዚህ አይነቱ ምሳሌ ምን ያስተምረናል? የሚሉት ጥያቄዎችና ሌሎች ጉዳዮች በተለያየ መልኩ መመርመርና ለሌሎች ውሳኔዎች መሰረትና መማሪያ መደረግ አለባቸው እላለሁ።

በዚህ ረገድ የውጪ ኢንቨስትሮችን ሳያስገባ የኢትዮጵያ መንግሥት ካደረጋቸውና እያደረገ ካላቸው ሥራዎች ውስጥ የኢትዮጵያ አየር መንገድና የዓባይ ግድብ እራስን በራስ የመቻል ውሳኔዎች ለበርካታ የሀገራችን ድርጅቶች የይቻላል አራአያና መማሪያ መሆን እንዳለባቸው መታወቅ ይገባዋል። ስለእነዚህ ሁለትና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች፣ ሌሎች ድርጅቶች ሁሉ እንዲሰሙ ድምጻችንን ከፍ አድርገን መናገር ይኖርብናል።

እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ በዱቤ ወይም ተብድሮ መግዛት እያለ ለብዙ ሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችንና ብዙ የውጪ ምንዛሪ የማያስገኙ ድርጅቶችን አገልግሎቶች ለውጪ ኢንቨስተርስ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አሳልፎ መሸጥ ከራሳችን ጠንካራ ድርጅቶች ለመማር ካለመቻል ወይም ለመማር ፈቃደኛ ካለመሆን ወይም በደላላዎች ግፊት የተደረጉ ውሳኔዎች ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ይቻላል።

ለምሳሌ ያህል አቶ ግርማ ዋቄ፣ አቶ ተወልደ እና ሌሎችም በተለያየ መልኩ የውጪ ኢንቨስተሮች ሳያስገቡ አውሮፕላኖች ከቦይንግ ከኤርባስ በዱቤም ይሁን በብድር ገዝተው እጅግ በጣም የተዋጣለት ሥራ የሚሰሩና የመሩ መሆኑ እየታወቀ፤ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን 40 በመቶ ወይም የ28 ሚሊዮን ደንበኞቹ መጠቀሚያ የሆነውን አገልግሎቱን ለምን ለውጪ ኢንቨስተሮች እንደሸጠ ስንጠይቅ በርካታ መልሶች ሊኖሩት ቢችልም፤ የመጀመሪያው መልስ ግን ከኢትዮጵያ አየር መንገድ መማር አለመቻሉን ወይም ለመማር አለመፈለጉን እንገነዘባለን፡፡

**በተለይ የኢንዱስትሪ ምርት አምራች የሆኑ የውጪ ኢንቨስተሮች ምርት በሚመረትበት ጊዜ የሚወጣው ፍሳሽም ሆነ ጭስ ወይም ሌላ ነገር በአየር ጠባይና የአካባቢ ብክለት በቀላሉ የሚያስከትሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ አስፈላጊ ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ በአካባቢ ነዋሪዎች፣ እንስሳትና የተፈጥሮ ሀብት ላይ ከፍተኛ ችግር ማስከተል እንደሚችሉ በማወቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት**

ይህንንም የምለው በዓለም በቻይና፣ በአሜሪካ፣ በደቡብ ኮሪያ በእንግሊዝና በሌሎች ሀገሮች እጅግ በጣም ዘመናዊ ተወዳዳሪና ተፎካካሪ የሆኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ታወሮችና መሳሪያዎች በሰፊው የሚያመረቱ፣ የሚሸጡና የሚከራዩ መሆናቸው የሚታወቅ ስለሆነና የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሥራ አፈጻጸም ለኢትዮጵያ ቴሌኮምም ሊሰራ እንድሚችል ስለማምን ነው። ምክንያቱም ከነዚህ ወደ 28 ሚሊዮን ከሚሆኑ ደንበኞች በየወሩ የሚሰበሰበው በአብዛኛው በብር ሲሆን፤ ለውጪ ኢንቨስተሮች የሚከፈለው ግን በውጪ ምንዛሪ ነው።

ይህ በወራዊ፣ በመንፈቃዊና ዓመታዊ ተሰለቶ ወደ ውጪ ምንዛሪ ከተለወጠ በኋላ የኢትዮጵያ ቴሌኮም በአገልግሎቱ ከሚያገኘው የውጪ ምንዛሪ ገቢ ጋር ማወዳደሩ ለወደፊት ለሌሎች ሃገራዊ ዉሳኔዎች ጥቅም ያለዉ ይመስለኛል። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ይህ ዉል ለእኔ ከላይ እንደጠቀስኩት እንደ የ1897 ከአዲስ አበባ ጂቡቲ የባቡር መንገድ ግንባታ ዉልና ስምምነት መጪዉን ትዉልድ ጭምር ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል ይመስልኛል። ኢትዮጵያ ለኬንያ የምትሸጠዉ የመብራት ሃይል በአብዛኛው የማምረቻ ምርት (Producer Good) ሲሆን፤ እየገዛን ያለነው ግን በአብዛኛው የፍጆታ ምርት (Consumer Good) ነዉ። በመሆኑም በርካታ የሀገራችን ድርጅቶች ከዚህ አይነቱ ዉሳኔ መማርና መራቅ አለባቸዉ እላለሁ።

ሌላው ለኢትዮጵያ እጅግ አሳሳቢ የሚሆነው በባንኮች ዙሪያ ያለው የውጪ ባንኮች የመጋበዙ ፍላጎት፣ ጥረትና ሃሳብ ነው። የባንኮች እንቅስቃሴና ሥራ ለሀገር እድገት እጅግ በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ነው። ለፋብሪካ መስፋፋት፣ ለእርሻ እድገት፣ ለንግድ እድገትና መጠናከር፣ ለግንባታ ሥራዎች መስፋፋትና እድገት፣ ፈጣን የሆነ የገንዘብ ዝውውር ለሚሹና ለሁሉም የምጣኔ/ኢኮኖሚ ዘርፎች ማደግ ብዙ የውጪ ምንዛሪ ዋጋ የማያስከፍሉ የሀገር በቀል ባንኮች ብዛትና ስርጭት እጅግ በጣም ወሳኝና አስፈላጊ ነው።

ስለሆነም በታከታታይ በቁጥርም ሆነ በአገልግሎት አይነት የሚያድጉ ባንኮች በብዛት ያስፈልጉናል። እነዚህም ሀገር በቀል ባንኮች በሥራቸውና በእድገታቸው ላይ ጫናና አላስፈላጊ ከሆነ የውጪ ተፎካካሪዎች ነጻ በመሆን ከሕዝባችን እድገት ጋር ማደግ አለባቸው። ከንግድ ባንክና ከልማት ባንክ በስተቀር የባንኮቻችን እድሜ 30 ዓመታት ገደማና ከዚያ በታች በመሆኑ ገና ታዳጊዎች ናቸው።

ስለሆነም እጅግ ብዙ እድሜና ብዙ ካፒታል ባካበቱ ዋናው ዓላማቸው ትርፍ፣ ለዜጎቻቸው የሥራ እድል ፈጠራና ወለድ አልባ የሆነ ገንዘባቸውን ማሸሻ ከሆኑ ባንኮች ጫናና አግባብ የሌለው ፉክክር ነጻ መሆን አለባቸው። ስለሆነም የውጪ ባንኮች ወደ ሀገራችን መጋበዝ በጥንቃቄና አስፈላጊነታቸውና የሥራ ድርሻቸውን በአግባቡ በበርካታ ባለሙያዎች የተለየ ፣ የተደገፈና የተረጋገጠ ምክንያታዊ መሆን ያስፈልገዋል። አለበለዚያ እጅግ አስከፊና ለትውልድ የሚተላለፍ ችግርና እዳ ውስጥ ልንገባ እንችላለን።

በዚህ ረገድና አቅጣጫ የሌሎችንም ሀገሮች ልምድ መመርመሩና ማየቱ እጅግ አድርጎ ይጠቅማል። ለምሳሌ ያህል፣ ናይጄሪያ ከፍተኛ የውጪ ንግድና የኢኮኖሚ ትስስር ከምእራባውያን ጋር ያላት መሆኑ ቢታወቅም 94 በመቶ የሚሆነው የባንክ አገልግሎታቸው ሀገር በቀል ለሆኑ ባንኮች ብቻ የተፈቀደና የተሰጠ ነው። ሌላው፣ በእስራኤል ያለው የውጪ ባንኮች ፖሊሲም ከዚሁ ጋር የሚመሳሰልና የሚቀራረብ ነው። በእስራኤል ሀገር ገና ከጅምሩ ማሳደግ የሞከሩት የራሳቸውን ባንኮች በመሆኑ ዛሬ 95 በመቶ የሚሆነው የባንክ አገልግሎት የሚሰጠው ሀገር በቀል ለሆኑ ባንኮች ብቻ ነው።

የእነዚህ ሁለት ሃገሮች በራስ መተማመንና ለራሳቸዉ በሚሰጡት ብሄራዊ ክብር (National Pride) ሀገሮቻቸው በውጪ ባንኮች እንዳይወረሩ በማድረጋቸው በበርካታ የዓለም የምጣኔ ሀብት ሙያተኞች ከፍተኛ ሙገሳ እንዲያገኙ ያደረጋቸው መሆኑ ይታወቃል። ሌላው በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችለው የአሜሪካ፣ የካናዳ እና የእንግሊዝ ነው። እነዚህ ሶስት ሀገሮች እጅግ በጣም የጠበቀ በርካታ የምጣኔና የፖለቲካ ትስስር ቢኖራቸውም፤ አንድም የአሜሪካ ባንክ በካናዳ ወይም የካናዳ ባንክ በአሜሪካ (ኒዮርክ ከተማ ውስጥ ካሉ ጥቂት ቅርንጫፎች በስተቀር) በሌሎች ከተሞች ቅርንጫፍ ከፍተው አይታዩም ወይም አይሰሩም። እንደዚሁ የአሜሪካ ባንኮች በእንግሊዝና የእንግሊዝ ባንኮች በአሜሪካ ከተሞች አይታዩም። ከነዚህ ሁኔታዎች ብዙ መማር የምንችል ይመስለኛል።

ከዚህ በተቃራኒ በርካታ የውጪ ባንኮች ወደ ሀገራቸው በመጋበዝ ከመበዝበዝ መውጣት ያቃታቸው በርካታ ሀገሮች መኖራቸውን አውቀን፤ በዚህ የውጪ ባንኮች ወደ ሀገር መግባት ግብግ ዙሪያ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ጉዳይ ነው። እናም ውሳኔው የፖለቲካ ወይም የሎቢስቶች ጉዳይ ሳይሆን የባለሙያዎች ውሳኔ መሆን አለበት እላለሁ።


በአጠቃላይ የውጪ ኢንቨስትመንትና ኢንቨስተሮች ግብግ ውሳኔ ከጥቅሙ ባሻገር ያሉ ጉዳዮችን በጥንቃቄ መመልከት፤ አስፈላጊነቱ ከተረጋገጠና ሌሎች አማራጮች አለመኖራቸው በባለሙያዎች ተመርምሮ፣ ምስክርነት ከተሰጠበት በኋላ የሚወሰን ካልሆነ በስተቀር ቅጥ ያጣ የረጅም ጊዜ እዳ ውስጥ ለመግባት ስምምነት እንደተደረገ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባዋል። ሀገራችን ከአቅማችንና እጅግ ወሳኝ ከሆነ ፍላጎታችን ውጪ በሆነ መልኩ የውጪ ኢንቨስተር ስትጋብዝ ጉዳቱ ከሚገኘው ጥቅም በጣም የበዛ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ጥቅምና ጉዳቱ በሙያተኞች ስሌት በአሃዝ በተደገፈ መልኩ መመዘንና ሌሎች አማራጮች መኖር አለመኖራቸው መረጋገጥ አለበት። ከዚህም በተጨማሪ የዚህ አይነቱ ውሳኔ ከደላላዎች ወይም ከሎቢስቶች ነጻ በሆነ መልኩና በፖለቲከኞች ውሳኔ ብቻ ሳይሆን፤ ከላይ እንደጠቀስኩት በሙያተኞች ነጻ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በጥንቃቄ ተገምግሞና ተመርምሮ የሚወሰን መሆን አለበት። ይህ ካልተደረገና ውሳኔዎች በችኮላና ጥንቃቄ ባልተሞላበት መልኩ በጥቂት ግለሰቦች ፍላጎት ከተወሰኑ ከላይ እንደጠቀስኩት ሀገራችን ለትውልድ የሚተላለፍ እዳና ለረጅም ጊዜ የውጪ ምንዛሪ የሚያስከፍለን አስገዳጅ ውል ውስጥ በቀላሉ ልትገባ ትችላለች እላለሁ።

# ወቅታዊ

# “ኢትዮጵያ በሕዝቦቿ እጅ ውስጥ ናት”

-ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር


ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

አስቴር ኤልያስ

**ኢትዮጵያውያን ከመቼውም ጊዜ በላይ የሚናፍቁት ጉዳይ ቢኖር ሰላምን ነው፡፡ ምንም እንኳ የኑሮ ውድነቱ ከጊዜ ወደጊዜ እያሻቀበ ቢመጣም ከሰላም መስፈን እንደማይበልጥም አሳምረው ያውቃሉ፡፡ ታድያ ለዚህ ሰላም መስፈን ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ድርሻ መኖሩን እምብዛም ትኩረት ሲሰጥ አይስተዋልም፡፡ በደጅ ባለውና በተዘረጋው የሰላም አጀንዳ ተዋናይ ለመሆን መዘጋጀት ብልህነት ነው፡፡ ይህ የሰላም አጀንዳ ደግሞ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ይዞ የቀረበው ታላቅ ጉዳይ ነው፡። ከዚሁ ጉዳይ ጋር ተያይዞ አዲስ ዘመን የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር እና እንዲሁም የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ከሆኑት ከፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ጋር ቆይታ አድርጓል፤መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለው ችግር ከየትኛው የተሳሳተ ትርክት የሚመነጭ ነው ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር አንድ አይነት ብቻ አይደለም።ችግሮቻችን አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት... እየተባሉ የሚቆጠሩ ናቸው። አንዳንዱ ችግር በአንዳንድ ወቅት ገንፍሎ የሚወጣ ነው።እሱንም ችግር እንለዋለን። ቀጥሎ ደግሞ ፈረንጆች (Moving Target) ተንቀሳቃሽ ኢላማ የሚሉት የቸገረ አይነት ሁኔታ ደግሞ ነው።ተንቀሳቃሽ ኢላማ መምታት አስቸጋሪ ነው።ተንቀሳቃሹን ነገር አነጣጥሬዋለሁ ብለን ልንመታው ስንል ወዲህ ወዲያ ስለሚንቀሳቀስ ዒላማችን ውስጥ ለማስገባት ያስቸግራል። ልክ እንደዛው ሁሉ የኢትዮጵያ ችግሮች እንደተንቀሳቃሽ ኢላማ ናቸው። አነጣጥሮ ለመምታት ተንቀሳቃሽም በመሆናቸው በጣም ከባድ ነው።ስለዚህ በዚህኛው ችግር ላይ አተኩር እስኪ እስካልተባልኩ ድረስ ለጠየቅሽኝ ጥያቄ ምላሼ የሚሆነው ጠቅለል ያለ ነው፡፡

ያም ሆኖ ግን እኛ ኢትዮጵያውያንን ለየት የሚያደርገን በችግሮቻችን ውስጥ ሆነን ማለፍ እንችልበታለን።አሁንም ቢሆን ስለምንችል በችግር ውስጥ እያለፍን ነው።የእኛ አይነት ችግር የደረሰበት ሌላ ሀገር ቢሆን እስካሁን ተበታትኗል፡፡

ደርግ ወድቆ ኢህአዴግ የገባ ጊዜ በሽግግር መንግስት ወቅት በቻርተር ኮንፍረንሱ ላይ ብዙዎችን የማግኘት እድል ነበረኝ።አንድ በጣም ያስገረመኝ የኢጋዴን ነጻ አውጪ ድርጅት የሚባለውን የሚመሩ በጉባኤው ውስጥ የነበሩ ሰው የተናገሩት ነገር ነው። ሰውዬው በአጼ ኃይለስላሴም ዘመን የነበሩ ናቸው። በወቅቱ በነበረው የአስተዳደር ሥርዓት ውስጥም የሰሩ እንደመሆናቸው ብዙ ነገር የሚያውቁ ናቸው።‹‹ልጅ በየነ፣ አሁን ሱማሊያም ተቸገረ፤ እያንዳንዱ የጎሳ መሪ ሀገሪቱን የምመራው እኔ ነኝ እያለ ነው፤ ኢትዮጵያም ተቸገረች።መንግሥትም ወድቋል።ሱማሊያም ፈረሰች፤ ኢትዮጵያ ግን ያልፈረሰችው ለምንድን ነው? ሲሉ ጠይቀውኝ እራሳቸው መልሰው፤ ኢትዮጵያ ግን መንግሥት እንኳ ሳይኖር ሕዝቡ ሰላም ነው፤ በየጎሳ መሪው ተከፋፍሎ ሀገር አልተበታተነም። ኢትዮጵያ ቋሚ መንግሥት ለዘመናት ያለባት ሀገር ናት።ሕዝቡ መንግሥታዊ አስተዳደርን ያውቃል።ስለዚህ ስልጣን ላይ ያለው ቢፈልግ አንዱ ሌላውን ይገለብጣል፤ ሌላኛው ደግሞ ሌላውን ይገድላል እንጂ ሀገሪቱን ግን ሕዝቡ ያስቀጥላል አሉኝ።

በእርግጥም ባለው ባህላዊ እሴት በመታገዝም ኢትዮጵያ ሳትበታተን እንድትቆይ ያደረገው ሕዝቡ ነው። ሁሉም እንደየመልካም እሴቱ አካባቢውን በመጠበቁ ነው። በየድንበሩም ያለ እንዲሁ ሀገሩን በንቃት ጠብቆ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ የዚህ የትጉህ ሕዝብ ሀገር ናት፤ ችግሮች ይመጣሉ፤ ይሄዳሉ።የሚራኮቱት ገዥዎቹ ናቸው። በመሆኑም ይህንን ለይተን ካጤንን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያጋጥሙን ችግሮች ጨርሶ ተስፋ ሊያስቆርጡን አይችሉም።ኢትዮጵያ በሕዝቦቿ እጅ ውስጥ ናት።

አስቀድሜ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ችግሮች ብዙ ናቸው፤ በአሁኑ ጊዜ ሀገሪቷን መረጋጋት የሚያሳጡ እንቅስቃሴዎች በየቦታው አሉ፤ በእርግጥ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም። ድሮም የሚከሰት ነው።ይሁንና ሀገር እስከመበተን የሚያደርሱ አይሆኑም፤ ራሳቸው ይከስማሉ።በእርግጥ ነገሮች በተጋጋሉበት አካባቢ ችግር መኖሩ አይቀሬ ነው። የቀረው ደግሞ የሁልጊዜ ሂደቱን ይቀጥላል። የዚህች ሀገር ባለቤት ሕዝቡ ነው የሚል መንፈስ ስላለ ኢትዮጵያ ልትበታተን አትችልም፡፡

አንዳንዶቹ እዚህም እዚያም የሚነሱ ችግሮችን በማየት ብቻ በቃ ኢትዮጵያ ትበተናለች ይላል።የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊበትናት ከሚያስበው አካል በላይ ግንዛቤ ያለው ስለሆነ ይህ አባባል እኔን ብዙ አያሳስበኝም። መንግሥት እንኳ ባይኖር ባለው መልካም እሴት እየተመራ የሚኖር ሕዝብ ነው።ጎረቤታችን ሱማሊያ ስትበታተን ኢትዮጵያ ምን ሆነች? ምንም።

ስለዚህ አሁን እየሆነ ያለው ነገር በእኔ እምነት ዘላቂ ችግር ሳይሆን ጊዜያዊ ነው። ትልቁ ችግር በዚህ መንፈስ ተነሳስተው ‘እኛም ይሳካልናል’ የሚል ምኞት ያላቸው የሚመስሉ እዚህም እዚያም ጦርነት እያጫሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላም ወጥቶ እንዳይገባ የእንቅስቃሴ አድማሱን እያጠበቡ መምጣታቸው ነው።

ለችግሩ መንስኤ የሆነው ትርክት የቱ ነው ወዳልሽው ስመጣ ሁሉም የጎበዝ አለቃ ለመሆን መሯሯጡ ነው። በኦሮሚያ ውስጥ ያሉ ጎረምሶችም ያው የጎበዝ አለቆች ናቸው፤ በተመሳሳይ አማራ ክልልም ያሉት እንደዛው የጎበዝ አለቆች ናቸው። እነዚህን ሕዝቡ በትዕግስት የሚያስተምርበት ሁኔታ ቢኖር ጥሩ ነው። የሀገሪቱ መከላከያ ደግሞ ድጋፍ እየሰጠ ቢንቀሳቀስ ሰላሙ ይመጣል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡ ይህ ከሆነ መፍትሔ ይመጣል የሚል እምነት አለኝ።

ሕጋዊ መብት ያለው በዴሞክራሲ የሚያምነው አካል ነው። ዴሞክራሲያ ሒደት ደግሞ የሕዝብ ይሁንታን ያገኘ አካል ሲሆን፣ ይኸው አካል አገሪቷን ይምራ።እንዲህ ማለት ደግሞ የተደራጁና ዴሞክራሲያዊ የሆኑ አካላት ተፎካክረ ሕዝብን ማወክ ሳይጠበቅባቸው ተወዳድረው ይሁንታን ካገኙ አገር ማስተዳደር ይችላሉ። የሚይዙት ጥያቄ በአንድ ቀን እንደማይፈታ ሁሉ እነርሱም ወደስልጣን ማማ መጥተው አገር ማስተዳደር ከፈለጉ ሒደቱን ጠብቀውና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተወዳድረው ሊሆን ይገባል። ሁላችም በሰላማዊ አግባብ ጥያቄ የምንፈታበት ልቦና ቢሰጠን መልካም ነው፤ የብዙዎቹ የጸጥታ መደፍረስ ምክንያቱ የስልጣን ፍላጎት ነው።

ሌላው የከፋው ነገር በየቦታው አትንኩኝ ባይነትና እልሸኝነት መኖሩ ነው። እንዲያ ከሆነ ደግሞ ማን ለማን በቀላሉ ይበገራል የሚለው መጤን ያለበት ነው። ምክንያቱም ያለውን ችግር ለመፍታት በሚደረገው ሒደት አልንበረከክም የሚለው ነገር ትልቅ ፈተና ነው። ከዚህ የተነሳ የግጭቶቹ መንስኤ ይህና ያኛው ነው ብለን የምንናገረው ሳይሆን በርከት ያለ ነው ብሎ መናገሩ ይሻላል። ለምሳሌ አንዱ ዘንድ የወሰን ጉዳይ ሊሆን ይችላል፤ ያልተፈቱ ጥያቄዎች አሉ።እነዚያን ለመፍታት ግን መደማመጥ ያስፈልጋል።ማንም ቢሆን መሬቱን ተሸክሞ የሚጓዝ አይኖርም፤ መሬቱ ይኖራል፤ ሰዎች ደግሞ እያለፉ ትውልድ ይተካል።ስለዚህ ሁኔታዎችን አስፍቶ ማየቱ የተሻለ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ለዘመናት የነበሩ ችግሮች ሳይፈቱ ዛሬ ላይ ደርሰዋል።ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ያመለጡ መልካም አጋጣሚዎች የሚባሉ ነገሮች አሉ። አንድ የኢትዮጵያ ወዳጅና የኢትዮጵያ ታሪክ አዋቂ ኢትዮጵያን ያመለጡ ሰባት ያህል መልካም አጋጣሚዎች ነበሩ ብለው ያስቀመጧቸው አሉ። እርሳቸው በሙያቸው የማኅበረሰብ አጥኚ (ሶሲዮሎጂስት) ናቸው።ኢትዮጵያዊ አይደሉም፤ ነገር ግን ኢትዮጵያ መጥተው አርሶ አደሩ መሃል ኖረው ታሪክ ሲያጠኑ ነበር። እኚህ ምሁር ኢትዮጵያን በደንብ የሚያውቁ ናቸው ከሚባሉ ዓለም አቀፍ ምሁር መካከል አንዱ ነበሩ።

እኚህ ባለሙያ ኢትዮጵያ ያመለጣት መልካም አጋጣሚ ብለው ካስቀመጧቸው ጥቂቱ ለምሳሌ የአጼ ኃይለስላሴ ሥርዓት በሌላ ሲተካ የደርግ ጎረምሳ መኮንኖች የፈጠሩት ችግር ከመኖሩ አስቀድሞ ደርግ ሲያደርግ የነበረው አካሔድ ጤነኛ ነበር። ምክንያቱም ደርግ በወቅቱ ሲንቀሳቀስ የነበረው ‹‹ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም›› በሚል መርህ ነበር። በሂደት ግን መርዝ የበላ እንስሳ ይመስል መክለፍለፍ ጀመረ። ግድያው፣ ማሰቃየቱና ሌላው ሌላው መንጸባረቅ መጀመሩ የሚታወስ ነው። በዚያን ጊዜ ሰላማዊ ሽግግር ተብሎ የተጀመረው ነገር ቢኖርም በወቅቱ ንጉሱን እጅ በመንሳት የተጀመረው ብልጠት እያደር ከረር እያለ መምጣቱ አይዘነጋም።በሒደትም "ጠቅላይ ሚኒስትር ይቀየር እስኪ" በሚልም ጥያቄ ቀረበ። ለውጡ ሲመጣ እኔም በወቅቱ ትምህርቴን አጠናቅቄ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተቀጠርኩበት ጊዜ ነበር። እኛም በወቅቱ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አሁኑኑ ካልሆነ ብለን ሀገሩን አቀጣጠልነው።በዚህ ጊዜ ደርግም ደነገጠ።

በወቅቱ ሁኔታው ተረጋግቶ ቢሆን ኖሮ በሰላማዊ መንገድ ወደሽግግሩ ይመጣ ነበር። ነገር ግን እሱ ደፈረሰ። ጦሱ የብዙዎቹን ዜጎች ሕይወት የቀማ ሆነ።ከዚያ ጦስ የተራረፍነው ጥቂቶች አሁንም አለን፡። በወቅቱ የተፈጠረው ሁኔታ (The Crime and the Nation) የሚባለው አይነት ነው። እጅግ በጣም አዋቂና ለኢትዮጵያ ታላቅ ርእይ ያላቸውን ዜጎችን ሁሉ የፈጀ ነበር።

ቀጥሎ ደግሞ ደርግ ሲወድቅ ጥቅም ላይ ሳይውል የቀረው መልካም አጋጣሚ አውሮፓ ላይ የተደረገው ኢህአዴግ፣ ደርግ እና ሻዕቢያ ለውይይት የተቀመጡበት አጋጣሚ ነበር።እዛ ውይይትና ምክክር ላይ ሳይግባቡ ቢቀሩም ሰላማዊ በሆነ አግባብ ከደርግም ሆነ ከኢህአዴግም እንዲሁ ከሀገር ሽማግሌም ማለትም በወቅቱ እነፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ሁሉ የነበሩበት ነበር።

ያኔ ውይይቱ ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ ወያኔ በብልጠት ያደረገው አካሄድ በለዘበ እና በቁጥጥር በዋለ ነበር።ችግሩ ምንድን ነው ያልሽ እንደሆነ የአሸናፊ ፍትህ (Victor's justice) የሚሉት ነገር አለ። ይህ አይነቱ አካሔድ ረግጦ ይዞ ልግደልህ አይነት ነው። ተሸናፊው ምንም የማለት መብት የለውም። እነዚህ መጥተው የደርግ ሰራዊትንም የጦር ኃይሉንም ወንጀለኛ የማድረግ አባዜን ተያያዙት።ይህ ጨርሶ ፍትህ ወይም መልካም የሚባል አልነበረም፡፡

እኔ በወቅቱ በሽግግሩ ውስጥ የነበርኩ እንደመሆኔ ሁኔታውን አውቃለሁ። የማያውቁ ሰዎች የሚናገሩት የተለያየ ነገር ነው። በወቅቱ እዚህም እዚያም ኢትየጵያን ነጻ አውጪ ነን እያሉ የመጡ ነገሮች ኢትዮጵያን ነጻ ማውጣት ሳይሆን ፍላጎታቸው መበታተን ነበር። ሁሉም በየፊናው እንደጥሩ አጋጣሚ ሲጠቀምበት የነበረው የመንግሥትን መውደቅ ነበር። የተወሰዱ እርምጃዎች ሁሉ የብልጠት ነበሩ። ይህን የብልጠት አካሄዳቸውን ያልተገነዘቡ ሁሉ የሚያውሩላቸው ሌላ ነገር ነው። የነበሩ መልካም አጋጣሚዎችን የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ሳይጠቀሙባቸው የባከኑ ናቸው።

ሕዝቡ ደግሞ ዝም ብሎ "እመራሃለሁ" የሚለውን ሁሉ ያዳምጣል።የሚያስቸግሩት ስልጣኑን እኛ ካልያዝን በሚል ነፍጥ አንግበው ጫካ የገቡ ካልሆኑ በስተቀር የቀረው ሕዝብ የሚለው ነገር የለውም። ሕዝቡ በትክክል የሚመራውን ካገኘ አካባቢውን እየጠበበቀ ምርቱን ማምረት ይያያዛል። ስለዚህ እየተንከባለለ የሚመጣ ችግር የበዛው ያመለጡ አጋጣሚዎች ስላሉ ነው።ቢያንስ እየፈተናቸው እንሔድ ነበር።ነገር ግን ችግሩን የመፍታት ብቃት ያላቸው የፖለቲካ መሪዎች ባለመኖራቸው እዚህ መድረስ ተችሏል።

ኢህአዴግ ሴረኛ ለመሆኑ ዋናው ምክንያት ጉድለቱን ለመሙላት ሲል ነው።ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመምራት ብልጠትን መጠቀም የግድ ነበር።እኔ በበኩሌ እንደእዛ ማድረጋቸው አያስደንቀኝም። ሁሌም በቁጥር አነስ የሚለው ወገን ደግሞ ብልጠትን ቢያካትት አይገርምም።የተወሰዱትን የብልጠት እርምጃዎች ጊዜው የፈጠረው በመሆኑ ምንም ማድረግ አይቻልም። እንደእዛ ካላደረጉ እነርሱም የበላይነቱን ይዘው አይቆዩም ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ብልጽግና የነበሩትን ችግሮችን በግልጸኝነት ለመፍታት ቢሞክርም ሕዝቡ ግልጸኝነትን ተቀብሎ ማዳበር ባለመቻሉ ችግር**

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## “ኢትዮጵያ በሕዝቦቿ...

ከገጽ 7 የዞረ

**ተከስቷል። ስለሆነም መፍትሔው ምንድን ነው ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር** በየነ፡- እኔ የፖለቲካ ስብዕና አለኝ ብዬ አስባለሁ።አስቀድሜ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ያመለጡን የፖለቲካ አጋጣሚዎች የምንላቸው አሁንም ቢሆን አሚጠን ስላልተጠቀምናቸው ነው የሚል እይታ አለኝ።ለምሳሌ እኛ አሁን እየሰራን ያለነው ከብልጽግና ፓርቲ ጋር በትብበብር መንፈስ ነው።ለኢትዮጵያ እና ለሕዝቧ በሚበጅ ጉዳይ ላይ በትብብር እንሰራለን፡፡

እንዲህ ሲባል ግን መስመራችንን ትተናል ማለት አይደለም። ይህች ሀገር ትንሽ እፎይታ ያስፈልጋታል። በአመራርነቱ ቆንጮ ላይ ያለው አካል መልካም አስተሳሰብ ያለው እና ለሕዝቡም ለሀገሪቱም የሚበጅ ነገር እፈልጋለሁ ብሎ በተግባርም እያስመሰከረ እስከሔደ ድረስ ያንን ማመን የሚከብድ አይሆንም።እንደእዛ ካልሆነ ሌላ አጀንዳ ነው ማለት ነው። ዝም ብሎ ግርግር መፍጠር እና እከሌ እንዲህ አለ፤ እከሊት እንዲህ አለች እየተባባሉ ለመኖር ካልሆነ በስተቀር ማለት ነው።እኛ ያንን አልመረጥንም።ምክንያቱም ለሕዝባችንም አይበጅም በሚል ነው።

ችግሩ አሁን የደረሰበት ሊደርስ የቻለው ብልጽግናን ያቋቋሙ መልካም አስተሳሰብ ያላቸው መሪዎች በመቸኮላቸው ነው እላለሁ።ከኢህአዴግ ወደ ብልጽግና ሲሸጋገሩ በነበረው ጊዜ ፍጥነቱ በጣም የበዛ ከመሆኑ የተነሳ የጥይት ያህል የተወነጨፈ ነበር። በዚህ ፍጥነት ውስጥ አንድ ያመለጠ አጋጣሚ እንዳለ እረዳለሁ።ትንሽ የሽግግር ጊዜ ያስፈልግ ነበር። ሕወሓትም አኩርፎ መሸጎ ነበር። መመሸግ ብቻ አልነበረም። ጥቃት እስከማድረስ መክፋቱ የሚታወቅ ነበር።የዚያን ያህል ዝግጅት ላይ ሳይደረስ ሁኔታዎችን ለመግታት ሲባል የተናደደ ንዴቱ እስኪበርድለት ጊዜ አልተሰጠውም።

በወዲያኛው በኩል ያሉ ሰዎች በፖለቲካው ጥርሳቸውን የነቀሉ ናቸው። አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ ያቋቋሙ አይነት አይደሉም። በፖለቲካው ዘርፍ ጠንከር ያሉ እንደመሆቸው ከእነርሱ ጋር መወያየት እንደሚያስፈልግ ግንዛቤው ቢኖር ጥሩ ነበር።እዛ ላይ መቻኮል ታይቷል ባይ ነኝ። መቻኮል ባይኖር ኖሮ የደረሰውን አደጋ በትንሹም ቢሆን መቀነስ እንችል ነበር።


አሁን ባለው ሁኔታ ምን ማድረግ ይቻላል ላልሽው አንደኛ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም አስበልጦ የማየትን አካሄድ ማዕከል ማድረግን መልመድ አለብን። የተናደዱ፣ የተቆጡ እንዲሁም ተበደልን ያሉ ወገኖች ሁሉ ፍልስፍናዊ የሆነ አመለካከት ያስፈልጋቸዋል ባይ ነኝ።ዝም ብሎ የጎበዝ አለቃነት የትም የሚያደርሰን አይደለም። ምክንያቱም ከዚህች ሀገር ጋር የየዕለት ግንኙነት የሌላቸው ስንትና ስንት ሺ ኪሎ ሜትር ላይ ተቀምጠው በሀገሪቱ ላይ የሚወነጭፉት ነገር ብዙ ነው። የሚገድሉት ሆነ የሚያድኑት እንዲሁም የሚያፈርሱትና የሚገለብጡት ጉዳይ መብዛቱ ለመቆጣጠር ፈታኝ ነው። በመሆኑም ጊዜውን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

በእርግጥ ሰለጠኑ በሚባሉ ሀገራትም ዘንድ እንዲህ አይነቱ አካሄድ እየፈተናቸው መሆኑ የሚታወቅ ነው።እነርሱም በጋለ ምጣድ ላይ የመቀመጥ ያህል ጉዳዩ አንገብጋቢ እየሆነባቸው መጥቷል።ስለዚህ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ብቻ የደረሰ አድርጎ ማየት የለብንም። ሁላችንም ጉዳዩን ሰፋ አድርገን ለማየት መሞከር አለብን።እንዲያም ሆኖ እኛ ከሀገራችን ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም የምንለው ወገኖች፤ የተሻለውንና ሰላማዊ በሆነው ጉዳይ ላይ ልናተኩር ይገባል።

በዚህ ሀገር የማያባራ ጥያቄ አለ። ነጻ አውጪው ከመብዛቱ የተነሳ መቼ ነጻ ወጥተን እንደምናልቅ አይገባኝም። አንዳንዱም ገና ነጻ አልወጣሁም ይላል።ተማርን እውቀት አለን የሚሉትም ዘላለም ነጻ አልወጣንም ሲሉ ይደመጣል።ማን ከማን ነጻ ይወጣል? ማንስ ማንን ነጻ ያወጣል? ከዚህ መንፈስ መውጣትም መዳንም አለብን።ለዚህ ደግሞ ትዕግስት ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ዘመን ትዕግስት የሚታጣ ከሆነ መሳሪያ የሚያቀብል ሞልቷል።ሰርቶ የመኖር መላ ለጠፋበት አካል ደግሞ ይህ የሚመረጥ ይሆናል።እያወኩን ያለው ከዚህ የተሻለና የጠለቀ አጀንዳ የሌላቸው ናቸው።በአሁኑ ወቅት ሮጥ ብሎ ዘመድ ጠይቆ መምጣት ዝም ብሎ የሚወሰን ነገር አልሆነም።

እኔ ለምሳሌ በቅርቡ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት



ሠራተኞችን ይገፍ ለመዝናናትም ዓመታዊ ጉባኤ ለማካሄድም ወደ አርባምንጭ ተጉዤ ነበር። ወደ አርባምንጭ የመሄዳችን ነገር በአንጻራዊነት የሰላሙ ነገር ይሻላል በሚል ነው።ይሁንና ከሠራተኛው ውስጥ ፈርቶ የቀረ ነበር።ስለዚህ የእንቅስቃሴ ነጻነታችንን መነጠቅ አንሻም።በፍርሃት ቆፈን ውስጥ መውደቅም ጤንነት አይደለም።በፍርሃት ቆፈን ውስጥ ስንወድቅ ለሌላው የልብ ልብ ለመስጠት እንገደዳለን።ስለዚህ ሰው በእልኸኝነት እንቅስቃሴ መጀመር አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ስራውን የጀመረው ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ከዚህ አኳያ ተስፋውና ተግዳሮቱ ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** በሌሎችም ሀገራት አንዱ ሌላውን ከመበደሉ የተነሳ እስከ በቀል የሚያደርሱ ስሜቶች ይኖራሉ። በዚህ ጊዜ በመጀመሪያ እርቀ ሰላም ተብሎ በእኛ ሀገር ተሞከረ፡።በዚያን ጊዜ የኮሚሽኑ አባል ነበርኩ።ለሶስት ዓመት ያህል ያንን የእርቀ ሰላም መንፈስ ለማስረጽ ተሞከረ።ይሁንና በታሰበው ልክ ፈጥኖ ሊሄድልን አልቻለም።ምክንያቱም ኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ያላትና ሰፊ ሀገር እንደመሆኗ ለማዳረስ ችግር ነበር።አንደኛ የጥንት ሀገር እንደመሆኗ ጉዳዩ ከየት ነው የሚጀመረው የሚለው በራሱ አጠያያቂ ነበር።

በዚህች ሀገር ነው ታሪካዊ በደል ተበድለናል የሚለውም እየተንጸባረቀ ያለው። ከዚህ የተነሳ ስንቱ ተለይቶ ከተጋነነው ነጻ መውጣት ይቻላል።ነገር ግን በአግባቡ አነጣጥሮ ትክክለኛ ሕመም ያለበት ካለ ለማዳን ጥረት ይደረጋል እንጂ በግለሰብ ደረጃ ያለው ችግር እየቆጠረ መፍታት አይቻልም።ከዚህ የተነሳ በወቅቱ ጉዳዩ ትንሽ አስቸጋሪ እንደሆነ ተረድቻለሁ።

በእርግጥ የአሁኑ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚለው እንመካከር ነው። እኔ የነበርኩበት ደግሞ ችግሩን እንፍታ ነበር። አሁን እየመራሁት ባለው የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት፣ ፈጥነን የዓለም አቀፉ ሁኔታ ምን ይመስላል በሚል አጥንተን ለዚህ ኮሚሽን አቅርበናል። የኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች ብሔራዊ ውይይት የሚባለው ዓለም አቀፋዊ ገጽታው ምን ይመስላል? በአፍሪካ እና በሌላው የዓለም ሀገራት ምን ይመስላል? የሚለውን የዳሰሳ ጥናት አድርገን ለኮሚሽኑ አባል ማብራሪያ ሰጥተናል። የተጠረዘ ሰነድም ሰጥተናል። በዚህ መልክ ለተሞክሮ ይሆን ዘንድ ጥሩንም መጥፎውንም አጥንተን አቅርበናል፡፡

ስለዚህ ይህንን ሰፊ ማኅበረሰብ አገናኝቶ ለማወያየት አንደኛ ማኅበረሰቡን በትክክል የሚወክሉት ሕዝባዊ አመኔታ ያላቸው እንዲሆኑ ስብሰባዎችን ማካሔድ ያስፈልጋል።ምክንያቱም ከ120 ሚሊዮን በላይ የሆነውን ሕዝብ ማወያየት አይቻልምና ጉዳዩን በውክልና ማካሔድ ነው።

ይህ ሲደረግ አንዱ ተግዳሮት ሊሆን የሚችለው አንዳንዱ አካባቢ ተደራሽ ላይሆን መቻሉ ነው።እንዲህም ስል አሁን የጸጥታ ችግር ያለባቸውን አካባቢዎች ማለቴ ነው። እንዲያውም ዋና ውይይቱ የሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች ብዙ ችግር አለ።ያንን አካባቢ ሳንሸፍን ብንቀር ደግሞ ችግሩን ከመሰረቱ ፈትታን ማለት አይቻልም። ስለዚህ እነሱንም በማወያየት ወደሰላማዊ ሁኔታ ማምጣት ይመረጣል፡፡

አንዱ እኔን የሚያሳስበኝ ነገር ለራሳቸው ሰላም አጥተው ሀገሪቷን ሰላም የነሱ አካላት እንዴት አድርገን እናካትት የሚለው ጉዳይ ነው።እነሱን ትተን ሌሎቻችን ተስማማን ብንል በጥባጭ ባለበት የጠራ ውሃ መጠጣት አይቻልምና ችግር ይሆናል።በእርግጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከቁጥር አንጻር ስናይ እነሱ ሚዛን የሚደፉ አይደሉም።እንደዛም የተወሰነ ሆነው ሳለ እየበጠበጡ ነውና ይህ እንዳልኩሽ አንዱ ስጋቴ ነው።

ሰፊው ሕዝብ እንኳ በውይይቱ ላይ በሙላት ይሳተፋል። ያለበትን የልቡን ችግር በግልጽ ይናገራል። መፍትሔም እንዲያገኙ ወደአደባባይ ያመጣል። ይህን እንደ አንድ ተስፋ መውሰድ ይቻላል። ነገር ግን በጥባጮች አሉ። እነዚህ በጥባጮች ደግሞ "እኛ ያልነው ካልሆነ በስተቀር ስንበጠብጥ እንኖራለን" የሚሉ አሉ።ከዚህ የተነሳ ተወያዮችንና የመወያያ አጀንዳዎችን ኮሚሽኑ እየለየሁ ነው ቢልም ከእነዚህ ከተለዩ አካላት ጋር ሰርገው ገብተው የታለመለት የምክክር መድረክ እንዳይሳካ የሚያደርጉ አይጠፉምና እዚህ ላይ ጥንቃቄ ማድረጉ ተመራጭ ነው። ምክንያቱም ሰርጎ ገቦች አዳራሽ ድረስ ገብተው ሃሳብ እንዳይደራጅ የማድረግ ሙከራ ሊኖራቸው ስለሚችል ማጤን ይገባል። አጀንዳው ስኬታማ መሆን የሚችለው ምክክሩ ላይ የጋራ ግንዛቤ መጨበጥ ሲቻል ነው። ይህ እንዳይሆን የሚያደርግ አካል ምክክሩን እንዳይቀላቀልና እንዳያውክ በሚል ስጋት አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ መፍትሔው ምን መሆን አለበት ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** እንደ እኔ አተያይ ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም ነው የምለው።ምክክሩ መካሄድ አለበት።እሱ ጥሩ ጅምር ነው።ምናልባትም ይህ መንፈስ አስተማሪ ሆኖ ሌሎቹም ልብ እንዲገዙ ይረዳ ይሆናል።ምክንያቱም ሕዝቡ ከእነርሱ ጋር እንዳይደለ ሊረዱ ይችሉ ይሆናል።ምናልባትም በዚህ አጋጣሚም በጥባጮች ሊጋለጡ ይችላሉ። ከዚህ በኋላ በዱር በገደሉ መረበሽ አያስችለው ይሆናል። ስለዚህ እስከተቻለ ድረስ ይህ ምክክር መካሄድ ይኖርበታል። ምክክሩን መቶ በመቶ ማዳረስ ስላልቻልን ዋጋ የለውም የሚል ስሜት ሊነግስ አይገባም።

ምክክር መካሄዱ የሚያሳጣን አንዳች ነገር የለም፤ ይልቁን የሚጨምርልን መልካም ነገር አለው።መቼም ሚዛን የሚደፋው የሕዝብ ቁጥር በዚህ ምክክር ላይ የተለየ አቋም ይኖረዋል ብዬ አልገምትም።ፀጥታውን ያደፈረሱብንን አካላት ፈርተን ይህን መልካም አጋጣሚ እንዲያመልጠን ማድረግ የለብንም።እስካስኬደን ድረስ መሄድ አለብን።ከዚያም በሒደት እየገመገምን ምን ማድረግ ይቻላል የሚለውን እያየን እንቀጥላለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዓለም አቀፉ ማኅብረሰብ ለምክክሩ ሒደት ታማኝ ይሆናል ብለው ያስባሉ? የመፍትሔስ አካል መሆን ይችላሉ?**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሲባል በስደት ዓለም ያለው ዳያስፖራንም የሚያካትት ነው ባይ ነኝ። አብዛኛው ዳያስፖራ በጥባጭ ነው።በዛ በኩል አፍራሽ አስተሳሰብ ሊመጣ ይችላል።አንደኛ ከራሳቸው አልፎ የውጪውንም ማኅበረሰብ የማስተባበር ጥረት ያደርጋሉ።ለኢትዮጵያ የማይመጥን ገጽታ እያላበሱ ስሟን ለማጠልሸት ይሯሯጣሉ። ይሁንና ኢትዮጵያ እነሱ ከሚሏት በተቃራኒ ያለች ሀገር ናት፡፡

የዓለም አቀፉ ማኅብረሰብ ላልሽው እነርሱ ጉዳዩን የሚያዩት ከራሳቸው ጥቅም አኳያ ነው።አንድ ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር ከኢትዮጵያ ጋር መወዳጀት የማይፈልግ የውጭ ሀገር መንግሥት አለመኖሩን ነው። ኢትዮጵያ ዝነኛም ታሪካዊም ናት። ስለዚህ ከዚህች ሀገር ጋር ሁሉም መወዳጀት ይፈልጋል።እንዲያውም ወደእኔ ካልመጣሽ እየተባለ ለመወዳጀት የሚደረግ ሽሚያ ነው የሚበዛው እንጂ ሆነ ብሎ ኢትዮጵያን ለማፍረስና ለመበታተን የሚያስብም መንግሥት የለም ባይ ነኝ።ነገር ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ ነገሮችን በጥንቃቄ ማጤኑ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ ብትፈርስ የሚጠቀም አይኖርም። የኢትዮጵያ መፍረስ በብዙ የሚያጎድል እንደሆነ መንግሥታት አሳምረው የሚያውቁት ነው። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ፣ በጠቅላላ በአፍሪካ እንዲሁም በዓለም አቀፉ ዘንድ ተፈላጊ ሀገር ናት።

ለምሳሌ የቅርቡን ብቻ ማስታወስ በቂ ነው። በአህጉራችንም ሆነ በሌላ አህጉር በኢኮኖሚያቸው የሚበልጡና ሊመረጡ የሚችሉ ስንቶች እያሉ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል እንድትሆን መመረጧ ተፈላጊነቷን የሚያሳይ ነው። እንዲያውም እኔ ኢትዮጵያ ጠላቷ ታዋቂነቷ ነው ባይ ነኝ። ስለዚህ ኢትዮጵያን የሚፈልጓት ለማፍረስ ሳይሆን የራስ ለማድረግ ሊሆን ይችላል። በዚህ ውስጥ በሚደረግ ሩጫ ደግሞ መጎነታተል አይጠፋ ይሆናል እላለሁ፡፡

ኢትዮጵያ ደግሞ በስልት መጫወት ትችላለች። ከሁሉም ጋር በጋራ በሆነ ጉዳይ ላይ መስራት ነው። እኔ የምለው ኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ልጆቿ የውጭ መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ እንዲያምጹ የሚያደርጉትን ልመና ማቆም አለባቸው። የኢትዮጵያ መንግሥት ሆነ ብሎ አንድን ማኅበረሰብ ሊጎዳ እንደተነሳ አድርገው ማሰባቸውን ማቆም ይጠበቅባቸዋል። በጣም የሚያስ ገርመኝ አንዳንዶቹ በደርግም ሆነ በኢህአዴግ ጊዜ በሀገራችን ዴሞክራሲ ይምጣ ብለን ስንታገል የነበሩና በቅርብ የማውቃቸው ጭምር ናቸው።

እነዚህ አካላት ማዕረጋቸው ፕሮፌሰር፣ ዶክተር የሚል ሆኖ አሁን እየጻፉ ያለውን ሳስተውል ይደንቀኛል።እነዚህ ምሁር የተባሉ አካላት በአሁኑ ወቅት በጡረታ እድሜ ላይ የሚገኙም ጭምር ናቸው።" ወደቀ" ሲባል "ተሰበረ" ለማለት መፍጠናቸው ያስገርመኛል። መንግሥት ሲባል ዝም ብሎ ያሰኘውን የሚናገር አይደለም። አቋም መውሰድ ካለበት እንኳን ግራ ቀኙን መዝኖ ነው እንጂ እነርሱ በጮኹ ቁጥር አይደለም።ለምሳሌ ከ40 ዓመት በላይ የማውቃቸው "ለኢትዮጵያ እንታገላለን" የሚሉ ታጋዮች፣ ቀደም ሲል ለዴሞክራሲና ለነጻነት ሲታገሉ የነበሩ ናቸው። አሁን ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ካልፈረሰ በሚል አሜሪካንንም ሆነ ሌላውን ሀገር የሚማጸኑ መሆናቸው ያስደንቀኛል።

ስለዚህ ለኢትዮጵያ አደጋ የሚሆኑት የገዛ ልጆቿ ናቸው ባይ ነኝ እንጂ በእውነቱ የአለም አቀፉ መንግስታት ኢትዮጵያ ደክማ፣ ፍርሳና ተበታትና ሊያዩዋት አይፈልጉም። ምክንያቱም ከዚህ ሊጠሙ አይችሉምና ነው። ኢትዮጵያ እንድትጠፋ መስራት ማለት ራሳቸውን እንደማጥፋት የሚቆጠር ነው። ኢትዮጵያ ብትፈርስ ከ120 ሚሊዮን በላይ የሆነው ሕዝቧ የሚሰደደው ወደእነርሱ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ እንድትፍረከረክ በፍጹም አይሹም።

**አዲስ ዘመን፡- ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**ፕሮፌሰር በየነ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# የባለሀብቶችን ተሳትፎ ከግብርና አሻግሮ የማስፋት አዲስ ጥረት

አንተነህ ቸሬ

**በርካታ ባለሀብቶች ከግብርናው ዘርፍ በተጨማሪ በማምረቻና በአገልግሎት ዘርፎች እንዲሰማሩ ማድረግ ከ2016 የበጀት ዓመት እቅዶች መካከል አንዱ ነው። ክልሉ ከግብርናው ዘርፍ ባሻገር ባለሀብቶች በማምረቻና በአገልግሎት ዘርፎች በስፋት እንዲሰማሩ የሚያስችል የመሬት ዝግጅት ተግባር አከናውኗል**

ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንቱ ዘርፍ የሰጠችውን ትኩረት ተከትሎ መንግሥት የግሉ ዘርፍ በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ እንዲሰማራ በየጊዜው ምቹ ሁኔታዎችን ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ ሀገሪቱ በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ መሰማራት ለሚፈልጉ አካላት ያላትን እምቅ አቅም በማሳየት፣ ዘርፉን የሚያሳድጉ ሕጎችን በማውጣትና በመሳሰሉት ሠርቷል፤ እየሠራም ይገኛል፡፡

በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ የሚስተዋሉ ማነቆዎች ዘርፉን እንደሚፈለገው አላራምድ ባሉ ቁጥርም ማነቆዎቹን ለመፍታት ሠርቷል፡፡ ማነቆዎቹን ለመፍታት ካደረጋቸው ጥረቶች መካከል የዘርፉን የመሬት አቅርቦት እና የመሰረተ ልማት ችግር ለመፍታት የሄደበት ርቀት ይጠቀሳል፡፡ ለእዚህም የገነባቸው ግዙፍ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በአብነት ይጠቀሳሉ፡፡ የፓርኮቹ መገንባት በተለይ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ በኩል ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ እስከ አሁንም 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተገንብተው ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡

ይህም ባለሀብቶቹ የመሬት፣ የመሰረተ ልማትና የአገልግሎት ዘርፍ ችግር ሳይገጥማቸው ማምረቻዎቻቸውን አምጥተው በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ሼዶች በመትከል በቀጥታ ወደ ማምረትና መላክ የሚሸጋገሩበትን ሁኔታ ፈጥሯል፤ ይህ ምቹ ሁኔታ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ ኢንዱስትሪዎች ባለሀብቶችን ጭምር ለመሳብ አስችሏል፡፡

ባለሀብቶቹ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ችለዋል፤ ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እያቀረቡም ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ እያስገኙ ናቸው፡፡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው መስራት ጀምረዋል፡፡

የኢንቨስትመንቱ እንቅስቃሴው በክልሎችም በስፋት እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በክልሎች የተለያዩ ከተሞች በኢንቨስትመንቱ መስከ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው፡፡ ባለሀብቶች በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግና በመሳሰሉት ዘርፎች ተሰማርተው እያለሙ ተኪ እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በስፋት እያመረቱ ይገኛሉ፡፡ ይህ የባለሀብቶቹ ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ይህ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ጎልቶ ከሚታይባቸው ክልሎች አንዱ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ነው፡፡ ክልሉ እንደ ክልል ከተቋቋመ ቅርብ ጊዜ ቢሆንም፣ በዘርፉ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡

ክልሉ ለኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ሊውሉ የሚችሉ በርካታ ሀብቶች እንዳሉት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የክልሉን ሀብቶች ለመለየት የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ ክልሉ ለዓመታዊ ሰብሎች፣ ለቡናና ቅመማ ቅመም እና ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚውል ሰፊና ለም መሬት አለው፡፡ በአገልግሎትና በኢንዱስትሪ ዘርፎችም የኢንቨስትመንት መዳረሻና አማራጭ መሆን ይችላል፡፡

ክልሉ ወርቅን ጨምሮ በተለያዩ ማዕድናት ባለፀጋ እንደሆነም የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከወርቅ ማዕድን በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል የድንጋይ ከሰል በዳውሮ እና በኮንታ አካባቢዎች በስፋት የሚገኙ ሲሆን፣ ማእድኑ እየለማ ያለበት ሁኔታም አለ።

በክልሉ 15 አነስተኛ ደረጃ አምራቾች እና ሦስት በከፍተኛ ደረጃ አምራቾች በአጠቃላይ 18 አምራቾች ፈቃድ ወስደው ድንጋይ ከሰል ወደ ማምረት ሥራ ገብተዋል ፡፡ ከክልሉ በ2015 በጀት ዓመት 748 ሺ24 ቶን ያህል የድንጋይ ከሰል ለማምረት ታቅዶ፤ 209ሺ398 ቶን ለማምረት ተችሏል፡፡ ከገቢም አንጻር 30 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማስገባት ታቅዶ፤ 29 ነጥብ3 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት መቻሉን የክልሉ ማእድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ መረጃ ያመለክታል፡፡

ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የብረት ማዕድንም ሌላው በክልሉ የሚገኝ ሀብት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው ማዕድን ለማዕከላዊ ገበያ ከሚያቀርቡ የሀገሪቱ አካባቢዎች መካከል አንዱ ሆኗል፡፡ በክልሉ ገና በጥናት ያልተለዩ ብዙ ሀብቶች አሉ፡፡ ኦፓልና ሌሎች ማዕድናትም በክልሉ ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል፡፡

በርካታ ባለሀብቶች በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት አሳይተዋል፡፡ ክልሉ በክልልነት ከተዋቀረ አጭር እድሜ ቢኖረውም፣ ኢንቨስትመንቱ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሰፊ ጥናትና ውይይት ተደርጓል፡፡ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ገብተው በኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ለማበረታታት የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና የካቢኔ አባላትን ጭምር ያሳተፈ የንቅናቄና የፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ተሠርቷል፡፡

ክልሉ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ የተሰሩት የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሥራዎች በክልሉ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ በክልሉ በአጠቃላይ በተለያየ የሥራ ደረጃ ላይ የሚገኙና ለ112ሺ983 ዜጎች የሥራ እድል (7983 ቋሚ እና 105ሺ ጊዜያዊ) የፈጠሩ 380 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አሉ፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በ2015 በጀት ዓመት አበረታች የኢንቨስትመንት አፈፃፀም ማስመዝገቡንና በ2016 በጀት ዓመትም ይህን አፈፃፀሙን ለማሳደግ እየሠራ እንደሚገኝ የክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በ2015 የበጀት ዓመት በክልሉ ከሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ላስመዘገቡ 141 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱት ፕሮጀክቶች መካከል በግብርና 48፣ በማምረቻ 50 እና በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ስድስቱ ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ለሁለት ሺ 892 ዜጎች ቋሚ እና ለ79ሺ335 ዜጎች ደግሞ ጊዜያዊ የሥራ እድል መፍጠር እንዲሁም ለግብርና ሥራዎች የሚውል 32ሺ170 ሄክታር መሬት መለየት ተችሏል፡፡ ሦስት ሺ 600 አርሶ አደሮች የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ለ648 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ክትትል ተደርጓል፡፡ ማኅበረሰቡ ከኢንቨስትመንት ሥራዎች በሥራ እድል ፈጠራ፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በገበያ እድል እንዲሁም ባለሀብቶችም ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት በሚያከናውኗቸው ተግባራትም ኅብረተሰቡ የልዩ ልዩ ድጋፎችና አገልግሎቶች ተጠቃሚ እየሆነ ይገኛል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በኢንቨስትመንት ዘርፍ በ2015 በጀት ዓመት ያስመዘገባቸውን ስኬቶች በ2016 በጀት ዓመትም አጠናክሮ ለማስቀጠል እቅድ ማዘጋጀቱንና ዝግጅት ማድረጉን የክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ ምክትል ኃላፊና የኢንቨስትመንት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ከበደ ተስፋዬ ይገልጻሉ፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፣ በበጀት ዓመቱ በግብርና 84፣ በአገልግሎት 64 እንዲሁም በኢንዱስትሪ 58፣ በአጠቃላይ ለ206፣ ፕሮጀክቶች ፈቃድ በመስጠት ወደ ስራ ለማስገባት ታቅዷል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች ከ11 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል እንደሚያስመዘግቡና ከ109ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች (ሦስት ሺ 181 ቋሚ እና 105ሺ 951) የሥራ እድሎችን እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል፡፡

በክልሉ በርካታ ባለሀብቶች የተሰማሩት በግብርና ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው፣ በርካታ ባለሀብቶች ከግብርናው ዘርፍ በተጨማሪ በማምረቻና በአገልግሎት ዘርፎች እንዲሰማሩ ማድረግ ከ2016 በጀት ዓመት እቅዶች መካከል አንዱ መሆኑን ምክትል የቢሮ ኃላፊው አመልክተዋል፡፡ በክልሉ ከግብርናው ዘርፍ ባሻገር ባለሀብቶች በማምረቻና በአገልግሎት ዘርፎች በስፋት እንዲሰማሩ የሚያስችል የመሬት ዝግጅት መደረጉንም ነው ያስታወቁት፡፡

እንደ አቶ ከበደ ገለፃ፣ ከ2016 በጀት ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ በክልሉ እስካሁን ያለው ከፍተኛ የዝናብ ስርጭት መቀነሱን ተከትሎ ወደ ኢንቨስትመንት ተግባራት በስፋት ለመሰማራት ከሚደረገው ቅድመ ዝግጅት ጎን ለጎን፣ የመሬት ኦዲቲንግ ተግባር በከፍተኛ ትኩረት እየተሠራ ነው፡፡ ባለፈው የበጀት ዓመት በተከናወነ የመሬት ኦዲቲንግ ሥራ ስድስት ሺ 628 ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ ማስገባት ተችሏል፡፡ «እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች ካልተወሰዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በታለመላቸው የጊዜ ገደብ ላይጠናቀቁ ይችላሉ፡፡ ለዓመታዊ ሰብል ምርት ልማት የሚውል መሬት ፆም ማደር እንደሌለበት ታምኖ፣ በዘንድሮው በጀት ዓመት 64 ፕሮጀክቶችን ኦዲት ለማድረግ ታቅዷል፡፡ ይህ የኦዲቲንግ ሥራ መሬት ተረክበው የማያለሙ ባለሀብቶች በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ ወይም መሬቱን ለሌሎች አልሚዎች ለማስተላለፍ ያግዛል፡፡» ሲሉ አመልክተዋል፡፡

የኢንቨስትመንት አዋጁ (1180/2010) ለባለሀብቶች የተሰጡ መሬቶች ሊነጠቁ የሚችሉባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በግልፅ አስቀምጧል፡፡ የባለሀብቶች የሥራ እንቅስቃሴዎች በእነዚህ መስፈርቶች መሰረት ተገምግመው ቅድመ ሁኔታዎቹ ካልተሟሉ መሬት እንዲነጠቁ ይደረጋል» ይላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለአዳዲስ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እየተሰጠም ይገኛል፡፡ ለአምስት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ፕሮጀክቶች ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን፣ 28 የግብርና ዘርፍ ፕሮጀክቶች ደግሞ አስፈላጊው ማጣራትና ግምገማ ተደርጎባቸዋል፡፡

ለኢንቨስትመንት የሚሆን አቅም ያለውን መሬት በማጥናት ረገድ በበጀት ዓመቱ 12ሺ650 ሄክታር መሬት ለማጥናት መታቀዱን ጠቅሰው፣ የግብርና ሚኒስቴር ከክልሉ በቀረበለት የድጋፍ ጥያቄና የፕሮጀክት እቅድ መሰረት ለጥናቱ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በየደረጃው የሚገኙ የክልሉ ተቋማት ለባለሀብቶች መረጃ ከመስጠት ጀምሮ የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ለማስፈን ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች በጥልቀት እንዲታዩ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፈቃድና መሬት በፍጥነት እንዲሰጡ እየተደረገ ነው፡፡

በመሰረተ ልማት ዝርጋታ ረገድ ነባሮቹን የማጠናከር እና የተጀመሩትን የመጨረስ እንጂ አዳዲስ በተለይ መንገዶችን ለመገንባት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እንደሌሉም አቶ ከበደ ይገልፃሉ፡፡ እርሳቸው እንደሚናገሩት፣ በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ላይ መሰናክል ሊፈጥር የሚችለው ዋናው ችግር የበጀት እጥረት ነው፡፡ የክልሉ ዞኖች የሚመደብላቸው በጀት ቀደም ሲል በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር በነበሩበት ጊዜ የነበራቸው በጀት ነው፡፡ ሀገሪቱ ያለችበት ነባራዊ ሁኔታም ተጨማሪ በጀት ለማግኘት የሚያስችል አይደለም፡፡

«በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ‹አንድ ባለ ሀብት ወደ አንድ አካባቢ ሲመጣ ለማኅበረሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት ምንድን ነው?› የሚለው ጥያቄ ትኩረት የሚሻ ዐቢይ ጉዳይ ነው» የሚሉት አቶ ከበደ፣ ይኸው ጉዳይ የክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተግባር አካል እንደሆነም ይናገራሉ፡፡ «ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት መስክ ሲሰማሩ የሥራ እድል መፍጠር አለባቸው፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡» ሲሉ ገልጸው፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር አስተዋፅኦ የማያበረክቱ ከሆነ፣ የኅብረተሰቡ ኑሮ ሊለወጥና ሊሻሻል አይችልም ፤ ይህ ደግሞ የኢንቨስትመንት ተግባራት ዘላቂ ፋይዳ እንዳይኖራቸው ያደርጋል ይላሉ፡፡

ስለሆነም ባለሀብቶች ለቴክኖሎጂ ሽግግር ትኩረት እንዲሰጡ ጥረት እንደሚደረግ አስታውቀው፣ በዚህ መሰረት በበጀት ዓመቱ ሰባት ሺ 949 አርሶ አደሮች የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆኑ መታቀዱን ተናግረዋል፡፡ በሌላ በኩል ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ተግባራት የሚሰማሩት ሰርተው ለመጠቀም (ትርፍ ለማግኘት) አልመው እንደሆነ ባይካድም፣ አቅማቸው በፈቀደ መጠን ለኅብረተሰቡ ዓይነተ-ብዙ ድጋፎችን ያደርጋሉ ያሉት አቶ ከበደ፣ በክልሉ በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ ባለሀብቶች ለተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ያደርጋሉ፤የአረጋውያንን ቤት ያድሳሉ ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ባለፈው ዓመት ከ88 ኪሎ ሜትር በላይ መዳረሻ መንገዶች በባለሀብቶችና በኅብረተሰቡ ትብብር ተገንብተዋል፡፡ በዘንድሮው የበጀት ዓመት ደግሞ 96 ኪሎ ሜትር መንገድ ይገነባል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ «ባለሀብቱ ከኅብረተሰቡ ጎን፣ ኅብረተሰቡም ከባለሀብቱ ጎን ካልቆመ ጥሩ ያልሆኑ አጋጣሚዎች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ቀደም ሲል ከተፈጠሩ ክስተቶች ተምረናል፡፡ ባለሀብቶች ለኅብረተሰቡ ድጋፍ ሲያደርጉ ኅብረተሰቡ የባለሀብቶችን ንብረት ይጠብቃል፣ ይንከባከባል ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡ የኅብረተሰቡን ድጋፍ ያላገኙ ባለሀብቶች ደግሞ ብዙ ጉዳትና ኪሳራ ይደርስባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ ክልሉ ከባለሀብቶች ጋር ተቀራርቦ በትብብር እየሠራ ይገኛል ሲሉ የኅብረተሰቡና የባለሀብቶች ትብብር ስላለው ትልቅ ትርጉም አስረድተዋል፡፡

# ጎሜ

# ተመካክረን ውስጣችንን እናጽዳ

አስቴር ኤልያስ

ሰፈር የደረሰችው አርፍዳ ነው፤ እንደዋዛ የእጅ ቦርሳዋን ጠረጴዛው ላይ ጣል አድርጋ የሁለቱን ጓደኞቿን ጉንጮች አንዳንድ ጊዜ ብቻ በጎንጯ አነካክታ ሶፋው ላይ ዘፍ አለች፡፡...ወደ ኋላዋ ደገፍ ብላ በረጅሙ ከተነፈሰች በኋላ ‹‹እኔ ደግሞ አቦሉ ያመለጠኝ መስሎኝ ነበር›› ስትል በዝግታ ተናገረች።

እውነት ለመናገር ማርታ ታደሰ፣ የጓጓችው አቦል ለመጠጣት ብቻ አልነበረም፤ ምንም እንኳ ዛሬ ቅዝዝ ብትልም ቡናው እየተጠጣ የሚነሳው የተለያየ ርዕስ የያዘ ወሬ ጭምር እንጂ።በእርግጥ ዛሬ ብዙም የማውራት እቅድ ያላት አትመስልም፡፡፡

‹‹አይ ማርቲ! ያንቺን መምጣት እየጠበቅን እንጂ አቦሉማ እስካሁን አይቆይሽም ነበር›› አለቻት ጓደኛዋ ሮማን ባልቻ፣ በማንደጃው ላይ ያለው ከሰል አመዱን ለማላቀቅ ያህል በመቆንጠጫው ነካ ነካ እያደረገች።‹‹እኔማ እኮ ቶሎ የምትመጪ መስሎኝ ቡናውን መቁላት ጀምርኩ፤ ትንሽ አዘግይቼው ቢሆን ይሸትሽ ነበር።የሆነው ሆኖ መቆየትሽ በሰላም ነው?›› ስትል ሮማን ጠየቀቻት፡፡

ቀድማ የተገኘችው ጓደኛዋ ዘነበች ደስታም ‹‹ዛሬ ስራ በዛ እንዴ? ስትል የሮማንን ጥያቄ አጠናከረች።ማርታ የቆየችበትን እውነተኛ ምክንያት ለጓደኞቿ መግለጽ አልፈለገችም፤ በእርግጥ ብትነግራቸው የእርሷን ያህል የሚጨነቁላት እንደሆነ ታውቃለች።ይሁንና የእርሷ ጭንቀት አንሶ እነርሱንም ማስጨነቅ በፍጹም አትፈልግም፤ ይህን እያሰላሰለች ሳለ መልስ መስጠት እንደሚጠበቅባት ዘንግታው ኖሮ ...‹‹አሃ!... ዛሬ ደግሞ ከየት የመጣ ዝምታ ነው በይ!›› ስትል ሮማን ለመጀመሪያው ጥያቄዋ መልስ ሳታገኝ ሌላ ጥያቄ ደገመች፡፡

‹‹ውይ...የዛሬው የታክሲ ሰልፍ ደግሞ አይጣል ነው፤ ታክሲ ጥበቃ ሰልፍ ላይ ከአርባ ደቂቃ በላይ አልቆምኩም ብላችሁ ነው!?›› ስትል ቀድሞ የመጣላትን ሰበብ ተነፈሰች።በእርግጥ ቀለሟ ለአዲስ ዓመት እናቷን ለመጠየቅ አስባ አልተሳካላትም።ከዛ በፊትም መሄድ ፈልጋ የነበረ ቢሆንም ያለው የጸጥታ ሁኔታ አሳሳቢ በመሆኑ እናቷን ለመጠየቅ አልታደለችም።ዛሬ ያሳሰባት ግን በለመደችው የስልክ ቁጥር ላይ ከቀናት በፊትም ሆነ ዛሬ ደጋግማ ብትደውልም ከአገልግሎት መስጫ ከልል ውጭ በመሆኑ ነው፡፡

ምንም እንኳ የተቀዳላትን ቡና ያለፋታ ጠጥታ ስኒውን ከዘነበች ቀድማ ብትመልስም ከእርሷና ከዘነበች ፊት የተቀመጠውን የቡና ቁርስ ግን ዘነበች በተደጋጋሚ ስትቆርስለት ማርታ ግን በተደጋጋሚ ስልኳን ትጠቀጥቅ ነበር።‹‹ማርቲ!..፣ደህና ነሽ?... አልታወቀሽም እንጂ እያጉተመተምሽ እኮ ነው›› አለቻት ሁኔታዋን በትኩረት ትከታተል የነበረችው ሮማን፡፡

በዚህ መሃል የማርታ ስልክ አቃጨለ፤ የማታውቀው ቁጥር ነው፤ ፈራ ተባ እያለች አነሳችው። ‹‹ከወዲያኛው ጫፍ ተለቅ ያሉ ሰው አይነት ድምጽ ‹‹ሃ..ሎ...›› ሲል ተሰማት።ባለማንሳት በዝምታዋ ልትጸና ወሰነች።ነገር ግን ያለ ፈቃዷ እጇ ሳይታዘዝ አረንጓዴውን ነክቶት ኖሮ ‹‹ሄሎ..አቤት!...›› የሚል ድምጽ ከውስጧ ሲወጣ ታወቃት።‹‹ማርታ ነሽ የኔ ልጅ...›› ሲሉ በድምጻቸው የእናቷ ጎረቤት መሆናቸውን አወቀች።አሁንም በደመነፍስ አዎንታዋን ገልጻላቸው በእርሳቸው ስልክ ከቀን ጀምሮ ስትሞክርላቸው እንደነበር ነገረቻቸውና የእናቷን ደህንነት ጠየቀቻቸው። ‹‹እርሷ ምን ትሆናለች ብለሽ ነው፤ ደህና ናት የኔ ልጅ። የእኔ ስልክ ባትሪዋ አልቆ ኖሮ ነው የተቸገርሽው።በይ ይኸው እናትሽን አናግሪያት...›› ሲሏት እውነት አለመሰላትም።‹‹የልጄን ድምጽ ሳልሰማ ሰነበትኩ ስላለችኝ ነው በሌላ ሰው ስልክ ለምኜ መደወሌ...›› ቢሏትም የሰማቻቸው ‹‹አናግሪያት›› የምትለዋን ቃል ብቻ ነውና ጆሮዋን አቁማ ከወዲያኛው ጫፍ ትጠባበቅ የነበረው የእናቷን ድምጽ ነበር፡፡

አሁን ሁሉም ሰላም ሆኗል፤ ማርታ የእናቷን ድምጽ በመስማቷ ለበሽታው ትክክለኛ መድኃኒት አግኝቶ እንደተፈወሰ ሰው ፊቷ ሁሉ በራ።ለጭንቀቷ እፎይታ በማግኘቷም ለጓደኞቿ ሲያሳስባት የነበረውን ነገረቻቸው።

ዘነበች፣ በተራዋ ጭንቀቱ የተጋባባት ይመስል ‹‹ግን እስከ መቼ ነው በዚህ አይነት መንገድ የምንቀጥለው›› ስትል ፊቷን ክስክስ አደረገች።‹‹አንድ የማይገባኝ ነገር ቢኖር ልጅ ወላጁን፤ ወገን ወገኑን የሚጠይቀው እንዴት ነው? አሁን እኮ ዘመድ ለመጠየቅ ወደ ምዕራቡም ሆነ ወደ ሰሜኑ የአገራችን ክፍል ላቅና ብትይ ከመንቀሳቀስሽ በፊት ደጋግመሽ ማሰብ ይጠበቅብሻል።እንደ አጋጣሚ ሆኖ ደግሞ የክፍለ ሀገር ልጆች ነን።ከወገንሽ ጋር አትቆራረጪም።አያድርስና ከዘመዶቻችን አንዳቸው እክል ቢያጋጥማቸው ለመሄድ ያለው ስጋት ከባድ ነው።መቼም ምንም እንኳ ሮሚ የሸገር ልጅ ብትሆኚም ክፍለ አገር ያሉ ዘመዶችሽን ለመጠየቅ በደስታም በሐዘኑም መድረስሽ አይቀርም›› አለች፡፡

ምንም እንኳ ዘነበች አሁን ላይ ስላለው ሁኔታ እና እሱን ተከትሎ ስለተፈጠረው ስጋት ቅዝዝ ባለ መንፈስ ሆና እያወራች ቢሆንም በማርታ ፊት ላይ እየታየ ያለው መረጋጋት አልደበዘዘም፤ ብቻ የእናቷን ድምጽ በመስማቷ ደስ ብሏታል።‹‹ሰው ቤተሰቡንም ሆነ ዘመዱን ጥየቃ በመኪና መሄድን ፈርቷል።ከመኪና ውጭ ያለው አማራጭ ደግሞ አውሮፕላን ነው።ነገር ግን እሱም ቢሆን የሚያደርሰው ዋና ከተማ የሚባሉት ድረስ እንጂ በየዞኑ፣ ወረዳውና ቀበሌው ድረስ አያስገባ!...›› ስትል ዘነበች፣ ሁለተኛውን ቡና ቀድታ ሲኒውን እያቀበለች ያለችው ሮማን ደግሞ፤ ‹‹ዘኒ!... አሁን እንዳልሽው አውሮፕላኑ ቀበሌሽ ድረስ ኸረ እንዲያው ሰፈርሽ መግባት ቢችል ዋጋውን አስበሽዋል? ትችያለሽ!? እንደ እኔ ከባድ ነው።

እንዲያው ግን.... አፍ አውጥቶ አይናገር እንጂ አሁን አሁን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትርፍ በትርፍ ሳይሆን ይቀር ብለሽ ነው። በቀደም ዕለት ከክፍለ ሀገር የመጡ ዘመዶቼን ልሸኛቸው አየር መንገድ ስሔድ ገና ረፋድ ላይ ወደዚያች ከተማ በቀን ለስድስተኛ ዙር ተሳፋሪዎች ወደ አውሮፕላኑ እየገቡ መሆናቸውን ሰማሁ።ለወትሮው እኮ እኔ እስከማውቀው ድረስ ወደዚያች ከተማ አውሮፕላኑ የሚበረው ረፋድ ላይ አምስት ሰዓት፤ ከሰዓት በኋላ ደግሞ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ብቻ ነበር።ታዲያ በዚህ ዘመን እንደ አየር መንገዳችን ማን የታደለ አለ?! "ትርፍ በትርፍ ሆኛለሁ" ብሎ ሚዲያውን ጠርቶ መግለጫ አለመስጠቱ እሱ ሆኖ ነው እንጂ ትርፉንማ እያጋበሰው ነው›› አለች፡፡

የእናቷን ድምጽ መስማቷ አቅምም ደስታም የፈጠረላት ማርታ፣ መጨረሻ አካባቢ ሮማን ያወራችውን በመስማቷ ‹‹በአየር መንገዳችንማ እንድትመጪብኝ አልፈቅድልሽም ሮሚ፤ መኩሪያዎቻችንንና መንቀባረሪያዎቻችንን ጫፉን መንካት አትችይም። በከፍታው ላይ ከአህጉር አህጉር ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርጎ የሚያሳየውን ተቋም መንካት የአይናችንን ብሌን እንደመንካት ነው የሚቆጠረው።ደግሞ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ምን አሳጣኝ ብሎ ነው ከአገር ውስጥ የተቃረመችውን ገንዘብ ‹ትርፉማ ሆኛለሁ› ብሎ መግለጫ የሚሰጠው!? ተቋሙ እኮ በየቀኑ በሚያስብል ደረጃ አንዴ ከአህጉራችን ሌላ ጊዜ ደግሞ ከዓለም አቀፍ የታላቅነቱን ምስክርነት የሚያረጋግጥለትን ማስረጃ የሚቀበለው፡፡

ወይኔ...!? ምናለ በአገራችን ያሉ ተቋማት ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ አስተማማኝ ቢሆኑ!?...›› እያለች ልትቀጥል ሲዳዳት፤ ‹‹እንዴ ማርቲ!?...እኔ መች ታላቅ ተቋም አይደለም አልኩሽ? እኔ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ አንቺ አለኝ ከምትይው በላይ ክብርም ኩራትም እንዳለኝ መዘንጋት የለብሽም›› ብላ አጋምሳ ያስቀመጠችውን ቡና ለመጨረስ ስኒውን አንስታ ወደአፏ ስታስጠጋው ቡናው ቅዝቅዝ በማለቱ መልሳ አስቀመጠችውና ረከቦቱን ባለበት ትታ ወደሶፋው መጥታ ተቀላቀለቻቸው፡፡

ዘነበች፣ የራሷን እና የማርታን ስኒ ደራርባ ካነሳች በኋላ ሳትነጣጥላቸው እንደዚያው ረከቦቱ ላይ አስቀምጣ ወደነበረችበት ተመለሰች።ቀጥላም ‹‹ጓደኞቼ! ኢትዮጵያ አየር መንገድ ባይኖር እኮ የበለጠ ከዘመዶቻችን ጋር ለመገናኘት ይቸግረን ነበር።የእሱ መኖር ነው በቀላሉ ዘመዶቻችንን ለበዓል እንኳ እንድንጠይቅ ያስቻለን።የሆኖ ሆኖ ዋናው ሰላም ነውና ሀገራችንን ሰላም ያድርግልን።ሰላሙ ሲመለስ እንደለመድነው በአውቶቡስ ሽር ብትን ብለን የፈለግነው ቦታ ደርሰን መመለስ እንችላለን፡፡

ግን በዚህ መሃል የታዘብኳቸው አሉ።ሰላም ሲባል የሚያማቸውና የሚያንቀጠቅጣቸው።በለው፤ ግደለው፤ ግፋው ማለት የሚቀናቸው።‹ብጥብጡና ኹከቱ በጣም ተመችቶኛል፤ በዚሁ ይቀጥል› ላለማለታቸው በእርግጥ ማሳያ የለኝም እንጂ ሕዝቡ እንዳይተማመን የሚያደርጉ፤ አንዱ ሌላውን በጎሪጥ እንዲያይ የሚጥሩ መኖራቸው የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ሰንብቷል። ሲሆን ሲሆን ዘመቻ መክፈትና የማያዳግም እርምጃ መውሰድ እነርሱ ላይ ነበር›› ስትል በቁጭት መንፈስ ተናገረች።

‹‹ዘኒ! አስር ቦታ ሆኖ አንዱንም ለመስማት ግራ ገብቶሽ ካልሆነ በስተቀር በአደባባይ አይደለም እንዴ በማህበራዊ ትስስር ገጹ ላይ ‹በለው! ግፋ! በርታ! ውቃው!› እያሉ ምኞታቸውን በቁም ሲቃዡ የሚውሉ።በእርግጥ ምኞት ብቻ ሆኖባቸው ቢቀር መልካም ነበር፤ አንዳንዶች ባለማወቅ በቁማቸው ሲቃዡ የሚውሉትን ቅዠት ሲሰሙና በስሜት ሲናጡ ይስተዋላሉ፡፡

ሰውም ክፉ ምክራቸውን ባይሰማ ይበጅ ነበር። አገር አፍራሽ ጥሪያቸውን አልሰማም ቢል ያዋጣ ነበር።ሁሌ ከጉዳታችንና ከውድቀታችን የምንማረው ነገር አላበቃ ማለቱ ያስገርመኛል›› ስትል ነገ ሊከሰት የሚችለውን አሻግራ በማሰብ ስለነበር፤ ቅድም ስትገባ የነበራት ስሜት መልሶ ሊቆጣጠራት ሲዳዳው ተሰማትና ዝም አለች።

> የሚካሄደው አገራዊ ምክክር ሁሉንም ህዝብ የሚያሳትፍ ነው፡፡ በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል፣ መተማመን የሰፈነበትና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችል አግባብ ነው የሚከናወነው

ማርታ ‹‹መፍትሔው ምንድን ነው!?›› ስትል በልቧ አሰበች። ወደአዕምሯዋ የመጣው ነገር ግን ይህ ከሰሞኑን አጀንዳ ልየታ ነው...ተሳታፊ ልየታ... የተባለው የምክክር ኮሚሽኑ ስራ ነበርና ‹‹እኔ የምለው ጓደኞቼ...ይህ እነ ፕሮፌሰር መስፍን ያሉበት የምክክር መድረክ በዚህ ዓመት እንዲያው የሆነ መላ ያመጣልን ይሆን!?›› ስትል የሮማንን እና የዘነበችን አይን እያየች ጠየቀቻቸው፡፡

ዘነበች፣ ቀበል አድርጋ ‹‹በነገራችን ላይ ውይይት እና ምክክር የሚለው ቃል ይለያያል፤ ማለቴ ማወያየት እና ምክክር ማድረግ ለየቅል ናቸው፡፡...›› ብላ ልዩነታቸውን በብያኔ አስደግፋ ልታብራራ ስትል፤ ሮማን ቀበል አድርጋ ‹‹ያው ናቸው ባክሽ፤ መከረም ዘከረም ያው እርቅ ለማምጣት አይደል!? የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው አሉ...›› ብላ እሷም ገና ሐሳቧን ስትጨርስ፤ ማርታ፣ መፍትሔው የተገኘ ያህል ፈጥና ‹‹መመካከርም ሆነ መወያየት በጣም መልካም የሆነ ነገር ነው፤ ለሰላም ሲባል ደግሞ አስገድዶም ለሰላም እጅ ማስጠት እንኳ ቢሆን ትርፉማ እንሆናለን እንጂ ማንም ኪሳራ ውስጥ አይገባም›› አለች።

ከአፏ እየነጠቃት አላስወራ ያሏትን ሁለቱንም ጓደኞቿን በየተራ እያየች የቆየችው ዘነበች፣ ሁለቱም የየበኩላቸውን ተናግረው ጋብ ማለታቸውን አስተውላ ‹‹ለማንኛውም ይህ ዛሬ ያነሳነው ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁ በዋዛ የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም፤ በትክክለኛው መንገድ አስተውለን ካልተንቀሳቀስን በነገው ትውልድ ማለትም በልጆቻችን እጣ ፈንታ ላይ ጭምር እንደመቀለድ የሚቆጠር ይሆናል።የሆነው ሆኖ መመካከር እኮ መልካም ነገር ነው።

ለምን ይሆን ኮሚሽኑ የያዘውን እቅድ ለማጣጣል ታች ላይ የሚሉ የሚበዙት!?...፡ ማለት... የሚካሄደው አገራዊ ምክክር ሁሉንም ህዝብ የሚያሳትፍ ነው። በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል፣ መተማመን የሰፈነበትና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችል አግባብ ነው የሚከናወነው። ታዲያ ችግሩ ምኑ ላይ ነው?›› ስትል እንዳያቋርጧት በመፍራት እና ጊዜውም ለአይን ያዝ ማድረግ በመጀመሩ አጠር አድርጋ ሐሳቧን ጥያቄም ስጋትም ያዘለ አድርጋ ገለጸችላቸው፡፡

አከታትላም፣ "እስስቷን ሳያት ነው የምበረግገው አለ አለ ዘፋኙ" አለችና "እኔም ልክ ዘፋኙ እንዳለው ምክክሩ ስኬታማ እንዳይሆን ለማድረግ ይጥራሉ ብዬ የማስበው እስስቶች ከተቀላቀሉ ነው ባይ ነኝ።ቀና ልብ ያለውና ተበድያለሁ ባይ ለዚህ ምክክር ይሁንታውን የሚነፍግ አይመስለኝም።የእውነት ቅር ተሰኝቶ ከሆነ፣ የምርም ተበድሎ ከሆነ በይቅርታ መካስን የሚጠላ እና አሻፈረኝ የሚል አለ ብዬ አላስብም።

ከፍቶ የሚመጣ ብሶት ቢኖር፤ የነፈረና የቆሰለ ውስጠት ባይጠፋም ተመካክረን ውስጣችንን እናጽዳ በሚል ለመጣ አጀንዳ ጀርባውን የሚሰጥ ይኖራል ብዬ አልገምትም።ጀርባውን ከሰጠማ በቀላሉ መታከም ሲችል ቁስሉ እንደመረቀዘ ሊቀር ይችላል።ስለዚህ እኔን የሚያሳስበኝ ወገን ከወገኑ ጋር፣ ብሔር ከብሔሩ ጎሳውም ከጎሳው ጋር እንዳይስማማ እና እርስ በእርሱ ጥርጣሬ ውስጥ እንዲወድቅ የምታደርገው የእስስቷ ጉዳይ ነው፡፡"

ጓደኛሞቹ ለተጨማሪ ወሬ ጊዜ ስላልነበራቸው ሁሉም ሐሳባቸውን ወደመምሸቱ ላይ አድርገው ማርታ እና ዘነበች የእጅ ቦርሳቸውን ብድግ ብድግ አድርገው ቆሙ።ሮማን፣ ‹‹እስኪ መልካሙን ያምጣልን...›› ስትል፣ ‹‹ዋናው ነገር ከመልካም ነገር ጋር መተባበር ነው›› አለች ማርታ።‹‹ሌላውንም የመልካም ነገር ተባባሪ ማድረግ ወደ አሸናፊነት የመጠጋት ያህል የሚቆጠር ነው›› አለችና ልትሸኛቸው ከተል ያለቻቸውን ሮማንን እንዳትወጣ ገፋ አድርጋት ልክ እንደማርታ ሁሉ ጉንጯን ከጉንጯ ጋር አነካክታ እስከመገንጠያው ድረስ ለመሄድ ከማርታ ጋር ተያይዘው ወጡ።

# የዘመን ጥበብ

# ጥበብ- በአሜንታ ወይንስ በጉምጉምታ?




ሙሉጌታ ብርሃኑ

አንዳንድ የኪነ ጥበብ ዘርፎች ወደ ሀገራችን ብቅ ብቅ ማለት ሲጀምሩ ሕዝቡም ማልዶ በመነሳት ‹ይሄ ደግሞ የምን ጉድ ነው› ሲል አይኑን በጥያቄ ማሸቱ አልቀረም ነበር። በግራ መጋባትና በጥርጣሬም በአይነ ቁራኛ ሲመለከታቸው ኖሯል። የቆየ ባህልና ሥርዓቱም አዳዲስ ነገሮችን በአሜንታ የመቀበል ፍላጎቱን ከልቡ ውስጥ በሩን በመዝጋት ክርችም አድርጎ ቆልፎበት ነበር። እንደ ባዕድና ዘመን አመጣሽ ይታይ ስለነበረም ፍጥጫው ትውልዱን ነጻ የማውጣትም ጭምር ነበር። ንጉሱ አጼ ምሊኒክ ስልክን ወደ ሀገራችን አስገብተው በቀጭኑ ሽቦ ለመጀመሪያ ጊዜ `ሃሎው` ሲሉ ሕዝቡም፤ ንጉሱ የሰይጣንን ነገር ወደ ሀገራችን አስገቡ እያለ በጊዜው ሲያማቸው ነበር። ታዲያ የኋላ ኋላ ጥቅሙን ሲረዳ `አበስኩ ገበርኩ! ለካ እንዲህ ኖሯል እንዴ? በማለት የሀሜት አፉን አብሶ በምስጋና መመለሱ አልቀረም። በኪነ ጥበቡም ቢሆን የነበሩት አብዛኛዎቹ ከዚሁ ተመሳሳይ ናቸው። ሲመጡ አዲስ እየሆኑብንና ጠረናቸው እየከረፋን አፍንጫችንን እንይዝባቸዋልን። የኛን ባህልና ወግ የሚያጠፉ እየመሰለን ከአዝመራው መሃል እንደበቀለ አረም ነቅለን ለመጣል ብዙ እንታገላለን። መጨረሻውም ሊሆን የሚችለው ወይ ሰልችቶን እንተወዋለን አሊያም ወደን በፍቅር እንቀበለዋለን።

ለኢትዮጵያዊማ ስለ ጥበብና ኪነ ጥበብ እንዴት ይነገረዋል? ቀድሞውንስ የእርሱ የራሱ አይደሉምን? ሁሉም የኪነ ጥበብ ዘርፍ አሜንታዊ ገጽታ አልነበራቸውም እንዳንል የድንጋይ ላይ ሥዕሎችን፣ የብራና ላይ ጽሁፎችን ለዓለም ያስተማረው ማን ሆነና... ቅኔ ማህሌቱን በአዕዋፋት ዝማሬ ያስደመጠውስ? ብቻ ግን የጉምጉምታ ናዳ እየወረደባቸው የኛው ሆነው ወደፊትም ወደኋላም ሳይሉ፤ በተዘጋ ቤት እንዲኖሩ የፈረድንባቸው የኪነ ጥበብ ልጆችም አሉ። ለምሳሌ ያህል ለዛሬው ልናነሳቸው ከመረጥናቸው ሙዚቃ በቤት ስሙ ደግሞ አዝማሪነት አንደኛው ሲሆን ሌላኛውና ሁለተኛው ደግሞ መነሻውን ከወደ ባህር ማዶ አድርጎ ከቴክኖሎጂው ማሳ ስለበቀለው የፊልሙ ኢንዱስትሪ ይሆናል። ሁለቱ የኪነ ጥበብ ዘርፎች በሀገራችን ከመነሻቸው አንስቶ በአሜንታና በጉምጉምታ ታጥረው ሲኮረኮሙ የኖሩ ናቸው። ከውልደታቸው አንጻር ለእድገታቸው መቀጨጭ መንስኤውም ይሄው ኩርኩም ነው ሲሉ አንዳንዶች ይቼን ሀሳብ ጣል ያደርጋሉ። ከባህልና ማሕበረሰብ እስከ ኪነ ጥበብ፣ ከአዝማሪነት እስከ ሙዚቀኝነት፣ ከሰይጣን ቤት እስከ ፊልም ኢንዱስትሪው በአሜንታ ወይንስ በጉምጉምታ?

የሀገራችን የሙዚቃ ታሪክ ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ይጀምራል፡፡ መነሻው ከወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን፤ ታላቁ የሙዚቃ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ደግሞ ዛሬ የምንመለከተውን የባሕላዊ ሙዚቃ መሠረት የጣለ የመጀመሪያው ባለቅኔ ነው፡፡ ከዚያም ሙዚቃ የሚባለው ጽንሰ ሀሳብ በብዙዎች እየታወቀና ውስጥ ውስጡን እየሰረጸ የባሕላዊ ሙዚቃና ድምጻውያን ተወለዱ። እንደዛሬው ቴክኖሎጂው ባለመኖሩ ሙዚቃዎቹ በቴፕ አሊያም በካሴት ክር የሚቀዱ ሳይሆኑ እንደ አዝማሪያኑ ሁሉ ሥራዎቹ የሚቀርቡት ፊት ለፊት ወይንም ገጽ ለገጽ ነበር። የባሕል ድምጻውያኑ የራሳቸው የሆነ ፈተና ቢኖርባቸውም እንደ አዝማሪያኑ ጉምጉምታው አልበረከተባቸውም። በባሕላዊ የሙዚቃ ታሪክ ሁለተኛው ወሳኝ በር የተከፈተው በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ሲሆን በዚህች በር የገባው የመጀመሪያው ሙዚቀኛ ደግሞ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ነበር። ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ በሀገረ ጀርመን ሳለ አንድ የጀርመን የሙዚቃ ካምፓኒ ሙዚቃዎቹን በሸክላ ሊቀርጽለት እንደሚፈልግ ነገረው። እሱም በሀሳቡ በመስማማት ዘለሰኛን ጨምሮ 17 ያህል ልዩ ልዩ ይዘት ያላቸው ሥራዎቹ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሸክላ ታተሙ።

ከአራተኛው ክፍለ ዘመን በፊትም ሆነ በኋላ በሙዚቃ ሐረግ በቅሎ ዛሬም በ21ኛውም ክፍለ ዘመን ያለ አንድ ግዙፍ የሙዚቃ ግንድ አለ። ይሄውም አዝማሪነት ነው። ባሕላዊውም ሆነ ዘመናዊው ሙዚቃ የበቀለው ከዚሁ ከአዝማሪያኑ ግንድ ላይ ነው። ዘመናዊውን የሙዚቃ ዓለም በማስተዋወቅ ነጮቹ ቢቀድሙም በሙዚቃ ዓለም በመኖር ግን አዝማሪዎቻችንን የሚቀድም አልነበረም። ጥበብም እንደ አምላክ የተናቁትንና ትንንሾቹን መረጠች። ካልጠፋ መንደር ሁሉ በአዝማሪዎቹ መንደር ማደርን ሽታ በችግር እራሷን ለቅርቃር አሳልፋ ሰጠች። በሀገራችን፤ የሙዚቃ ጥበብ በአዝማሪያኑ ልብ አድራ በሯን ዘግታ ያለቀሰችበት ዘመነ ሰቆቃ የታሪክ ምዕራፍ እንደነበራት ግልጽ ነው። ያውም አዝማሪነት እስከ ውግዘት የሚል ባለ ብዙ ገጽ ምዕራፍ። የሙዚቃው ናርዶስ የሆነው የመንፈሳዊው ዝማሬ ከወደ ቤተ ክርስቲያን እንደ እጣን ከርቤው የሚያውድ መዓዛ ነበረው። በሌላኛው ወገን ያለው የአዝማሪያኑ ሙዚቃ ግን ቃናው የሚከረፋ ጣዕሙም መራራ ነበር። የሙዚቃ ጥበብና የአዝማሪው ሙዚቃ እንደ ጉድፍና እንደ አጻያፊ ነገር እየታየ ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ ጅራቱ የተቆረጠበት ዘመንም እሩቅ አይደለም። ከወዲህኛው አለፍ ብሎ የነበረው ዘመን ሁለቱንም በቀኝና በግራ ይዞ መልካቸውን ያሳየናል።

በአዝማሪያኑ ዘመነ ሰቆቃ፤ የአባት ለልጅ ትልቁ ምርቃት "ዘማሪ እንጂ አዝማሪ ከመሆን ይጠብቅህ" ነው። አዝማሪ መሆን ጦሱ ለራስ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰብና ለዘመድ አዝማዱም ነው። የእከሌ ልጅ አዝማሪ ሆኖ ዘራችንን አሰደበ ተብሎ ለተግሳጽና ለምክር የሚሰበሰበውን የዘመድ አዝማድ ጉባኤ መመልከት አዝማሪነት ባፍንጫዬ አስብሎ የሚያስበረግግ ቢሆንም፤ አዝማሪና አዝማሪነት ግን ፈጽሞ አልሞቱም። በጊዜው የነበረው አዝማሪነት ከአሁኑ ባህላዊ ሙዚቃ ጋር የበለጠ ቁርኝት ቢኖራቸውም የባህላዊም ሆነ የዘመናዊ ሙዚቃ ውልደታቸው ከዚሁ ከአዝማሪዎቹ መንደር ነው። በዚህኛው ዘመን ሙዚቀኛ መሆን አንገት የሚያስደፋ ሳይሆን ደረት የሚያስነፋ ነው። ለመናገርም የሚያሸማቅቅ ሳይሆን ምነው በጠየቁኝና ቶሎ በነገርኳቸው የሚያስብል ነው። ሙዚቃ በዚያኛው ዘመን ግን፤ በሕግ ያልተደነገገ አንቀጽ አልባ የወንጀለኛ መቅጫ ነበር። ፍርዱም ማሕበረሰባዊና ቤተሰባዊ የሆነ ጥምር የጋራ ውግዘት ነው። አዝማሪነት የተወገዘ በመሆኑ ወደዚህ የሚገባ ሁሉም የተወገዘና የተገለለ ይሆናል። አንዳንዴም አለፍ ብሎ የቅጣት እርከኑ ከፍ ሲል ከቤተሰቡ የልጅነት መዝገብ ላይ የሚያሰርዝ ፍርድን ያስከትላል። ለአንድ አባት ትልቁ ሞት ማለት ልጅህ አዝማሪ ሆነ ወይንም ሆነች ሲባል መስማት ነው። ለእናትም ቢሆን ከዚህ የከፋ ሕመም የለም። "በተከበርኩበት ሀገር አዋረድከኝ...ዘጠኝ ወር በሆዴ ተሸክሜ በእነዚህ ሁለት ጡቶቼ እንዳላሳደኩሽ ዛሬ አንገቴን አስደፋሽኝ...እንደ እከሌ ልጅ ቤልጅግና ምንሽሩን ታጥቀህ...እንደ እከሌ ልጅ የቀለም ቀንድ ሆነህ ስሜን ታስጠራለህ ስል እንዲያው ያንተ መጨረሻ አዝማሪነት ይሁን! ከእንግዲህ ወዲያ አንተም ልጄ እኔም አባትህ አይደለሁም" የተባሉስ ስንቶቹ ናቸው...ዛሬም በሙዚቀኞቹ ዘመን ጥንት የነበረው የጉምጉምታ ወላፈን በረድ፤ ቀዝቀዝ አለ እንጂ ፈጽሞ ግን አልተዳፈነም። ከዚህ ረገድ ሁለት ጽንፍ የያዙ ሙግቶች አሉ። አንደኛው ሙዚቀኞችን በመቃወም ሙዚቃ አይጠቅምም፤ አያስፈልግም በማለት በአራት ነጥብ የሚዘጉ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ሙዚቃ ሕይወት ነው በማለት አስፈላጊነቱን ብቻ ሳይሆን ሀያልነቱንም የሚናገሩ ናቸው። ዛሬ ላይ ሆነው የቀደመውን ጊዜ በመደገፍ ሙዚቃን በሚቃወሙም ሆነ የቀደመውን እየነቀፉ ስለ ታላቅነቱ በሚገልጹት በሁለቱም ሰዎች ዘንድ የራሳቸው የሆነ እውነት አለ። እውነቱም የሚገኘው እራሳቸው ጋር ብቻ ነው።

ጊዜው ገሰገሰ ዘመንም ዘምኖ ቴክኖሎጂን አፈራ። የቴክኖሎጂውን ጽዋ ከቀመሱ የኪነ ጥበብ ልጆች መካከል አንደኛውና ዋነኛው የፊልሙ ኢንዱስትሪ ነው። የፊልሙ አንዱስትሪ ያለቴክኖሎጂ የማይታሰብ ነበር። ውልደቱ ደግሞ ከቴክኖሎጂውም አስቀድሞ የነበረው የቲያትሩ ዓለም ነው። ከ1988 ዓ.ም በፊት በሀገራችን ስለ ፊልም ምንነትም ሆነ ፊልም የሚለውን ነገር ጨርሶ ማንም አያውቀውም ነበር። በ1988 ዓ.ም እስቴቨን የተባለ አንድ የውጭ ዜጋ ወደ አጼ ምኒልክ ጠጋ በማለት ስለነገሩ ምንነት ያጫውታቸዋል። ሁሉንም ቴክኖሎጂ ቀምሶ የማጣጣም ፍላጎታቸው ከፍተኛ የነበረው ንጉሱም እንዲህ ከሆነስ እስቲ እኛም እንየው በማለት ቴክኖሎጂውን ይዞ እንዲመጣ ነገሩት። ግለሰቡም በ1989 ዓ.ም `ቤንሀር` የተሰኘውን ስለክርስቶስ ገድል የሚያሳይ ዘጋቢ ፊልም ለማሳየት የሚረዳውን አንጸባራቂ ቴክኖሎጂ ይዞ ከተፍ አለ። በዚያው ዓመት ሚያዚያ 1 ቀን አጼ ምኒልክን ጨምሮ የቤተ መንግሥቱ ሹማምንትና ቀሳውስት ተሰባስበው ‹አጃኢብ ነው› ሲሉ ፊልሙን ተመለከቱት። ከአንድ ዓመት በኋላም 1890 ዓ.ም አንድ ሲኒማ ቤት ተከፈተ። በጊዜው ወሬው እየተናፈሰ ሕዝቡም ይህን ጉድ ለመመልከት ወደ ሲኒማ ቤቱ ይጎርፍ ጀመረ። መጀመሪያ ላይ ነገሩን በአሜንታ ቢቀበለውም ብዙም ሳይቆይ ግን የሚያየው ነገር ምትሀታዊና የማይጨበጥ እየሆነበት ሲመጣ ጊዜ አዝማሚያው አላምር አለው። ወደኋላ በማፈግፈግ ጉምጉምታውንም ጀመረ። ቤቱንም ``የሰይጣን ቤት`` ሲል ጠራው። ሰውም ከመዝናናት ወደ ፍርሃት ስለገባ ተመልካች ጠፍቶ ቤቱ ተዘጋ። የፊልም ቤቱ ባለቤትም ዕቃውን ለኢጣሊያን ሚኒስቴር ተወካይ ሸጦ ወደ ሀገሩ ገባ።

ከአስፈሪ ጉምጉምታ የተነሳ ሕዝቡ ይህ የፊልም ነገር እንዲያው ምንም አልዋጥልህ ቢለውም፤ ገመዱ ግን ሙሉ ለሙሉ አልተቆረጠም ነበር። ከሲኒማ ቤቱ ደጅ እንደምንም እየተፍገመገመ መጥቶ በሀገራችን የሚሰሩ ፊልሞች ወዳበቡበት 1990ዎቹ መጀመሪያ ደረሰ። ጥቂት አሜንታ ብዙ ጉምጉምታ፤ አሁንም ከፊልሙ አብዮት ጋር ተያይዞ ተነሳ። ከቴሌቪዥን የመስኮት ስርጭት አልፈው በዲስክና በሲዲ ወደየቤቱ መግባት ሲጀምሩ ደግሞ ውስብስብነቱ እየጨመረ በወጣቱና በአዛውንቱ፣ በታችኛውና በላይኛው ክፍል የአመለካከት ልዩነትን ፈጠረ። የታችኛው ክፍል በተለይ ደግሞ የወጣቱ ክፍል ወደዚህ እየተሳበ መሄዱን በጨመረ ቁጥር የላይኛው ክፍል ደግሞ አንድ እግሩን በእጁ እየጎተተ ለማስጣል ቢሞክርም የማይቻለው ነበር። እንደዛሬው ቤተሰብ ተሰባስቦ ሲኒማ ሲመለከት ማየት ከተአምር የማይተናነስ ምትሀት ነበር። ገንዘብ እያስከፈሉ ፊልሞችን ያሳዩ የነበሩ ፊልም ቤቶች በማሕበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ምስል ልክ እንደያኔው የሰይጣን ቤት ነበር ። ሲኒማ ቤት ሳይሆን የብልሽት ክትባት የሚሰጥበት የመጥፊያ ካምፕ ተደርገው ነበር የሚቆጠሩት። በርግጥም በከፊል መሆናቸው አልቀረም ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ የወላጆቹን ከቤት አለመኖር እየጠበቀ ለሁለትና ለሶስት ሰዓታት ፊልሙን ተከራይቶ የሚያየውም ልጅ አንድ አይኑን ከቴሌቪዥን መስኮት፤ አንድ አይኑን ከቤቱ በር ተክሎ ነበር የሚመለከተው። ነገሩ የአይጥና የድመት ጨዋታ ነበር የሚመስለው። ፊልም ማየት የዱርዬነት፤ አለማየትም የጨዋነት መለኪያ ተደርጎ መቆጠሩም አልቀረም። ወላጅ የልጁ አመል አስቸጋሪ የሆነበት እንደሆን "ይሄው ይሄን ፊልም የሚሉት ጂኒ ማየት ከጀመረ ወዲህ ጸባዩ ሁሉ ብልሽትሽት አለ" ሲል አመለሸጋው ልጅም ቁጭ ብሎ ፊልሙን ሲኮመኩም ድንገት የደረሰበት ጎረቤት ``አሄ... ትልቁ ዳቦ ሊጥ`` በማለት ተርቶ ይሄዳል።

በእነዚህ ሁሉ ነገሮች ውስጥ የማሕበረሰቡ በአሜንታ የመቀበል ፍላጎቱ ምንም እንኳን ዝቅተኛ ቢሆንም፤ ለመውቀስ የሚያስደፍር አንዳችም ምክንያት ግን የለም። ማሕበረሰባችን በሀይማኖቱ ታፍሮ በባህሉ ተከብሮ የሚኖር ሕዝብ በመሆኑ የሚሆነው ሁሉ ትውልዱ ከዚህ ማንነት እንዳያፈተልክ በመስጋት እንጂ በኋላ ቀርነት ተሸብቦ አይደለም። ነገር ግን በስጋት የበቀለውን ጉምጉምታ በእውቀት ላይ በቆመ አሜንታ መቀየር ይቻላል። አውቆ በመናገር ጠርጥሮ በመብላት ላይ የተመሠረተ የኪነ ጥበብ ዓለም የግድ ነው። በሙዚቃውም ሆነ በፊልሙ፤ በአሜንታና በጉምጉምታ እንደ አፋር ስምጥ ሸለቆ ለሁለት የተከፈለውን የሀገራችንን የኪነ ጥበብ ምድር አንዳች ስበትን ፈጥረን ወደ አንድ ማምጣት የምንችለው፤ የማሕበረሰባችንን የልብ ትርታ በመጨመር ሳይሆን በማድመጥ ነው።

መርፌን ካወቅህበት የወጋህን እሾህ ትነቅልበታለህ፤ ካላወክበት ግን የባሰውን እራስህን ወግተህ ታደማበታለህ። ኪነ ጥበብም ካወቅንበት መዳኛ ካላወቅንበት መጥፊያችን ለመሆን የሚያግደው አንዳችም ነገር የለም። ለአሜንታችንም ሆነ ለጉምጉምታችን በእውቀት ላይ የተመሠረተ ምክንያታዊነት ያስፈልገናል። ጉዳዩ ያለው ከአያያዛችን ላይ እንጂ የትኛውንም የኪነ ጥበብ ዘርፍ ከመቀበልና ካለመቀበል ጋር መሆን የለበትም። የተጠቀሙበት ሀገርና ባህላቸውን አሳድገዋል። አንዳንዶች ደግሞ `ከበሮ ሲያዩት ያምር ሲይዙት ያደናግር` አይነት ሆኖባቸው፤ማንነታቸውን ያጡበት እንደሆነም አይተንበታል። ቀድሞውኑ የኛ የሆኑትን ነገሮች ወስደው ለወዙ ከቅባቱ ደፋፍተው የራሳቸው እንደሆነ ነገር በኩራት ለኛው መልሰው ሲሰጡን፤ የፈረንጅ እያልን የተቀበልነው ስንቱን ነው? የኛ ለኛ የሆነውን ማየት ተስኖን በማይገባን ነገር የሚገባንን አጥተናል። ባህልና ኪነ ጥበብ ወደ አንዲት ሀገር የሕልውና ባህር በእኩል የሚፈሱ ገባር ወንዞች ናቸው። የአንዱ መድረቅ ሌላውን ያደርቃል፤ የአንደኛው መደፍረስም ሌላኛውን ያደፈርሳል። ባህልን ገሎ ኪነ ጥበብን ለማዳን፤ አሊያም ኪነ ጥበብን ገድሎ ባህልን ለማዳን መሞከር ዶሮዋን አርዶ እንቁላልዋን እንደመጠበቅ ነውና አንዱ ያለ አንዱ የማይገኝ መሆኑን መረዳት የመክፈቻው ቁልፍ ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ‹‹ከሚጥል ሕመም›› ጋር የሚደረግ ትግል

እዮሩስ ተስፋዬ



ራሄል ሞገስ ትባላለች። በተለምዶ ‹የሚጥል ሕመም› ተብሎ በሚጠራው ሕመም ከተያዘች ፲፩ ዓመት ሆኗታል። በሳይንሳዊ መጠሪያው ኢፕሊፕሲ ተብሎ የሚታወቀው ይህ የሚጥል ሕመም ሕክምና እንዳለው በመገንዘቧ ክትትሏን የጀመረችው በቶሎ ነበር። ‹‹አንዳንድ ሠዎች ርኩስ መንፈስ ነው። ርግማን ነው ይበሉ እንጂ የሚጥል ሕመም እንደሌሎቹ የጤና ችግሮች ነው። ሕክምናና መድኃኒትም አለው።›› የምትለው ራሄል፤ የታዘዘላትን መድኃኒት በአግባቡ በመውሰዷ አሁን ላይ ሕመሟን ተቆጣጥራዋለች። ይህም ብዙ ለውጦችን በራሷ ላይ እንድታይ አስችሏታል። በአካውንቲንግ ተመርቃም በአሁን ወቅት በሽያጭ ሠራተኛነት ሕይወትዋን እየመራች እንደምትገኝ ታስረዳለች።

ራሄል ከህመሙ ጋር በነዚያ ፲፩ ዓመታት ውስጥ ብዙ ፈተናዎችን አሳልፋለች። ከዚህ ቀደም ተቀጥራ በሠራችባቸው ቦታዎች ብዙ ፈተናዎች ገጥሟታል። በህመሟ ምክንያት ስትወድቅ ‹‹ባንቺ ምክንያት ገበያ ተመልሷል።›› ተብላለች። አንዳንድ አሠሪዎቿም ፈቃድ ይከለክሏታል። ችግሯንም አልተረዱላትም ነበር። ‹‹ብዙ ፈተናዎች ይኑሩ እንጂ ዋናው በጥንካሬ ማለፍ ነው።›› ትላለች።

‹‹መውደቅ ለእኔ የሆነ የታወከ ነገር በአምስት ደቂቃ ውስጥ ሲስተካከል ማለት ነው።›› ስትል ይህን የጤና ችግር የምትገልፀው ራሄል፤ ሌሎች ታማሚዎች መድኃኒታቸውን በሰዓት ከወሰዱ፣ ክትትላቸውን በሚገባ ካደረጉ፣ ራሳቸውን ከጭንቀት ካራቁ ብሎም የሕክምና ባለሙያዎች የሚሏቸውን ከሰሙ ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ ልምዷን ታጋራለች።

አቶ ዐቢይ አስራት በኬር ኢፕሊብሲ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። ማዕከሉ ከተመሰረተ ስምንት ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን፤ በነዚህ ዓመታት ውስጥ የሚጥል ህመም (ኢፕሊብሲ) በኅብረተሰቡ በኩል የሚፈለገውን ያህል እንኳን ባይሆን የተሻለ አመለካከት እንዳለው ያወሳሉ። ማዕከሉ ግንዛቤ ከመስጠት በተጨማሪ የሚጥል ሕመም ላለባቸው ታማሚዎች የተሻለ የሕክምና ዕድል ኖሯቸው አገልግሎት እንዲያገኙ እና መድኃኒቶቹም እንደልብ የሚገኙ ባለመሆናቸው ለታማሚዎች በሚገባ እንዲደርሱ ለማድረግ ዓላማ አድርጎ እየሠራ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም በማዕከሉ ውስጥ የሕክምና አገልግሎት እንዲደረግላቸው ማድረግን ያካተተ ሲሆን፤ በወር አንዴ ነጻ የሕክምና አገልግሎት ይሰጣል።

እንደ አቶ ዐቢይ ገለፃ፤ በማዕከሉ አንድ ሺህ የሚሆኑ አባላት ያሉ ሲሆን፤ ለአባላቱ በጎ ፈቃደኛ የሆኑ ኒውሮሎጂስቶች (የነርቭ ስፔሻሊስቶች) ሕክምና እንዲያገኙ ይደረጋል። በኢትዮጵያ ያለው የኒውሮሎጂ ባለሙያ ቁጥር አናሳ በመሆኑ ለሚሊዮን ሕዝብ መድረስ አይችሉም። በተለይም የሕጻናት ኒውሮሊጂስት ቁጥራቸው ከአምስት የማይበልጥ ቢሆኑም የተሻለ ሕክምና ሕፃናትን ጨምሮ ለአዋቂዎችም እንዲያገኙ ይደረጋል።

ከዚህ ጎን ለጎንም የሚጥል ሕመም ያለበት ሠው፤ ሕመሙ ያለበትን ደረጃ ሊገልጽ የሚችል እና ከየትኛው አንጎል ክፍል ነው የሚነሳው ብሎ የሚለካ ማሽን በማዕከሉ የሚገኝ ሲሆን፤ ታማሚዎቹ ነጻ ምርመራ እንዲያገኙ ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪም የኤም አርአይ ምርመራ ከዲያግኖስቲክ ማዕከላት ጋር በመነጋገር በነጻ እንዲያገኙ ሁኔታችን ያመቻቻል። ከሕክምናው በተጨማሪም መድኃኒቶቹ እንደልብ የሚገኙ ባለመሆናቸው እና አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ዋጋቸው ውድ መሆኑን ተከትሎ አቅም ለሌላቸው ታማሚዎች ማዕከሉ መድኃኒቱን በመግዛት ይሠጣል። ዓመታዊ የጤና መድህን ክፍያ በመክፈል እገዛ ያደርጋል።

ሲስተር ሜሮን ሽመልስ በኬር ኢፕሊብሲ ኢትዮጵያ በማኅበረሰባዊ ግንኙነት ታማሚዎችን በማየት እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በማዕከሉ ትሰጣለች። እንደ እርሷ ገለፃ፤ አብዛኛው የሚጥል ሕመም ያለበት ሠው ሕመሙ ምን እንደሆነ ግንዛቤው የለውም ። እንደውም ‹‹እንደ ልክፍት ወይም አውድቅ ይዞኛል›› የሚል አመለካከት ነው ያለው። ገና ወደ ማዕከሉ ሲመጡ ይድናል የሚል ተስፋም የላቸውም። ይህንን ተከልትሎም ማዕከሉ የሕክምና ድጋፍ እንዲያገኙ፣ ሕመሙን መቆጣጠር እና መዳን እንደሚችሉ ግንዛቤ ይሰጣል።

ሌላው በማዕከሉ ለታማሚዎች የሥነ ልቦና ድጋፍ ስለሚደረግላቸው ሥራ አግኝተው አግብተው ወልደው ሕይወታቸውን እየመሩ ያሉ ብዙ ናቸው የምትለው ሲስተር ሜሮን ሽመልስ፤ በተለይም ዘወትር ረቡዕ የሚሠጠው የምክር አገልግሎት (የቡና ጠጡ ፕሮግራም) ቋሚ መሆኑን ታስረዳለች። በዚህም የህመሙ መንስኤ ምንድነው? እንዴት እንቆጣጠረው? የሚለውን ጨምሮ ለወደፊት ሕይወታቸው የሚያግዛቸው ምክር ይሰጣል።

እንደ ሲስተር ሜሮን ገለፃ፤ ሁለት ዓይነት የሚጥል ሕመም አለ። አንደኛው ጄነራል ሲዢር የሚባለው በአንጎል ግራ እና ቀኝ በኩል የነርቭ ሴሎች በአንድ ጊዜ እኩል የሆነ የኤሌክትሪክ ንዝረት ወደ መላው የአንጎል ክፍል የሚረጭ ሲሆን፤ ምልክቶቹም ወድቆ መንቀጥቀጥ፣ አረፋ መድፈቅ ፣ አልፎ አልፎ ሰገራ እና ሽንት መልቀቅ ያጋጥማል። ሁለተኛው ደግሞ ፎካል ሲዢር ነው። ይህም ከአንጎል ክፍል የሚጀምር ወደ ሌላ የአንጎል ክፍል የማይሰራጭ ሲሆን ፤ አካላዊ እና ስሜታዊ ተፅዕኖዎችን ያስከትላል። ምልክቶቹም ለተወሰነ ሰከንድ የሰውነት ክፍል መድረቅ፣ድንገተኛ የመረበሽ ስሜት እና መሰል ምልክቶች ናቸው። በመሆኑም በዚህ ጊዜ መደረግ ያለበት የእርዳታም ይሁን የጥንቃቄ መረጃ እንዲኖራቸው ይደረጋል።

‹‹የሚጥል ሕመም በንክኪ አይተላፍም። ከሌላ አእምሮ ሕመም ጋር የማይያዝ መሆኑን ሠዎች ሊረዱት ይገባል። ልክ እንደማንኛውም የነርቭ ሕመም ሕመም ነው። በቂ ሕክምና፤ በቂ መደኃኒት አለው። ስለዚህም ሀኪም አቁሙ እስኪል ድረስ መድኃኒቱን በሚገባ መውሰድ ያስፈልጋል።›› በማለት ሲስተር ሜሮን ሙያዊ ምክራን ገልፃለች።

በሚጥል ሕመም ብዙ ችግሮች የደረሰባት ራሄል አሁን ላይ ሠርታ ትገባለች። ልምዷንም ወደ ማዕከሉ ለሚመጡ አባላት ታካፍላለች። ሕብረተሰቡም እንደ ማንኛውም ሕመም ሕክምና እንዳለው ማወቅ ይኖርበታል ባይ ናት። የሚጥል ሕመም ኖሮባቸው ከቤታቸው ያልወጡ ይኖራሉ። ስለዚህም ልጆቹን ቤት ቆልፎ ከማስቀመጥ ይልቅ ወደ ሕክምና እንዲሄዱ፣ መድኃኒታቸውን በአግባቡ እንዲወስዱ፣ ትምህርት እንዲማሩ፣ ሥራ እንዲሠሩ ማድረግ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ቤተሰብም እራሱን ማሰር የለበትም በማለት ትመክራለች።

‹‹ለሚጥል ሕመም በተለምዶ ክብሪት ማጨስ፣ ውሃ መስጠት፣ እንጨት እንዲነክሱ ማድረግ እና መሰል ድርጊቶች የሰዎችን ሕይወት እስከማሳጣት ይደርሳል›› ያሉት አቶ ዐቢይ፤ ስለዚህም ማዕከሉ የግንዛቤ ሥራዎችን በሥፋት እንደሚሰራበት ይገልጻሉ። ሌላው የሚጥል ሕመም ምን ሰዓት ላይ እንደሚነሳ ባለመታወቁ ለታማሚዎች የማይደገፉ ሥራዎች መኖራቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። ለአብነትም መኪና ማሽከርከር፣ አብዝቶ እሳት አጠገብ ከሚሠሩ ሥራዎች፣ በማሽን በመታገዝ ከሚሠሩ ሥራዎች ራሳቸውን ማራቅ ይኖርባቸዋል።

ማዕከሉ ለወደፊት ብዙ ራዕይ እንዳለው የሚገልጹት ሥራ አስኪያጁ፤ የመድኃኒት እጥረት፣ ማዕከሉ በኪራይ ቤት አገልግሎት ለመስጠት መገደዱ እና ድጋፎችን እንደልብ አለመገኘቱም ሥራቸውን ፈታኝ እንዳደረጉ ያስረዳሉ። አያይዘውም የኢትዮጵያ የነርቭ ሕክምና ማህበር እና ሌሎችም ለሚያደርጉት የበጎ አድራጎት ድጋፍ በማመስገን የመድኃኒት አምራቾች እና አቅራቢ ድርጅቶች ድጋፋቸውን እንዲያደርጉም ጠይቀዋል።

# ዓለም አቀፍ

## የአሜሪካ ምክር ቤት በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ አፈ ጉባኤውን ከኃላፊነት አነሳ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአሜሪካ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ አፈ ጉባኤውን የመተማመኛ ድምጽ በመንፈግ ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ አደረገ።

የአፈ ጉባኤነት መንበሩን ከተረከቡ አንድ ዓመት ያልሞላቸው የካሊፎርኒያ ተወካይ የምክር ቤት አባል ኬቨን ማካርቲ ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ምክር ቤቱ የወሰነው 216 ለ 210 በሆነ የድምጽ ብልጫ ነው።

ሪፐብሊካኑ አፈ ጉባኤ ማካርቲ እንዲነሱ ተቃውሞ የተቀሰቀሰው ባለፈው ሳምንት የአሜሪካ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲዘጉ ሊያደርግ የነበረውን የበጀት ጉዳይ ለማስተካከል ከዲሞክራቶች ጋር ስምምነት በመድረሳቸው ነው።

የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ አጋር የሆኑት የፍሎሪዳው እንደራሴ ማት ጊትዝ ናቸው አፈጉባኤው እንዲነሱ ያደረገውን የምክር ቤቱን የአሰራር ሂደት ሰኞ ዕለት እንዲጀመር ያስደረጉት።

አፈ ጉባኤው የአሜሪካ መንግሥት ተቋማት በከፊል እንዲዘጉ ሊያደርግ የሚችለውን የበጀት እክል ለማስቀረት ድርድር በሚደረግበት ጊዜ በምስጢር ከዋይት ሐውስ ባለሥልጣናት ጋር ለዩክሬን የሚደረገው ድጋፍ እንዲቀጥል ተስማምተዋል በሚል ነው የተከሰሱት። ኬቨን ማካርቲ ግን ይህንን ያስተባብላሉ።

ማካርቲ ክሱን ያቀረቡባቸው ተቀናቃኛቸውን ማት ጊትዝን "ትኩረትን የሚሻ" ሲሉ የወረፏቸው ሲሆን፣ ክሱ በእሳቸው ላይ ያነጣጠረ ግለሰባዊ እንጂ "ከመንግሥት ውጪ ጋር የሚያያይዘው ነገር የለም" ብለዋል።

ኬቨን ማካርቲ በአሜሪካ መንግሥት ውስጥ ከፕሬዚዳንቱ እና ከምክትላቸው ቀጥሎ ትልቁ ሥልጣን



የሆነውን የምክር ቤት አፈ ጉባኤነት ቦታ የያዙት ከተደጋጋሚ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት በኋላ ባለፈው ዓመት ጥር ላይ ነበር።

የአፈ ጉባኤውን ከሥልጣን መነሳት ተከትሎ ከዋይት ሐውስ የወጣው መግለጫ እንዳለው፣ "አገራችን የገጠሟት ተግዳሮቶች ጊዜ የሚሰጣቸው ባለመሆናቸው" ምክር ቤቱ በአስቸኳይ አዲስ አፈ ጉባኤ ይመርጣል የሚል ተስፋ እንዳላቸው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ተናግረዋል።

ማካርቲን ከመንበራቸው ያስነሳቸው የምክር ቤቱ የአሰራር ደንብ ባለፉት ዘመናት በአፈጉባኤ ላይ ተግባራዊ የተደረገው ለሁለት ጊዜ ሲሆን፣ ነገርግን አፈ ጉባኤዎቹን ለማንሳት በቂ ድጋፍ ባለማግኘታቸው የተሳኩ አልነበረም።

አሁን ግን በአሜሪካ የአፈ ጉባኤነት መንበር ላይ ላለፉት ዘጠኝ ወራት ብቻ የቆዩትን ኬቨን ማካርቲን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማስነሳት አስችሏል።

ተሰናባቹን አፈ ጉባኤን በመተካት ምክር ቤቱን ማን ሊመራ ይችላል የሚለውን በተመለከተ ግልጽ የሆነ ወይም ተገማች ዕጩ አስካሁን አልታወቀም።

## ኢሊምፒክን የምታስተናግደው ፓሪስ የተባይ ወረርሽኝ ስጋት ተደቅኖባታል

በጋዜጣው ሪፖርተር

ፓሪስን ጨምሮ በተለያዩ የፈረንሳይ ክፍሎች የተከሰተው የትኋን ወረርሽኝ አገሪቱ በቀጣይ የአውሮፓውያን ዓመት በምታስተናግደው የኦሊምፒክ ጨዋታዎች ላይ የጤና እና የደኅንነት ጥያቄን አስከትሏል።

በማርሴይ ዋና ሆስፒታል ኢንቶሞሎጂስት የሆኑት ዢን ሚሼል በረንገ በሞቃታማ ወራት የትኋኖች ቁጥር በጣም ሲጨምር እናያለን። ዋናው ምክንያት ደግሞ ሰዎች በሐምሌና በነሐሴ ወራት ከሚያደርጉት ጉዞ በኋላ ትኋኖቹን በሻንጣቸው ይዘው ስለሚመለሱ ነው ብለዋል።

አክለውም በዚህ ዓመት የታየው የተባዮቹ ወረርሽኝ መጨመር ካለፈው የበለጠ ይሆናል ሲሉ አመልክተዋል። ባቡር ላይም በትኋኖች ተነከስን የሚሉ ስሞታዎች በዝተዋል።

የፓሪስ ማዘጋጃ ቤትና የፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን አስተዳደር የትኋን ወረርሽኙን ለመቆጣጠር የሚያስችል ርምጃ እንዲወስዱ ጥያቄ እየቀረበላቸው ነው።

የሚወሰደው ርምጃም ከወራት በኋላ ከሚካሄደው የ2024ቱ የፓሪስ ኦሊምፒክ በፊት ጉዳዩን ምን ያህል በትኩረት እንደሚመለከቱትና የፓሪስን ገጽታ እንዴት እንደሚጠብቁ የሚታይበት አጋጣሚም ነው ተብሏል።

የተባዮቹን ወረርሽኝ በተመለከተ አስፈሪ ታሪኮች በበይነመረብ ላይ በፍጥነት እየተሰራጩ ጉዳዩን ወደ ብሔራዊ የአስቸኳይ ጊዜ አደጋነት እየቀየሩት ነው።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ትኋኖች በዲዲቲ



ምክንያት ቁጥራቸው ቀንሷል። አሁን ያሉት ትኋኖች ደግሞ በጊዜ ሂደት ዲዲቲን የበለጠ መቋቋም የሚችሉ ሆነዋል።

በረሮዎች ትኋኖችን ይመገባሉ። በዘመናዊ ኑሮ መስፋፋት ምክንያት በረሮዎች ቁጥራቸው ቀንሷል። ይህም ለትኋኖች ቁጥር መጨመር ሌላው ምክንያት እንደሆነ ይታመናል።

ትኋኖች አደጋ ያስከትላሉ። ይህ አደጋ ግን ከአካላዊነቱ ይልቅ ሥነ ልቦናዊ ነው። ንክሻቸው ቢያምም ብዙ አይቆይም። በሽታም አያስተላልፉም ይላሉ ባለሙያዎች።

አንዳንዶች አንድ ጊዜ ትኋን አልጋቸው ላይ በማየታቸው ብቻ ለመተኛት ይቸገራሉ። በእኔ ዕይታ ትኋኖችን ለማስወገድ ሁሉም ላይ ከማነጣጠር ዋናዎቹ አሰራጮች ላይ ትኩረት ማድረግ ተገቢ ነው በማለት ኢንቶሞሎጂስቱ ይመክራሉ።

# ስፖርት



## ‹‹የውድድር ዓመቱ ስኬታማ ነበር››

**- ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ**



ብርሃን ፈይሳ

የዓለም አትሌቲክስ በዓመቱ ለማከናወን ያቀዳቸውን ዓለም አቀፍ የውድድር መርሐ ግብሮቹን አጠናቋል።በነዚህ ውድድሮች ምርጥ አቋም ያሳዩ አትሌቶችንና ሌሎች ባለሙያዎችን ወደመሸለምም እየተንደረደረ ይገኛል።የዓለም ሀገር አቋራጭ ቻምፒዮና፣ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና እና የዓለም የጎዳና ላይ ቻምፒዮና በዓመቱ የተደረጉ ዋና ዋና ውድድሮች ሲሆኑ፤ እንደ ዳይመንድ ሊግ፣ የቤት ውስጥን ጨምሮ ሌሎች የዙር ውድድሮችም መከናወናቸው ይታወቃል።

ኢትዮጵያ በእነዚህ ውድድሮች ላይ አትሌቶቿን በማሳተፍ ስኬታማ የውድድር ዓመት አሳልፋለች።ይህም እንደ አጠቃላይ ሲታይ መልካም የሚባሉ ውጤቶች የታዩበት፣ ለቀጣዩ 2024 የፓሪስ ኦሊምፒክም ደካማና ጠንካራ ጎኖች የተለዩበት ነው።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉም ዓመቱ 90 ከመቶ ስኬታማ ሊባል የሚችል ሆኖ ማለፉን ትናገራለች።ውድድሮች መብዛታቸው ለአትሌቶችም ሆነ በስፖርቱ ስመጥር ለሆኑ ሀገራት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።ባለፉት ዓመታት በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ውድድሮች ተሰርዘዋል፣ አዘጋጅ ሀገራትም ተቀያይረዋል፣ እንዲሁም የመርሐ ግብሮች መሸጋሸግ፣ መዘበራረቅና መደራረብ ተፈጥሯል።ይህ ዓመት በአንጻራዊነት ሲታይ ግን ውድድሮች ወደነበሩበት የተመለሱበት ነበር፡፡

ከወር በፊት በቡዳፔስት በተካሄደው የዓለም ቻምፒዮና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከአሪጎን የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ ቢያቅድም በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ በተጠበቁ ውድድሮች ውጤት አልተገኘም።ያም ሆኖ በሴት አትሌቶች የተመዘገቡ ውጤቶች የውድድር ዓመቱን ስኬታማ እንዲሆን ትልቅ አስተዋፅኦ እንደነበረው ደራርቱ ታብራራለች።ይህም ተመሳሳይ የአየር ሁኔታ ለሚኖረው የፓሪሱ ኦሊምፒክም ትምህርት የሰጠና ተገቢውን ዝግጅት ያመላከተ ነበር።ከቀናት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ በላቲቪያ ሪጋ በተካሄደው የጎዳና ላይ ቻምፒዮናም መልካም የሚባል ውጤት በማስመዝገብ የውድድር ዓመቱ መጠናቀቁን አብራርታለች።

ይህንን ተከትሎም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሀገር ውስጥ የውድድር መርሐ ግብሮቹን በመጪው የጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም የሚጀምር ሲሆን፤ ጠቅላላ ጉባኤውንም በተመሳሳይ ያካሂዳል።በቀጣዩ የፈረንጆቹ የውድድር ዓመት የሚካሄዱ ዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚደረጉ ዝግጅቶችም በዚያው የሚቀጥሉ ይሆናል።በመሆኑም በተጠናቀቀው ዓመት መልካም ውጤት የተገኘ ባቸውን በማጠናከር እንዲሁም ውጤት የታጣባቸው ላይ ትኩረት በማድረግ በዋነኛነት የፓሪሱን ኦሊምፒክ ያለመ ዝግጅት እንደሚደረግም ገልፃለች።

በሌላ በኩል በዓመቱ በአራት አትሌቶች (ለሜቻ ግርማ፣ ጉዳፍ ጸጋይ፣ ትዕግስት ግርማ እንዲሁም ድርቤ ወልተጂ)የዓለም ክብረወሰኖች የተሻሻሉበትም እንደነበር ያስታወሰችው ደራርቱ፣ ለዚህ ውጤት ድርሻ የነበራቸው አካላት ሁሉ ሊመሰገኑ ይገባል ትላለች።ምክንያቱም ፌዴሬሽኑ እንደ ቀድሞ ብሄራዊ አትሌቶች የሌሉትና እገዛም የማያደርግ እንደመሆኑ አትሌቶች በጥረታቸው ያስመዘገቡት ነው።በመሆኑም በተለያዩ የዓለም ሀገራት በተለያዩ ውድድሮች ላይ ባንዲራዋን ከፍ ያደረጉና የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ የገነቡ አትሌቶች ሊመሰገኑ ይገባል።

እንደ ደራርቱ ማብራሪያ፣ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ዝግጅት እንዲሁም ሽልማት ፌዴሬሽኑ በራሱ ከሚያደርገው ባለፈ በመንግሥት በኩልም እገዛ ይደረግለታል።በተለያዩ ውድድሮች ውጤት ላመጡ አትሌቶች የመሬት ሽልማት ሲሰጥ ቢቆይም በቡዳፔስት ዓለም ቻምፒዮና ለተካፈሉት ግን አልተሰጠም።በሌላ በኩል ለውጤቱ ከፍተኛውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉት አሰልጣኞች በእኩል አይን አይታዩም።በዚህም ምክንያት ባለፈው ዓመት ብቻ ወደ 7 የሚሆኑ አሰልጣኞች በውጪ ሀገራት ቀርተዋል።አሰልጣኝ ከሌለ አትሌት አይኖርምና በመንግሥት በኩል እኩል ሽልማትና ዕውቅና እንዲሰጥ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመኖሪያ ቤት መገንቢያ የመሬት ሽልማት በዓለም ቻምፒዮናው ውጤት ላስመዘገቡ እንዲሁም ክብረወሰን ለሰበሩ አትሌቶች እንዲሰጥም ጠይቃለች።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ በ70 ዓመት ታሪኩ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የለውም። አትሌቶች ለሀገራቸው ሜዳሊያ የሚያስመዘግቡትም ሆነ ክብረወሰኖችን የሚያሻሽሉት በተመቻቸ የማዘውተሪያ ስፍራ ተዘጋጅተው አይደለም። በመሆኑም ፌዴሬሽኑ የመለማመጃ እንዲሁም የውድድር ቦታን ያካተተ ሁለገብ የአትሌቲክስ ማዕከል እንዲገነባ ለመንግሥትም ጥያቄ ሲያቀርብ ቆይቷል።ከሩጫ ባለፈ የሜዳ ተግባራት ላይም ውጤት እንዳይገኝ አንዱ መሰናክል በቂ የመለማመጃ ቦታ አለመኖር ነው።በመሆኑም እንደ ጎረቤት ሀገር ኬንያ ሁሉ በተለያዩ የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ ተካፋይና ውጤታማ ለመሆን እንዲቻል ጥያቄው በመንግሥት በኩል አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኝ ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ ጥሪዋን አቅርባለች።


# ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር WWC 02/2016

**ለተለያዩ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውል መለዋወጫዎችን የብየዳ ቁሳቁሶችን እና ግብዓቶችን ግዥ ለመግዛት የወጣ ሀገር አቀፍ ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ**

የውሃ ሥራዎች ኮርፖሬሽን በ2016 በጀት ዓመት ለቀላልና ከባድ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ፤ ISUZU ፣ Mercedes-Benz፣ Beiben lew bed ፣ New Sino Trucks ፣ Ferd፣ Baion ፣ Grusher ፣ Belt with Nut፣ Grinding dise፣ Cutting disc፤ SINO TRUCK ፣ SINO HIGH BED ፤ የተለያዩ Workshop Censumable materials ፤ የተለያዩ Body and Welding Shop materials ፤ Excavator XGMA ፤ Wheel Leader Mode) ማለትም የተለያዩ ኤሌክትሮድ እና የተለያዩ መለዋወጫ ዓይነቶችን ሕጋዊ አቅራቢ ድርጅቶች በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል። በመሆኑም በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የሚከተሉትን ሕጋዊ ሁኔታዎች በማሟላት መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. በዘርፉ ለዘመኑ የታደሰ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድና የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር ያላቸው፤ የዘመኑን ግብር አጠቃለው የከፈሉ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑና የተ.እ. ታክስ ምዝገባ ቁጥር ፤ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (TIN No) እና የቫት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላቸው መሆን አለበት። ተጫራቾች እነዚህንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ኮፒ በማድረግ በጀርባው ፊርማና ማህተም በማድረግ በመጫረቻ ሰነዳቸው ላይ ማካተት ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች ለተጠየቁት የመለዋወጫና ግብዓቶች ግዥ ዋጋ ሲሰጡ ስርዝ ድልዝ መሆን የለበትም። ስርዝ ድልዝ በዋጋ ማቅረቢያ ላይ ከተገኘ ከውድድር ውጭ ያስደርጋል፡፡ በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሱትን እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ኦርጅናል እና ኮፒ በማድረግ በመጫረቻ ሰነዳቸው ላይ ማካተት ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. የሚቀርበው የዋጋ ማቅረቢያ ሕጋዊ የድርጅቱ ተወካይ ስም ፊርማና ማህተም መጠቀም ይኖርባቸዋል።
4. ተጫራቾች በውሃ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ስም የተሠራ/ የተዘጋጀ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በሲፒኦ ወይም ያለቅድመ ሁኔታ እንደተጠየቀ ወዲያውኑ የሚከፈል /Unconditional Bid bond/ በማሠራት በባንክ የተረጋገጠ ለጨረታ ማስከበሪያ የሚውል 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ ብር) ማስያዝ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች በዋጋ መሙያ ሠንጠረዡ ለተገለጹት መለዋወጫዎች እና ግብዓቶች የሚያቀርቡት ማስረጃዎችና የሚሞሉትን ዋጋ ኦርጅናል እና ኮፒ ቴክኒካል ስፔስፊኬሽን በተናጠል ከሚያሳይ ብሮሸር ጋር ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. ተጫራቾች በሚያቀርቡት የጨረታ ሰነድ ላይ የማቅረቢያ ጊዜያቸውን ውል በተያዘ ቢበዛ 60 ቀናት ውስጥ ማቅረብ የሚችል በግልጽ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡
7. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሃሳባቸውን ማለትም የቴክኒክ ፋይናንሻል ሰነዳቸውን ለየብቻ በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ኮፒ እና ኦርጅናል በማድረግ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 20 ቀናት ውስጥ የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን ባሕር ዳር ከተማ ከሚገኘው ዋና መ/ቤታችን ውሃ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ቢሮ ቁጥር 32 በመቅረብ ለጨረታው በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
8. ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ20ኛው ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ ቀን 8፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ የሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል፡፡
9. አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ውል መፈረም ይኖርበታል፡፡
10. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም በዘርፉ የተሰማራ ሕጋዊ ድርጅት የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 300/ሦስት መቶ ብር ብቻ/ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካውንት ቁጥር 1000265163223 በመክፈል ባህርዳር ከተማ ቀበሌ 14 በሚገኘው የድርጅቱ ህንፃ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 32 በመምጣት መግዛት ይችላሉ፡፡
11. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ይህንንም በሚያደርግበት ጊዜ በድርጅቱ የማስታወቂያ መለጠፊያ ቦርድ እና በደብዳቤ ለተጫራቾች ያሳውቃል ግን ተጫራቾች ደብዳቤያቸውን እንዲወስዱ በስልክ አድራሻቸው ተነግረው ካልወሰዱ እንደወሰዱ ይቆጠራል፤
12. ተጫራቾች ተወዳድረው ያሸነፉበትን ዕቃ ናሙና እንዲያቀርቡ በተጠየቁ ጊዜ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።
13. ተጫራቾች የሚሰጡት ዋጋ አጠቃላይ የትራንስፖርት ዋጋውን የሚሸፍን ይሆናል፡፡ ሌሎች ከሥራው ጋር የተያያዙ ማንኛውንም ወጭዎች በተጠሰው ዋጋ ላይ ተጠቃሎ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። አሸናፊው ድርጅት ዕቃዎቹን የአማራ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት ባህርዳር ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
14. ጨረታው ሲከፈት የጨረታውን ሂደት ለማዛባት የሚሞክር ተጫራች ከጨረታው ውድድር ውጭ ይሆናል፤ ለወደፊቱም ድርጅቱ በሚያደርገው ሌሎች ጨረታዎች ላይ አይሳተፍም፡፡ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናም ይወረሳል፤
15. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግና ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል አይችሉም፡፡
16. ድርጅቱ አሸናፊውን ተጫራች በሚመርጥበት ጊዜ የሚገዛውን መጠን እንደ አስፈላጊነቱ እስከ 30% ፐርሰንት ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል
17. የፋይናንሻል ጨረታው መክፈቻ ቀን በቴክኒካል ለተመረጡ ብቻ በደብዳቤ ይገልጻል፡፡
18. ተጫራቾች ተወዳድረው ያሸነፉበትን ዕቃ ናሙና እንዲያቀርቡ በተጠየቁ ጊዜ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

**ለበለጠ መረጃ፡-** በስልክ ቁጥር 058 226 52 03 መደወል ይችላሉ፡፡

አድራሻ፡- ባህርዳር ቀበሌ 14 ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ት/ቤት ጎን ወይም አዲናስ ጠቅላላ ሆስፒታል ፊት ለፊት

# የውሃ ሥራዎች ኮርፖሬሽን